

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀምና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ /2006 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ማውጫ


**ክፍል አንድ** .......... 1

መግቢያ .......... 1

የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አመሠራረት .......... 1

የአገልግሎቱ ራዕይ .......... 2

የአገልግሎቱ አላማ .......... 2

የአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባር .......... 2

የአገልግሎቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል .......... 2

የፋይናንስ ምንጭ .......... 3

የኦዲቱ ዓላማ .......... 3

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ .......... 3

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች .......... 4

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት .......... 4

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ .......... 5

የግዥና የውል አስተዳደር የአሰራር ሥርዓት መግለጫ /Process description/ .......... 6

**ክፍል ሁለት** .......... 7

የኦዲት ግኝቶች .......... 7

አገልግሎቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እና ዓላማውን ለማስፈፀም ያለው የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅምን በተመለከተ፤ .......... 7

አገልግሎቱ የባለበጀት መ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት ማሰባሰብ፣ መለየትና ማደራጀትን በተመለከተ፤ .......... 9

አገልግሎቱ ባዘጋጀው እስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት ዓመታዊ እና የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀቱን፣ ዕቅዱን ተግባራዊ ማድረጉን እንዲሁም የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ፤ .......... 11

የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር ተጠንቶ የግዥ አገልግሎት ስለመከናወኑ፤ .......... 13

አገልግሎቱ በሚፈለገው ጊዜና መጠን በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በማከናወን ለተጠቃሚዎች ማድረስን በተመለከተ፤ .......... 15

አገልግሎቱ የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተቀባይነት ማግኘቱን ስለማረጋገጡ በተመለከተ፤ .......... 18

አገልግሎቱ የተጫራቾችን ብቃት እና የስራ አፈፃፀማቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ፤ .......... 19

አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ጨረታ ጊዜ የክፍያ ሁኔታ ስለማመቻቸቱ እና አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን ተቀብሎ የእርምት እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ፤ .......... 22

አገልግሎቱ የሚፈራረማቸው የግዥ ውሎች የተሟላ መረጃ/መመሪያ መያዛቸውና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ ስለመከታተሉ እና ለመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዙሪያ ድጋፍ ስለማድረጉ፤ .......... 22

አገልግሎቱ የሚፈራረማቸው የግዥ ውሎች የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ /Specification/ የያዙ መሆናቸውን እና በዛ መሰረት ግዥ መፈፀሙን በተመለከተ፤ .......... 29

አገልግሎቱ የሚፈራረመው የግዥ ውል የገበያ ጥናትና
መረጃን የተመረኮዘ መሆኑን በተመለከተ፤ ..... 35
አገልግሎቱ በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለማስረከቢያ ቦታ፣ጊዜ እንዲሁም
የዋጋ ማስተካከያ ስለሚደረግበት ሁኔታ ያካተተ መሆኑን በተመለከተ፤ ..... 37
አገልግሎቱ ጥራታቸውን የጠበቁ ዕቃዎች በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛቱን እና
ጥቅል ግዥ በመፈፀም ኢኮኖሚያዊ  ጥቅም ማስገኘቱን በተመለከተ፤ ..... 38
አገልግሎቱ ከሌሎች አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓት
ስለመዘርጋቱ እና ግንዛቤ መፍጠሩን በተመለከተ፤ ..... 41
አገልግሎቱ የምክርና ስልጠና አገልግሎት ስለመስጠቱና እና
የመወያያ መድረኮችን ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤ ..... 44

**ክፍል ሦስት** ..... 46
የመደምደሚያ ሃሳቦች ..... 46

**ክፍል አራት** ..... 50
የማሻሻያ ሃሳቦች ..... 50
**አባሪ 1** ..... 1
የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ..... 1

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

### የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አመሠራረት

1. መንግሥት በየዓመቱ ከሚመድበው በጀት ውስጥ እስከ 70 በመቶ የሚደርሰው ለግዥ የሚውል ነው፡፡ የግዥ አፈፃፀም ውጤታማነት የሚለካው ፍላጎትን ለሚሟላት ወጪ ለተደረገ ገንዘብ ተገቢውን ጥቅም ማስገኘት መቻሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከፍተኛ መጠን ያለው የመንግሥት ሀብት የሚፈስበት የመንግሥት ግዥ ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘቱ አፈፃፀሙ አዝጋሚና ለብክነት የተጋለጠ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለግዢ ሥራ የሚመደቡ ባለሙያዎችም በቂ የትምህርት ዝግጅት የሌላቸውና በልምድ ብቻ የሚሠሩ የነበሩ በመሆናቸው እና ንብረት ማስወገድንም በተመለከተ ጥቅም ላይ የማይውል የመንግሥት ንብረት በተገቢው ጊዜ የማስወገድ ባህል በአገራችን የተለመደ አልነበረም፡፡ በዚሁ ምክንያት በመንግሥት መ/ቤቶች ይዞታ ሥር የሚገኙ ንብረቶች ለአገልግሎት በማይፈለጉበት ጊዜ በወቅቱ ስለማይወገዱ ለዝናብና ፀሐይ ተጋልጠው በሚደርስባቸው እንግልት ዋጋቸው እየቀነሰ መንግሥት ከንብረቶቹ ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም የሚያጣ ከመሆኑም በላይ ለሌላ አገልግሎት ሊውል የሚገባውን ቦታ ጨምሮ በመያዝ ከፍተኛ ችግር አስከትሏል፡፡

2. ስለሆነም ለመንግሥት ግዥ ለተከፈለ ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም መገኘቱን ለማረጋገጥ፣ የግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር ሥርዓቱን የበለጠ ሀብትና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሁም ግልጽ አሠራርን መሠረት አድርጎ በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያስችሉ አደረጃጀቶች እንዲኖሩት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

3. በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ረገድ በተደረገው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት የመንግሥት ግዥ አፈፃፀምን ብቃት በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል ይጠቅማሉ ተብሎ የታመነባቸው የጥናቱ ሀሣቦች የሕግ መሠረት እንዲኖራቸው ለማድረግ ተሻሽሎ በወጣው የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ከተካተቱ ለውጦች መካከል አንደኛው በመንግሥት መ/ቤቶች በወል የሚፈለጉ እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በአንድ ማዕከላዊ ተቋም አማካኝነት አጠቃሎ መግዛት ጠቃሚ መሆኑ በመታመኑ ነው፡፡

4. ይህን ሥራ በኃላፊነት የሚመራ እራሱን የቻለ አካል ማደራጀት ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በሚል ስያሜ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣ ደንብ ቁጥር 184/2002 ይህ አገልገሎት እንዲቋቋም ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ይህን ለመንግሥት መ/ቤቶች፣ ለክልል መንግሥታት፣ ለልማት ድርጅቶችና ለግሉ ዘርፍ ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ

ለማግኘት እንዲያስችል በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ግዥ አፈፃፀም መታየቱ ስለተወሰነ በዚህ የደሰሳ እና የቅኝት ኦዲት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

## የአገልግሎቱ ራዕይ

5. በአገሪቱ ውስጥ የላቀና ተመራጭ የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሰጭ ተቋም መሆን፡፡

## የአገልግሎቱ አላማ

6. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃና አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ ተመጣጣኝ ዋጋ፣ በተገቢው ጊዜና በተፈላጊው ጥራት እንዲቀርቡ ማስቻል፣ በሽያጭ እንዲወገዱ ውሣኔ የተሰጠባቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ንብረቶች በተቀላጠፈ አኳኋን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲወገዱ ማስቻልና ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች በዕቃና አገልግሎት ግዢ እንዲሁም በንብረት ማስወገድ ረገድ እገዛ ማድረግ ነው፡፡

## የአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባር

7. **በደንብ ቁጥር 184/2002 ዓ.ም. የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል:-**
   - ዝርዝራቸው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መመሪያ የሚወሰን የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ያከናውናል፤
   - ግምታቸው በሚኒስቴሩ መመሪያ ከሚወሰን የገንዘብ መጠን በላይ የሆነ በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ኃላፊነት ሥር ያሉ በሽያጭ እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶች ይሸጣል፣
   - ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ለክልል መንግሥታት እና ለግሉ ዘርፍ፤
     - በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሠረተ የአገር ውስጥና የአለም አቀፍ የግዥ አገልግሎቶች ይሰጣል፣
     - የግዥ አፈፃፀምን የሚመለከት የምክርና ሥልጠና አገልገሎት ይሰጣል

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የአገልግሎቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

8. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሆኖ በስራ አመራር ቦርድ፣ በአንድ ዋና ዳይሬክተር፣ በሁለት ም/ዋና ዳይሬክተር እና በአስር የስራ ሂደቶች ተዋቅሯል:: በዋና ዳይሬክተር ስድስት የስራ ሂደቶች ያሉ ሲሆን የተቀሩት አራቱ የስራ ሂደቶች በአንድ ም/ዋና ዳይሬክተር ይመራሉ፡፡ ለአገልግሎት መ/ቤቱ በጠቅላላው 234 የሰው ሀይል የተፈቀደ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ለግዥና ለውል አስተዳደር የስራ ሂደቶች የተፈቀደው 56 የሰው ሀይል ነው፡፡ ዋና

ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተሩን ጨምሮ በባለስልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ በስራ ላይ ያለው የሰው ሀይል እስከ ሰኔ30/2005 ዓ.ም 107(46%) ሰራተኞች ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 43(40%) ሴቶችና 64(60%) ወንዶች ናቸው፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ በኤም.ኤስ.ሲ/ኤም.ኤ ደረጃ ያሉ 5(5%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 68(63%)፣ ኮሌጅ ዲፕሎማ/10+3/ 18(17%)፣ እንዲሁም የቀለም ትምህርት ያላቸው ሰራተኞች 16(15%) የሚይዝ መሆኑን ከሰው ሀብት ልማት ሪከርድና ጠቅላላ አገልግሎት የስራ ሂደት ከተሰበሰበ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

9. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሥራውን የሚያንቀሣቅሰው ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት ሲሆን በ2003፣ በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመታት ,ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ እንደቅደም ተከተላቸው ብር 172,680,452.62፣ ብር 237,705,596.00 እና ብር 122,965,220.16 በድምሩ ብር 533,351,268.78 ከመንግሥት ፀድቆ ለሚተገብሯቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የተመደበለት ሲሆን ከተመደበለት በጀት ውስጥ በ2003 ዓ.ም [1]ብር 172,076,852.81(99.6%)፣ በ2004 ዓ.ም. ብር 431,681,049.88(182%) እና በ2005 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 30/2005 ዓ.ም. ብር 275,592,648.93(224%) በድምሩ ብር 879,350,551.62 ጥቅም ላይ አውሏል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

10. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ፣ የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ በተመጣጣኝ ዋጋ በተገቢው ጊዜና በተፈለገው ጥራት አቅርቦቱ ስኬታማና ብቃት ባለው መልኩ መፈፀሙን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀ የአሰራር ስርዓት መኖሩን ማረጋገጥ ሲሆን፤ አፈፃፀሙ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ አጥጋቢ ያልሆነባቸውን ምክንያቶች በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

11. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዢ አፈፃፀምና ውጤታማነትን ማረጋገጥ የሚል ነው፡፡

[1] በ2004 እና በ2005 ዓ.ም. ከበጀት በላይ አገልግሎቱ የተጠቀመበትን ምክንያት የፌዴራል ዋና ኦዲተር የ2004 እና የ2005 ዓ.ም. የፋይናንሻል ሪፖርት ላይ ተገለጿል፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

12. ከላይ ለተገለጸው የኦዲት አካባቢ ሶስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ የተለዩ ሲሆን በመጀመሪያው የትኩረት አቅጣጫ ሥር ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም ፡-

    1. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ለመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀም፤ የግዢ ደንብና መመሪያዎችን ተከትሎ መከናወኑን፣ ለተገልጋዮች አቤቱታ ተገቢውን ምላሽ መስጠቱን እና ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የግዢ ሂደት መኖሩን እንዲሁም የክትትል ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፡፡

        1.1 አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ፤ የግዢ ደንብና መመሪያዎችን ተከትሎ ማከናወኑን እንዲሁም የግዢ ሂደት አደረጃጀት መፍጠሩን ማረጋገጥ፤

        1.2 አገልግሎቱ የሚያከናውነው የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን እና የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታዎች ተቀብሎ ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ የሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

    2. የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ ተመጣጣኝ ዋጋ የተፈለገው ጥራት ያለው ዕቃ በሚፈለገው መጠን፣ በተገቢው ጊዜና ብቃት ባለው መልኩ መከናወኑን መገምገም፤

    3. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥን በተመለከተ በደንቡ መሰረት የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የመረጃ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፤

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

13. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሶስት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች እና ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 43 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) የተዘጋጁ ሲሆን የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 184/2002፣በማዕቀፍ ግዥ ዙሪያ የተመለከቱትን በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት የተዘጋጀ የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ፣ የግዥና የውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያ ቁጥር 02/2004፣የተገልጋዮች የቅሬታ፣ የአቤቱታ አቀራረብና አቀባበል ሥርዓት የውስጥ መመሪያ

ቁጥር 04/2004 ቃለ-መጠይቆች እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

14. ኦዲቱ የተከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2003 በጀት ዓመት እስከ 2005 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ የተሰራውን ሥራ ሲሆን፤ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የተለያዩ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን በመከለስ፣ ለሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በተመረጡ የመንግስት ባለ በጀት መ/ቤቶች፣ ለልማት ድርጅቶችና ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችን በናሙና መርጦ በአካል በመገኘት የተለያዩ የኦዲት መረጃዎችን በመሰብሰብና ማስረጃዎችን በመከለስ ነው፡፡ እንዲሁም ለሌሎች ባለድርሻ አካላት የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና መጠይቆችን በመላክ እና አሰራሩን በአካል ተገኝቶ በመመልከት ነው፡፡

15. በዚህም መሠረት ቅርንጫፍ መ/ቤቶችን ጨምሮ ከ173 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ከፍተኛ የግዥ በጀት ተጠቃሚ ከሆኑት የመንግስት መ/ቤቶች /High spending budgetary organizations/ ውስጥ ለሰባት ሚኒስቴር መ/ቤቶች(የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ግብርና ሚኒስቴር፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ማዕድን ሚኒስቴር፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ትምህርት ሚኒስቴርና የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር)፣ ለሁለት ባለስልጣን መ/ቤቶች(የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንና የጨረራ መከላከያ ባለስልጣን)፣ ለሶስት ኤጀንሲዎች (ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ካርታ ስራ ኤጀንሲ፣ ሆርቲካልቸር ኤጀንሲና የደረጃዎች መዳቢ ኤጀንሲ)፣ ለሶስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት(ጅማ ዩኒቨርስቲ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ) ለአንድ ፅ/ቤት(ውሃ ልማት ፈንድ ፅ/ቤት፣ ለሁለት ልማት የልማት ድርጅቶች እና ለአምስት ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች በአጠቃላይ ለ23 መ/ቤቶች በአዲስ አበባ ፣በጅማና በወልቂጤ ከተሞች ላይ በአካል በመገኘት የተለያዩ መረጃዎች ተከልሰዋል፡፡ በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀም ዙሪያ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከፍተኛና መካከለኛ የግዢ በጀት ላላቸው ለ 49 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና ለ10 የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች መጠይቆች ተልኮ መረጃዎችን በመሰብሰብ ና በመከለስ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## የግዥና የውል አስተዳደር የአሰራር ሥርዓት መግለጫ

## /Process description/

16. የግዥና የውል አስተዳደር የስራ ሂደት በፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች/common user items/፣ እንዲሁም ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ ከክልል ወይም ከተማ አስተዳደሮች እና ከግሉ ዘርፍ የሚቀርብለትን የግዥ አገልግሎት ጥያቄ ወይም የፍላጎት ጥያቄን መሠረት በማድረግ ተፈላጊ መረጃዎችን በዓይነትና በመጠን ለይቶ ያደራጃል፣ የግዥ ዓይነቶችን ለይቶ የግዥ ዕቅድም ያዘጋጃል፡፡ ለእያንዳንዱ ግዥ ስፔስፊኬሽንን ወይም ቢ.ጋር /Terms of Reference / ያካተተ የተሟላ የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት በግዥ ዕቅዱ መሠረት ለየግዥው ዓይነት የጨረታ ማስታወቂያ የማውጣትና የጨረታ ግምገማ ምዘና በማካሄድ አሸናፊውን ተወዳዳሪ /ተጫራችን/ በመለየት ውጤቱን ለሚመለከታቸው ያሳውቃል፡፡ እንዲሁም የማዕቀፍ ውል ይገባል አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ (International Competitive Bid) ከሆነ እንደአስፈላጊነቱ ሌተር ኦፍ ክሬዲት/LC/ መክፈት፣ የትራንዚትና ክሊሪንግ ሥራዎችን ተከታትሎ ያስፈፅማል፡፡ ይህ የስራ ሂደት ከላይ ከተገለጹት ተግባራት በተጨማሪ የተሸናፊና አሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ /Bid Bond/ እንዲመለስ የማድረግ፣ የጨረታ ማስከበሪያው ጊዜውን እየጠበቀ የማራዘሚያ ደብዳቤ የማዘጋጀት፣ የውል ማስከበሪያ /Performance Bond/ የመቀበል፣ የመያዝና የማስተዳደር እንዲሁም የተገዙት ዕቃዎች/አገልግለቶች በውሉ መሠረት ለተጠቃሚዎች መድረሳቸውን በማረጋገጥ የውል አስተዳደር ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

**ሀ. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ለመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀም፤ የግዢ ደንብና መመሪያዎችን ተከትሎ መከናወኑን፣ ለተገልጋዮች አቤቱታ ተገቢውን ምላሽ መስጠቱን እና ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የግዢ ሂደት መኖሩን እንዲሁም የክትትል ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤**

**አገልግሎቱ በደንቡ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እና ዓላማውን ለማስፈፀም ያለው የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅምን በተመለከተ፤**

17. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በደንቡ የተሰጠውን ኃላፊነት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግና ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስችል የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅም (Human and Institutional Capacity) ሊኖረው ይገባል፡፡

18. አገልግሎቱ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ የግዥ እና የውል አስተዳደር የስራ ሂደት በመዋቅሩ ከተፈቀደለት 56 የሰው ኃይል ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም. 30 (54%) በሥራ መደቡ ላይ ሰው ያልተመደበባቸው ሲሆን፣ በአጠቃላይ ለአገልግሎቱ ከተፈቀደው 234 የሰው ኃይል ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም. 127ቱ (54 በመቶ) ሰው ሳይቀጠርባቸው ክፍት እንደሆኑ ከአገልግሎቱ በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

19. በዚህ ረገድ ከታዩት ክፍተቶች ውስጥ አንዱን ለመጥቀስ በአገልግሎቱ የግዥ አፈፃፀም ሂደቱን የሚያሳዩ የግዥ ሰነዶችና ማስረጃዎች (ከጨረታ ሰነድ ጀምሮ ዕቃው ገቢ እስከሆነበት ድረስ) በተደራጀ ሁኔታ ያልተቀመጡ ሆነው የተገኙ ሲሆን ለዚህም ክፍል ራሱን የቻለ የግዥ ማስረጃዎችን የሚይዝ ባለሙያ ባለመመደቡ መሆኑ ይታያል፡፡

20. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የግዥ ሙያ ለበርካታ ሥነ-ምግባር ችግር የተጋለጠ በመሆኑ አገልግሎቱ ባለሙየዎችን ሲቀጥር ከፍተኛ ጥንቃቄና ማጣራት የሚያደርግ መሆኑና በገበያ በማስታወቂያ የተገኘ ባለሙያ በስፋት ስለማይወሰድ መዋቅሩን ሙሉ በሙሉ በሰው ኃይል በፍጥነት ለመሙላት ባለመቻሉ የታየ ክፍተት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

21. ይሁን እንጂ አገልግሎቱ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለመፈፀምና ከአገልግሎቱ ሊገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በቅልጥፍናና ውጤታማ በሆነ አሰራር ለማግኘት እንዲቻል በተሟላ

የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅም ካልጎለበተ በስተቀር የተቋቋመበት አላማ ሊሳካ የማይችል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

**አገልግሎቱ የግዥ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም**

**በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን በተመለከተ**

22.በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

23. አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን በተሟላ ሁኔታ የማያረጋግጥ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

24. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የግዥና የውል አስተዳደር የውስጥ አሠራር መመሪያ ቁጥር 02/2004 መሠረት ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ብሎ ካስቀመጣቸው ውስጥ ተሽከርካሪንና የመድህን አገልግሎትን በተመለከተ፤

- ❖ ፍላጎት አሰባስቦ በወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት የማዕቀፍ ስምምነት ተፈራርሞ በራሱ ዕቅድ መሰረት ግዥ የማይፈፅምና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ትዕዛዝ ሲመጣለት ብቻ ግዥ የሚፈፅም መሆኑ፣
- ❖ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች፣ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች፣ የደንብ ልብሶች፣ የኤሌትሪክ ዕቃዎችና መሳሪያዎች፣ መፅሐፍትና መፅሔቶች እና የህንፃ መሳሪያዎችና የግንባታ ዕቃዎች ለመንግስት መ/ቤቶች ግዥዎችን ያልፈጸመ መሆኑ፣

25. በተጨማሪም በ2004 በጀት ዓመት ግዥ በእስክሪብቶና በእርሳስ ላይ ተጫራች ሳያገኝ ቀርቶ በግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ድጋሚ ማስታወቂያ ማውጣት ሲገባው በቂ ተወዳዳሪ አልተገኘም በማለት ማስታወቂያ ያላወጣ መሆኑን በ2004ዓ.ም ከስራ አመራር ቃለ ጉባኤ ለመረዳት የተቻለ ሲሆን፤ እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16.26 ቁጥር 1 እና 2 ላይ በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እንደአስፈላጊነቱ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30 በመቶ የሚደርስ የቅድመ ክፍያ ሊሰጥና አቅራቢዎች በውሉ መሠረት ከሚጠይቁት የቅድሚያ ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንደአቅራቢው ምርጫ ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የተረጋገጠ ቼክ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል የሚል ቢሆንም የመንግሥት መ/ቤቶች ከፌዴራል መንግስት የክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003ና ከግዥ አፈፃፀም መመሪያ ውጭ ክፍያ ፈፅመው ዕቃ እንዲረከቡ በአገልግሎቱ በታዘዙት መሰረት መ/ቤቶቹ ለሚገዙት ዕቃ ከመረከባቸው በፊት ቅድመ ክፍያ እንዲፈጽሙ መደረጋቸው እና የቅድመ ክፍያ እንዲፈፅሙ ሲደረግም የዕቃ

አቅራቢዎች ከሚወስዱት የገንዘብ መጠን ጋር ለመንግስት መ/ቤቶቹ እኩል የሆነ ዋስትና እንዳላቀረቡ ከመ/ቤቶቹ ከተከለሱ ዶክመንቶችና ከአገልገሎቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

26. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ የተሽከርካሪንና የመድህን አገልግሎትን በተመለከተ፤ ከፋይናንስ አቅም ጋር ታይቶ ተሽከርካሪ በማዕከል የሚገዛ እንደመሆኑ መጠን አገልግሎቱ በራሱ ፍላጎት አሰባስቦ የሚገዛበት አሠራር አለመኖሩ፣ የመድህን አገልግሎትም ቢሆን በየአመቱ የሚገዛ ሳይሆን ለ3 ዓመታት የሚያገለግል አጠቃላይ ውል ከአገልግሎቱ ጋር ከተፈራረመ በኂላ ተጠቃሚዎች ውላቸውን በየዓመቱ እያደሱ የሚጠቀሙበት አሠራር እየተተገበረ ስለሆነ ለነዚህ ዕቃዎች ፍላጎት የሚሰባሰብበት ሁኔታ አለመኖሩን እንዲሁም በእስክሪብቶና በእርሳስ ድጋሚ ጨረታ ማውጣቱ ተጨማሪ ጊዜ ስለሚወስድና ሥራ እንዳይበደል በማሰብ ተግባራዊ አለመደረጉን እና ቅድሚያ ክፍያን በተመለከተ በአንዳንድ አቅራቢዎች አስገዳጅነት ጥቂት መ/ቤቶት ቅድመ ክፍያ መፈጸማቸው በመታወቁ ማስተካከያ የተደረገበት መሆኑና በተጨማሪም ምንም እንኳ የቢሮ ችግር ቢኖርም ለግዥ ሰነዶች ራሱን የቻለ ክፍልና ሰነዱን የሚይዝ ሠራተኛ የግዥ ባለሙያ ቢመደብም በአሁኑ ወቅት የግዥ ሠነድ ብቻ የሚይዝ ባለሙያ ቅጥር ለመፈፀም በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

27. የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም ይኸውም የተሽከርካሪ አቅም ታይቶ በማዕከል ስለመገዛቱና የመድህን አገልግሎትም ለ3 ዓመታት የሚያገለግል አጠቃላይ ውል ፍላጎት ስለመሰባሰቡ የግዥና የውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያው ከመውጣቱ በፊት የሚታወቅ ከነበረ መመሪያው ላይ መካተት ያልነበረበት በመሆኑና መመሪያው ከወጣ በኂላም የታወቀ ከሆነ መመሪያውን ማሻሻል ወይም እስኪሻሻል የተፈቀደ የፅሁፍ መረጃ እንዲኖር መደረግ ይገባ የነበረ ሲሆን፤ በተጨማሪም እስክሪብቶና እርሳስ ድጋሚ ጨረታ ማውጣቱ ተጨማሪ ጊዜ ስለሚወስድና ስራ እንዳይበደል በማሰብ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን በተመለከተ ደግሞ መመሪያው የተጣሰው ድጋሚ ጨረታ ማውጣት እንደሚቻል ቀደም ብሎ ባለመታሰቡ የዕቅድ ችግር መኖሩን የሚያመለክት በመሆኑና ቅድመ ክፍያንም በአንዳንድ አቅራቢዎች አስገዳጅነት የተፈፀመና የተስተካከለ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም የግዥና የውል አስተዳደር መመሪያው በራሱ በአገልግሎቱና በአቅራቢዎች በተገቢው መንገድ ተግባራዊ አለመደረጉን የሚያመለክት ስለሆነ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## አገልግሎቱ የባለበጀት መ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት ማሰባሰብ፣ መለየትና ማደራጀትን በተመለከተ፤

28. በግዥና ውል አስተዳደር እና በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን /Common user items/ በተመለከተ በኤጀንሲው የተወሰኑትን የመ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት በየዓመቱ ከመጋቢት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ለቀጣይ በጀት ዓመት የሚገዙ ግዥዎችን ሊያሰባስብ እና በአስር የስራ ቀናት ውስጥ በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት ደረጃ እና በሚገኙበት ቦታ በተለያየ ምድብ/በሎት/ ሊለይ እንዲሁም ከገበያ

ጥናት የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ ከባለበጀት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን ፍላጎት ማደራጀት አለበት፡፡

29. አልግሎቱ በ2003 ዓ.ም. ለ2004 በጀት ዓመት ግዥ የፍላጎት ማሳወቂያ ደብዳቤ ከመጋቢት ወር በፊት ቀድሞ መላክ ሲገባው የፍላጎት ማሳወቂያ ደብዳቤውን የላከው ማሰባሰብ ካለበት 5 ወር ዘግይቶ በ22/11/03 የላከ መሆኑ፣ በ2004 ዓ.ም. ለ2005 በጀት ዓመት ማሰባሰብ ከነበረበት ጊዜ ከ2-8 ወራት ዘግይቶ እስከ ጥቅምት 20/2005 ዓ.ም የላከ መሆኑንና፣ እንዲሁም በ2005 ዓ.ም. ለ2006 በጀት ዓመት ግዥ ፍላጎት ደግሞ የካቲት 27/2005 ዓ.ም. የመ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት እንዲያሳውቁት የጠየቀ ቢሆንም አገልግሎቱ ከመጋቢት1 ጀምሮ ፍላጎት የሚያሰባስብበት ጊዜ ስለሆነ የመንግስት መ/ቤቶችም በ3 ቀናት ውስጥ ከዕቅዳቸው በመነሳት ፍላጎታቸውን ሞልተው ለመላክ በቂ ጊዜ ስላልተሰጣቸውና በተባለው ጊዜ ፍላጎት መላክ እንዳልቻሉ እና የግዥ ሂደቱ እንዲጓተት ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. እንዲሁም ግዥዎችን በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት ደረጃ እና በተለያየ ምድብ /በሎት/ የሚመድብበት የተቀመጠ የጊዜ ገደብ ስለመኖሩ ተጠይቆ ማስረጃ ያልቀረበ ሲሆን በተጨማሪም በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች ላይ የገበያ ጥናት ባለመኖሩ አገልግሎቱ ከባለበጀት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን ፍላጎት በገበያ ጥናት መሰረት ዕቃው በገበያ ላይ ስለመኖሩ በማረጋገጥ እንደማያደራጅ ታውቋል፡፡

31. ስለሁኔታው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የግዥ ፍላጎት ማሰባሰቢያ ጊዜ መዘግየትን በተመለከተ አገልግሎቱ ሥራ ሲጀምር በቂ ልምድ ያላቸው ሠራተኞችን ይዞ ስላልነበረ እንዲህ ዓይነት ክፍተት መታየቱ ብዙም አስገራሚ አለመሆኑ ሆኖም በየጊዜው ሥራው እየተሻሻለ መሄዱ እንዲሁም የግዥ ፍላጎት እንዲላክ በየዓመቱ የፌዴራል መ/ቤቶች ሰርኩላር ቢበትንም በተወሰነው ቀነ ገደብ ተፈላጊውን ፍላጎት የሚልኩት የተወሰኑ መ/ቤቶች ብቻ መሆናቸው እና በአገልግሎቱ አሥር ቀንም ሳይጠበቅ ከሥር ከሥር መረጃዎች የሚደራጁና የተቀመጠው አሥር ቀን ሳያበቃ መረጃዎች በዓይነት በጥራት ደረጃና በምድብ /በሎት/ ተደራጅተው ተጨማሪ ፍላጎታቸውን የሚልኩ መ/ቤቶች እንደሚጠየቁ በአጠቃላይ መረጃው ከሥር ከሥር እየተደራጀ የሚቆይ በተጨማሪም ከባለበጀት መ/ቤቶች የተሰበሰበው ፍላጎት በገበያ ላይ ስለመኖሩ በማረጋገጥ ማደራጀትን በተመለከተ የጋራ መጠቀሚያ ዕዎች ግዥ የሚፈጸመው በግልጽ ጨረታ በመሆኑ በግልጽ ጨረታ የሚፈጸመው ግዥ በገበያ ላይ የሚገኝ ዕቃ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

32. ይሁን እንጂ ተሻሽሏል የተባለው የፍላጎት ማሰባሰቢያ ጊዜው በ2004ዓ.ም በሁለተኛው ግዥ በጀት አመት እስከ 8 ወራት ዘግይቶ የፍላጎት መጠየቂያ ደብዳቤ የተላከላቸው መ/ቤቶችም ያሉ ሲሆኑ እንዲሁም በ2005ዓ.ም ለሶስተኛው ግዥ በጀት አመትም መ/ቤቶች ከዕቅዳቸው ጋር በማመሳከር ፍላጎታቸውን የሚያሳውቁበት በቂ ጊዜ ሳይሰጣቸው ፍላጎት መሰብሰብ ካለበት በሶስት ቀን ልዩነት የካቲት 27 የፍላጎት መጠየቂያ ለመ/ቤቶች የላከ በመሆኑና መረጃው ከሥር ከሥር አስር ቀን ሳያበቃ

መረጃዎች በዓይነት በጥራት ደረጃና በምድብ /በሎት/ እየተደራጁ ናቸው ስለተባለውም ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃዎቹ ተጠይቀው ባለመቅረባቸው እንዲሁም በግልጽ ጨረታ ግዥን መፈፀም ዕቃው በገበያ ላይ ስለመኖሩ አስተማማኝ አመላካች ቢሆን ኖሮ አገልግሎቱ ግልፅ ጨረታ ካወጣ በኋላ አቅራቢ ባለመገኘቱ የቀሩ ዕቃዎች ግዥዎች መኖራቸው ታውቋል፡፡ስለሆነም አገልግሎቱ በመመሪያው መሰረት የጊዜ ገደቡ እንዲጠበቅ ከተገልጋዮች ጋር በጋራ የሚወያይበት መድረክና በራሱም በኩል ሊሰሩ የሚገባቸው ስራዎች በወቅቱ ሊሰሩ ይገባል፡፡

## አገልግሎቱ ባዘጋጀው እስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት ዓመታዊ እና የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀቱን፣ ዕቅዱን ተግባራዊ ማድረጉን እንዲሁም የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ፤

33. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ዙሪያ ባዘጋጀው እስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት ዓመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅ፣ ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ እና ባሰባሰበው የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የግዢ ፍላጎት መሰረት የግዢ ዕቅድ በሚያዘጋጅበት ወቅት የታወቁትን የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የግዢ ፍላጎቶችና ለእያንዳንዱ ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዢ ዘዴ በመምረጥ በግዥ ዕቅዱ ውስጥ ሊያመላክት እንዲሁም በመርሐ-ግብር በማስደገፍ ለባለበጀት መ/ቤቶችና ለኤጀንሲው ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

34. ይሁን እንጂ የአገልግሎቱ ከ2003-2007 ዓ.ም የውጤት ተኮር ስርዓት የ5 ዓመት እስትራቴጂክ ዕቅድ ሲታይ፤

- የትኛው ተግባር በየትኛው ዓመት እንደሚሰራ ተለይቶና በስትራቴጂው የታቀደው ተግባር ከዓመታዊ ዕቅድ ጋር በየዓመቱ በተጣጣመ መልኩ ያልተቀመጠ መሆኑ፤
- እንዲሁም ዓመታዊ ዕቅድ ቢያዘጋጅም ከ2003-2005 ዓ.ም አገልግሎቱ የአፈፃፀም አቅሙን በማሳደግና የአሰራር ስርዓቱን በማሻሻል በሀገሪቱ የነበረውን የተበታተነ የግዥ አሰራር ወደ ተማከለ (ጥቅል) ግዥ በተገቢው ጊዜ፣ ጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ግዥ ለመፈጸም እና የግዥ ስርዓትን ለማሻሻል ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ ጋር ዘመናዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ፣ ክትትል፣ አደረጃጀት በቴክኖሎጂ የመጠቀም አሰራር ስርዓት ተግባራዊ የማድረግ እና የተሻለና ጥራቱን የጠበቀ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦት ለባለድርሻ አካላት በሚመች መልኩ የማዘጋጀት ስራዎች ያልተከናወኑ መሆኑ፤
- በ2003 ዓ.ም ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር ለመረከብ አቅዶ እስከ ሐምሌ 22/2003 ዓ.ም ከኤጀንሲው ተከታትሎ ያልተረከበ መሆኑና የግዥ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ተፈላጊ መረጃዎችን ከሁሉም ባለበጀት መ/ቤቶች የማሰባሰብ ስራ ቢታቀድም ያልተሰራ መሆኑ ከአገልግሎቱ የ9 ወር የዕቅድ አፈፃፀም የተገኘ መሆኑ፤

- ❖ በ2004 ዓ.ም. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በሚሰራው ሥራ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላትና ለተገልጋዮች የማስተዋወቅ ሥራ አለመከናወኑ፣ በ2004ና በ2005 ዓ.ም በግዥዎች ላይ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር የቅንጅት ስራ ታቅዶ አለመከናወኑ፣

35. እንዲሁም በ2004ና በ2005 በጀት ዓመት መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በራሱ ፕሮግራም በሚያከናውነው የአገልግሎት ግዥን በተመለከተ ዕቅዱን ተግባራዊ ስለማድረጉ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ያላቀረበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. አገልግሎቱ በግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ከ2003-2005 ዓ.ም በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ ለሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚገዛውን ዕቃና አገልግሎት ዓይነት፣ ግዥው የሚፈፀምበትን የገንዘብ ምንጭ፣ የግዥው ምድብ፣ ለግዥው የተያዘው የበጀት ግምት፣ የተመረጠው የግዥ ዘዴ፣ የግዥው ዓይነትና ግዥን ለመፈጸም የሚወስደው ጊዜ፣ ጨረታ የሚወጣበት ወይም የሚካሄድበት እና ግዥው ተጠናቆ ርክክብ የሚፈፀምበት ጊዜ በማካተት የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የግዥ ዕቅድ አላዘጋጀም፡፡

37. በተጨማሪም ከ2003-2005 ዓ.ም. ድረስ ባሰባሰበው የግዢ ፍላጎት መሰረት በመርሐ-ግብር የተደገፈ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ግዢ ዕቅድ በማዘጋጀት ለባለበጀት መ/ቤቶችና ለኤጀንሲው አላሳወቀም፡፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ 16 መ/ቤቶች እና በሰርቬይ መጠይቅ ከተሰበሰበው 24 መ/ቤቶች ውስጥ 15ቱ /62%/ የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ከ2003-2005 ዓ.ም. በመርሃ ግብር የተደገፈ በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች ግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት ልኮላቸው እንደማያውቅ የገለፁ ሲሆን፤ በዚህም ምክንያት መ/ቤቶቹ በአገልግሎቱ በኩል የሚገዙትንና የማይገዙትን ዕቃዎች እና የአልግሎቱ ግዥ የሚፈፀመው መቼ እንደሆነ በጊዜ በማወቅ በራሳቸው የሚገዙትን ዕቃዎች አቅደው ግዥ በወቅቱ እንዳያከናወኑ ያደረገ መሆኑና በጀታቸውን በአግባቡ ከአገልግቱ ኘሮግራም ጋር አጣጥመው ለመጠቀም እንዳላስቻላቸው፣ የመ/ቤታቸውን ዕቅድ እንዳያሻሽሉና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በየ3ወሩ የሚላከው ዕቅድና የሥራ መርሃ ግብር ላይ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ፍላጎት/ካሽ ፍሎው/ ትክክለኛውን ለማሣወቅ እንዳላስቻላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

38. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የግዥ ስርዓትን ለማሻሻል ከባለድርሻ አካለት ጋር ዘመናዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ፤ ክትትልና አደረጃጀት በቴክኖሎጂ የመጠቀም የአሰራር ስርዓትን በተመለከተ አገልግሎቱ እንደ አዲስ የተቋቋመ ከመሆኑ አንፃር እነዚህን ግዙፍ የማሻሻያ ስርዓትና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦት በአጭር ጊዜ አሟልቶ ለመስራት አለመቻሉንና በአገልግሎቱ ክትትል ማነስ የተፈፀመ አንዳችም ችግር አለመኖሩን እንዲሁም አገልግሎቱ በሚሰራው ስራ ዙሪያ የማስተዋወቅ ስራ በቂ ነው ባይባልም ሙከራ መደረጉን፤በተጨማሪም በግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት በመርሀ ግብር የተደገፈ የግዥ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለኤጀንሲውና ለመ/ቤቶች መላኩን

በተመለከተ አገልግሎቱ የግዥ ዕቅዱን የሚያቀርበው ለኤጀንሲው እንጂ ለባለበጀት መ/ቤቶች አለመሆኑንና የሚገዛውን ዓይነት እንደማያሳውቅ ግን ዘግይቶም ቢሆን ዝርዝሩን እንደሚያሳውቅ እንዲሁም ከ2003-2005ዓ.ም አገልግሎቱ ስራ የጀመረበትና በቂ ልምድ ያለው ሰራተኛ የሌለበት ዘመናት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

39. ይሁን እንጂ አገልግሎቱ የግዥ ዕቅዱን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ በግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 12ና በዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ አባሪ 1 መሰረት የተሰራ የግዥ ዕቅድ አላቀረበም፡፡

**የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር ተጠንቶ የግዥ አገልግሎት ስለመከናወኑ፤**

40. በደንብ ቁጥር 182/2002ና በአዋጅ ቁጥር 649/2001 መሰረት የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መመሪያ የሚወሰን የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አጥንቶ በሚልከው መሠረት ግዥ ሊያከናውን ይገባል፡፡

41. ይሁን እንጂ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ዝርዝራቸው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለሚወሰን የመንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች በጋራ ለሚፈለጉ እቃዎች የግዥ ውል ከመፈራረም ውጭ የዕቃ ግዥ የማያከናውን ሲሆን፤ እንዲሁም ለአገልግሎት ግዥም የግዥ ውል እንደማይፈራረም እና ግዥም እንደማያከናውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. በኦዲቱ ወቅት በዚህ ዙሪያ ከተጠየቁት 12 መ/ቤቶች ውስጥ 12ቱም(100%) አገልግሎቱ የዕቃ ግዥውን ባለመጀመሩ መ/ቤቶቹ ዕቃውን ለመረከብ በመመላለስ የገንዘብና የጊዜ ብክነት እንዳጋጠማቸው፣ የግዥ በጀት በአግባቡ ለመጠቀም እንዳላስቻላቸው፣ የሥራ ጫናና በሥራ አፈፃፀም ላይ ክፍተት የፈጠረባቸውና በተለይም መ/ቤቶቹ የአቅም ውስንነት ስላላቸው ኮምፒውተሮችና ፎቶ ኮፒ ማሽኖች ለማስጠገን እንደሚቸገሩ፣በዚህም ምክንያት ዕቃዎቹ አገልግሎት ሳይሰጡ ተቀምጠው እንደሚቀሩና በዝቅተኛ ዋጋ ጥራት ያለው አገልግሎት ከጥሩ ዋስትና ጋር ከሚያቀርቡ ድርጅቶች ግዥ በመፈጸም ከጥቅል ግዥ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ማግኘት እንዳልቻሉና ተሸከርካሪዎች በዕቃ አቅርቦት ችግር ጋራዥ እየቆዩና በወቅቱ የማይሰሩ መሆኑን የመ/ቤቶቹ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

43. እንደዚሁም በሰርቬይ መጠይቅ ከተበተነላቸው 24 የመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ 21ዱ (88%) የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎች ውል ከመፈጸም ውጭ ግዥን እንደማያከናውን፣ 16ቱ /67%/ ደግሞ የአገልግሎቶች ግዥ (የጥገና፣ የዕዳት፣ የጥበቃ፣ የመድህን ዋስትና የመሳሰሉትን ግዥ) ያልፈጸመ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

44. በተጨማሪም የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በአዋጁ መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚኖራቸውን ተመሳሳይ ፍላጎት ያላጠና፣ የዕቃና አገልግሎቶች ዝርዝር ያላወጣና ለአገልግሎቱ ያላሳወቀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም ምክንያት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችን ለማወቅ እንዳላስቻላቸው እና ፍላጎታቸውን ሲልኩ በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችን ብቻ ለይተው እንዳይልኩ ያደረጋቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

45. በዚህ ዙሪያ የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ ኃላፊ ስለጥናቱ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አገልግሎቱን ለማቋቋም የተሠራ አንድ የደሰሳ ጥናት እንዳለና ከዚህ በተጨማሪም በ2005 ዓ.ም. ወደ 351 ለሚጠጉ ቋሚና አላቂ የቢሮ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በኮንሰልታንቶች የተጠና አዲስ ጥናት ለደረጃዎች ኤጀንሲ ተልኮ የእቃዎቹ ደረጃ እየፀደቀ እንደሆነና የፀደቀው ዝርዝር በቀጣይ ለተጠቃሚ አካላት ታትሞ እንደሚሠራጭ የአጠቃቀም ሥልጠና ከተሰጠ በኂላ ሥራ ላይ እንደሚውል የገለጹ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ከኤጀንሲው የተገኘው የደሰሳ ጥናት ታይቶ አገራዊ ተጨባጭ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ የመንግስት መ/ቤቶች ፍላጎት በማጥናት ሳይሆን አገልግሎት መ/ቤቱን ለማቋቋም ሲባል የተለያዩ አገሮችን ተሞክሮዎች የተወሰዱ መሆኑን እንዲሁም ደረጃ ያልወጣላቸው ተመሳሳይ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የዕቃዎች ግዥን በተመለከተ እየፈጸመ መሆኑን ሆኖም ግን ውሉ ከመፈጸም ውጭ, ግዥ አያከናውንም መባሉ ግልፅ አባባል አለመሆኑን የገለጹ ሲሆን፤ እንዲሁም በአገልግሎቱ የተደራጀ የገበያ ጥናት መኖሩን ገልጸዋል፡፡

47. በመውጫ ስብሰባ ወቅት የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የሥራ ኃላፊዎች አገልግሎቱ ውል ተፈራርሞ ዕቃውን ገቢ በማድረግ ለመ/ቤቶች ቢያከፋፍል ጥሩ እንደነበር ነገር ግን ግዥ ለመፈፀም ዕቃ የሚያከማችበት ትልቅ መጋዘንና አቅም ስለሌለው አገልግሎቱ የዕቃዎች ግዥ ውል ከመፈራረም ውጭ ግዥ እንደማያከናውን እንዲሁም የአገልግሎት ግዥን በተመለከተ እንደ ዕቃ ግዥ የአገልግሎት ግዥን በራሱ ዕቅድ መሰረት ከመ/ቤቶች ፍላጉት አሰባስቦ ሳይሆን በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ትዕዛዝ መሰረት ለተገዙት ተሽከርካሪዎች የመድን ዋስትና ቢገባም የግዥ ሥርዓቱን ያላከናወነው በአቅም ውስንነት እንደሆነ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

48. ይሁን እንጂ ኦዲቱ በተሰራበት ወቅት ኦዲቱ በሸፈናቸው አመታት የገበያ ጥናት ቡድን በአገልግሎቱ እንዳልነበረ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**አገልግሎቱ በሚፈለገው ጊዜና መጠን በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በማከናወን ለተጠቃሚዎች ማድረስን በተመለከተ፤**

49. በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ሂደት በማጠናቀቅ ዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ለተጠቃሚው አካላት እንዲደርሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡

50. አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ሂደት በማጠናቀቅ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ለተጠቃሚው አካላት እንዲደርሱ አላደረገም፡፡

51. በአገልግሎቱ ከቀረቡ የመ/ቤቶች የግል ማህደር በናሙና እንደታየው በ2004ና በ2005 በጀት ዓመት ግዥዎች ላይ 19 የመንግስት መ/ቤቶች አገልግሎቱ በጀመረው የግዥ ሂደት የግዥ ትዕዛዝ ያስተላለፉበት ዕቃ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ተከታትሎ እንዲደርሳቸው አለማድረጉ ታውቋል፡፡

52. በመ/ቤቶቹ ማህደር ውስጥ ከተደረጉት የፅሁፍ ልውውጦች እንደተመለከተው አቅራቢዎች ጋ ሄደው የግዥ ትዕዛዝ ያስተላለፉበት ዕቃ በመጋዘናቸው ውስጥ የሌለ መሆኑ እንደገለፁላቸው የመጀመሪያው አቅራቢዎች ጋ የግዥ ትዕዛዝ ሰጥተው እስከ 1 ወር ከ2ሳምንት በመዘግየቱ ምክንያት አገልግሎቱ አሸናፊ የሆኑ ሌሎች አቅራቢዎችን ከአንድ ወር በኃላ ቢመድብላቸውም በአዲሱ አቅራቢ ድርጅቶቹ ደግሞ በጀት አመቱ ለመጠናቀቅ 2 ሳምንት እስከሚቀረው ድረስ ለመ/ቤቶቹ ያላቀረቡላቸው መሆኑ፣ እንዲሁም 6 መ/ቤቶች ሌላ አሸናፊ አቅራቢ ድርጅት ጋ ተመድበው መግዛት እንዲችሉ አገልግሎቱን ጠይቀው ክምችት እንደሌላቸውና ዕቃዎቹ ወደ ሀገር ውስጥ እንደሚያስገቡ መ/ቤቶቹ ተከታትለው ግዥ እንዲፈፅሙ የበጀት ዓመቱ መጨረሻ አካባቢ አገልግሎቱ ለመ/ቤቶቹ ያሳወቀው ቢሆንም መ/ቤቶቹ ለረጅም ጊዜ በመመላለስ እቃዎቹን ማግኘት ባለመቻላቸው የግዥ ትዕዛዙን የሰረዙ መ/ቤቶች /ለምሳሌ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲና የኢትዮጵያ ሲቭል አቬየሽን ባለሥልጣን/ እንዳሉ ከመረጃው ተገኝቷል፡፡

53. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በአካል ከታዩ መ/ቤቶች ውስጥ 9ኙ ዕቃ ለመረከብ አቅራቢዎች ጋ ሄደው በመጋዘን የሌላቸውና ተሸጠው ያለቁ መሆናቸውን በመግለፅ ሌላ ቀጠሮ እንደተሰጣቸው፤ እንዲሁም የዋጋ ማስተካከያ እስኪሰራላቸው ድረስ መጠኑን /ብዛቱን/ ቀንሰው እንዲወስዱ የነገሯቸው መሆኑንና እስከ በጀት አመቱ ማብቂያ ድረስ ማግኘት እንዳልቻሉ፣ ለኦዲቱ በተሄደበት ወቅትም ችግሩ እንዳልተቀረፈ አስታውቀዋል፡፡ ይህም በመሆኑ የሚፈለገው ዕቃ ለሚፈለገው ዓላማ በወቅቱ ለማዋል አለማስቻሉን፣ ስራዎች በወቅቱ እንዳይከናወኑ እንቅፋት የሆነባቸው እና በስራ አፈፃፀም ላይም ችግር የፈጠረባቸው፣ ከመሆኑም በላይ፣ ለተጨማሪ የግዥ ሂደትና አላስፈላጊ የግዥ ስርዓት ውስጥ እንዲገቡ እንዳደረጋቸው ገልፀዋል፡፡

54. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ፣ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን በሚፈለገው ጊዜ ለተጠቃሚዎች ማድረስን በተመለከተ የግዥ ሂደት በተለያዩ ምክንያቶች ሊዘገይ እንደሚችል፣ የቴክኒክ ግምገማ ቶሎ አለመጠናቀቅ፣ የአቅራቢዎች ቅሬታ፣ የቅሬታ አጣሪ ቦርድ ለቅሬታው የሚሰጠው ምላሽ የመሳሰሉት ከታሰበው በላይ ጊዜን ሊያራዝሙ እንደሚችሉ፤ ነገር ግን መጠንን በተመለከተ ከባለበጀት መ/ቤቶች የተሰበሰበው ፍላጎት  የተጠየቀው ሙሉ ለሙሉ ወደ ግዥው እንደሚሄድ የግዥ ፍላጎት ካሳወቁት መጠን በታች የተሰጣቸው መ/ቤቶች አለመኖራቸው እንዲሁም የተወሰኑ አቅራቢዎች ዕቃ ቶሎ ያስገቡ እንደነበረና እስከጭራሹ ያላስገቡ ሁለት አቅራቢዎች ያስያዙት የውል ማስረከቢያ ተወርሶ በውሉ መሰረት ባለመፈፀማቸው አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለመንግሥት ግዥና ንብረት አስተደደር ኤጀንሲ የተላከና ዋጋ ካልተስተካከለልኝ ብሎ አቅርቦት ያቋረጠም አቅራቢ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

55. ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ አገልግሎቱ ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የግዥ ሂደቱን /ፍላጎት ከማሰባሰብ እስከ ውል መፈራረምና የጨረታ አሸናፊ አቅራቢ ድርጅቶ እስከማሳወቅ ያለውን/ በጊዜ ሊያከናውንና በኦዲቱ ወቅት አብዛኛው መ/ቤቶች በሚፈልጉት ጊዜ ያላገኙና በመጠንም  ያላገኙ መ/ቤቶች መኖራቸውና ይህንንም ለአገልገሎቱ ማሳወቃቸውን ለአገልግሎቱ በጻፉት ደብዳቤ ለማወቅ ስለተቻለ አገልግሎቱ ይህንን ተከታትሎ ለመ/ቤቶች በሚፈልጉት ጊዜና መጠን እንዲያገኙ ድጋፍ አለማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

### የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስገወድ  አገልግሎት የግዥ ሂደት ከመንግስት መ/ቤቶች የበጀት አመት /ኘሮግራም/ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በተመለከተ፤

56. የግዥ ሂደቱ ከመ/ቤቶች የበጀት አመት /ኘሮግራም/ የተጣጣመ በገበያው ላይ ሰፊ አቅርቦት የሚገኝበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረገና ሰፊ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል በማድረግ የግዥ መፈጸሚያ ጊዜን ሊወስን ይገባል፡፡

57. የመንግስት መ/ቤቶች የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ቢሆንም በአገልግሎቱ አብዛኛውን ጊዜ መ/ቤቶች ግዥ እንዲፈፅሙ የሚደረገው የበጀት ዓመቱ 1ኛ ሩብ ዓመት ካለፈ በኋላ በመሆኑ፤ አገልግሎቱ የግዥ ሂደቱን ከመንግስት መ/ቤቶች የበጀት ዓመት/ፕሮግራም/ ጋር የተጣጣመ በማድረግ የግዥ መፈፀሚያ ጊዜን አልወሰነም፡፡ በኦዲቱ ወቅት ከታዩት 15 የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ 14ቱ(93%) እና  የሰርቬይ መጠይቅ ከተበተነላቸው 24 የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ለ14ቱ **(58 %)** ከ2004-2005 ዓ.ም. በአገልግሎቱ ያለው የግዥ ሂደት  ከመንግስት መ/ቤቶች የበጀት አመት /ኘሮግራም/ ጋር የተጣጣመ ባለመሆኑና በገበያው ላይ ሰፊ አቅርቦት የሚገኝበት ጊዜ ታሳቢ ያላደረገና ብዙ ተወዳዳሪ እንዲሳተፍ የሚያስችል በማድረግ የግዥ መፈጸሚያ ጊዜን የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት  ባለመወሰኑ  ምክንያት ዕቃዎችን በሚፈለገው ጊዜ በየሩብ ዓመቱ እንዳያገኙ

ያደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንደዚሁም የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችም ተጠይቀው ዕቃውን በወቅቱ ማቅረብ እንዳልቻሉ እና መ/ቤቶች የግዥውን በጀት ለመጠቀም አስቸጋሪ የሆነባቸው መሆኑን እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀማቸው ደረጃ እንዲቀንስ እንደ አንድ ምክንያት እንደሚወሰድ በተጨማሪም በአገልግሎቱ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ በአገልግሎት መ/ቤቱ የአፈፃፀም ችግር ምክንያት በመ/ቤታቸው በድጋሚ መውጣቱን ገልፀዋል፡፡

58. ይህንን በተመለከተ ለበጀት ዓመቱ የተመደበላቸውን በጀት በወቅቱ መጠቀም ካልቻሉትና በጀት ከተመለሰባቸው መ/ቤቶች ውስጥ የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በ2005 በጀት ዓመት በሂሳብ መደብ 6313፣ ከተበጀተው በጀት ውስጥ ብር 149,265.76 ሳይጠቀሙበት ተራፊ በጀት በመባል በሰኔ ወር 2005 ዓ.ም ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የባንክ ሂሳብ ፈሰስ የተደረገ መሆኑና ብር 40,706.55 ለላፕ ቶፕ ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ በጀት ዓመቱ በማለፉ ምክንያት ክፍያው በተሰብሳቢ የተያዘባቸው መሆኑን፤ የውሃ ልማት ፈንድ በሂሣብ መደብ 6212 የተያዘ የስቴሽነሪ በጀት የተመለሰበት መሆኑን፣ የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን በ2004 በጀት ዓመት የበጀት ዓመቱ በማለፉና ብዙ የመገልገያ ዕቃዎች በግዥ ባለመቅረባቸው የተቸገረና ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ ፈሰስ የሆነበት መሆኑን፣ የግብርና ሚኒስቴር የመ/ቤቶች የግዥ ዕቅድ ከሐምሌ 7 እስከ ሰኔ 30 ቢሆንም፣ አገልግሎቱ ከፍላጎት መጠየቂያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ግዥ ሂደቱ ስለሚጓተት በወቅቱ ግዥ እንዳይፈፀም ከማድረጉም በተጨማሪ የመ/ቤቱ የበጀት አጠቃቀም እስከ ግንቦት 30/05 ሰባ በመቶ /70%/ ብቻ መሆኑን፤ እንዲሁም የጅማ ዩኒቨርስቲ በ2004 በጀት ዓመት ወረቀት፣ ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተርና ሌሎች የሚፈለጉ ዕቃዎችን በወቅቱ ሳይገዛ በጀት ዓመቱ የተጠናቀቀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

59. በሌላ በኩል ከአገልግሎቱና ከመ/ቤቶቹ በተሰበሰበ ማስረጃ መሰረት 9 መ/ቤቶች የግዥ ሂደቱ ከመ/ቤቶች የበጀት ዓመት ወይም የግዥ ሠሌዳ ጋር ያልተጣጣመ በመሆኑ የተመደበላቸውን በጀት መጠቀም እንዳልቻሉና ለአገልግሎቱ ከጻፏቸው ደብዳቤዎች ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን፤ ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት በ2004 ዓ.ም. አገልግሎቱ የግዥ ሂደት አጠናቆ ውል የተፈራረመው የ3ኛ ሩብ አመት ላይ የካቲት 1 ሲሆን፤ እንዲሁም በ2005 ዓ.ም. በ2ኛው ሩብ ዓመት ውል የተፈራረሙ ቢሆንም፤ እስከ ታህሳስ 30/05 ዓ.ም የዕቃ አቅራቢ ደርጅቶች ዕቃ ማቅረብ ያልጀመሩ በመሆኑ፣ 3 መ/ቤቶች በጀቱን ለመጠቀም ብለው ግልፅ ጨረታ አውጥተው በመከልከላቸው ምክንያት የግዥ ሂደቱን ለማካሄድ ለማስታወቂያ በመክፈል ለአላስፈላጊ ወጪና ጊዜ ብክነት የተጋለጡ መሆኑን እንዲሁም 4 መ/ቤቶች ደግሞ ከአገልግሎቱ የአሸናፊ ተጫራቾች ደብዳቤ ላይ ከተገለፁት ዕቃዎች ውጭ በራሳችሁ ግዥ መፈፀም ትችላላችሁ የሚለውን ትዕዛዝ ሲጠባበቁ በመቆየታቸው የተነሳ፣ የመንግስት መ/ቤቶች በአገልግሎቱ በኩል ያልተገዙትን ዕቃዎች ጨረታ አውጥተው ለመግዛት ጊዜ እንዳልበቃቸውና በጀቱ ተመላሽ እንዲሆንባቸው ከማደረጉም በተጨማሪ አላስፈላጊ የግዥ ስርዓት ውስጥ እንዲገቡ የተደረጉ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

60. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የግዥ ሂደት ከመንግሥት መ/ቤቶች ከ2004-2005 በጀት ዓመት መጣጣሙን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመንግሥት መ/ቤቶች የግዥ ፍላጎታቸውን በወቅቱ ከላኩ ግዥ በወቅቱ እንደሚፈጸምና አገልግሎቱ በበጀት አመቱ የሚፈጽማቸውን ዕቃዎች ዝርዝር በወቅቱ ለመ/ቤቶች እንደሚልክ፣ እንዲሁም በዝርዝር ውስጥ የሌሉትንም መ/ቤቶች የመንግሥት ግዥ ሥርዓት ጠብቀው እንዲገዙ በወቅቱ መገለጹን እና በ2005 ዓ.ም. የግዥ ፍላጎት እንዲልኩ ከተጠየቁት 174 መ/ቤቶች ውስጥ በወቅቱ የላኩት 69 መ/ቤቶች ብቻ መሆናቸውን በዚሁ ምክንያት የመ/ቤቶቹ የግዥ ፍላጎት መረጃ ሲጠበቅ የግዥ ሂደት አለመጀመሩን ገልጸዋል፡፡

**አገልግሎቱ የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በግዥ**
**አፅዳቂ ኮሚቴ ተቀባይነት ማግኘቱን ስለማረጋገጡ በተመለከተ፤**

61. በግዥ መመሪያው መሠረት አገልግሎቱ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ለሚፈፀም በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚዘጋጅ ማንኛውም የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በኮሚቴው ተቀባይነት ሊያገኝ እና ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸው የማዕቀፍ ግዥዎችን በአለም አቀፍ ግዢ ጨረታ መግዛት አለበት፡፡

62. ይሁን እንጂ በኦዲቱ አሠራሩ ሲታይ፣ በአገልግሎት መ/ቤቱ ከ2003-2005 ዓ.ም. በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ለሚፈፀም በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚዘጋጅ የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተቀባይነት ማግኘቱ በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ እንደማይረጋገጥ ታውቋል፡፡

63. በመመሪያ አንቀጽ 16/3/3 ላይ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መሠረት ለሚፈጸም ግዥ የሚዘጋጅ ማንኛውም የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በኮሚቴው ተቀባይነት ማግኘቱ መረጋገጥ እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም ከመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በ2005 ዓ.ም. የክትትል ሪፖርትና የሥራ አመራር ቦርድ ቃለ ጉባኤ ለመረዳት እንደተቻለው በ2004 ዓ.ም. ለብር 28,173,094.00 የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እና በ2005 ዓ.ም. ለብር 355,021,356.23 የጨረታ ሰነዶች በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ተቀባይነት ሳያገኝ፣ በአገልግሎቱ ባለሙያዎች ተገምግሞ በሥራ አመራር ቦርድ የጸደቀ መሆኑን ለመረዳት የተቻለ ሲሆን፤ እንዲሁም አገልግሎቱ በ15/9/2004 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ እስከ 100 ሚሊዮን ለሚሆኑ ግዥዎች የግዥ ኮሚቴ በማቋቋም ግዥው እንዲጸድቅ የወሰነ ቢሆንም በ2005 በጀት ዓመት ከ100 ሚሊዩን ብር በላይ የሆኑትን ግዥዎች በሥራ አመራር ቦርድ ብቻ በማፀደቅ ግዥ ተፈፅሟል፡፡

64. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ለማየት እንደተቻለው የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አልግሎት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ እና የግዥና የውል አስተዳደር የውስጥ አሠራር መመሪያ ውጭ አገልግሎቱ በ2004 እና በ2005 ዓ.ም. ከ10,000,000 ብር በላይ ዋጋ ያላቸው የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ግዥ

በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ መገዛት ሲገባቸው፣ በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ከ9 ድርጅቶች ግዥ ፈጽሞ የተገኘ ሲሆን፤ ስለጉዳዩ አገልግሎት ተጠይቆ በ2004 ዓ.ም. በልዩ ሁኔታ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እንደፈቀደለት ምላሽ ቢሰጥም፣ ማስረጃው ተጠይቆ ያልቀረበና በተመሳሳይ ሁኔታ ይኸው አሠራር በ2005 ዓ.ም. በአገልግሎቱ እንደተደገመ ለማወቅ ተችሏል፡፡

65. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፤ የአገልግሎቱ ግዠዎች መጠን በጣም ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን በቦርድ እንዲፀድቁና ኤጀንሲው እንዲያውቀው እንደተደረገና ከ100 ሚሊዮን ብር በታች ያሉ ግዥዎች የማፅደቅ አሠራር እየተተገበረ መሆኑን፣ እንዲሁም በአለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ግዥ አለመከናወኑ በተመለከተ መረጃው በጊዜው ካለመቅረቡ በስተቀር በሁለቱም ዓመታት በኤጀንሲው ፈቃድ ግዥው በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ እንዲፈፀም የተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

66. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በ2004 ዓ.ም. ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ስለማስፈቀዱ ማስረጃ አልተገኘም፡፡ በኛ አስተያየት የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲም ቢሆን ከመመሪያ ውጭ መፍቀዱ አግባብነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## አገልግሎቱ የተጫራቾችን ብቃት እና የስራ አፈፃፀማቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ፤

67. በአገልግሎቱ እጩ ተጫራቾች የግዥ ውልን ከመፈራረማቸው በፊት ውሉን ለመፈጸም የሚያስችል ብቃት እንዳላቸው ሊረጋገጥና እንዲሁም ነባር የዕቃና አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች በድጋሚ ለመወዳደር የበፊት የሥራ አፈጻጸማቸውን መታየት ይኖርበታል፡፡

68. ይሁን እንጂ አገልግሎቱ እጩ ተጫራቾች የግዥ ውልን ከመፈራረማቸው በፊት ውሉን መፈጸም የሚያስችል ብቃት እንዳላቸው ወጥ በሆነ መልኩ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው የመገምገሚያ መስፈርት መሰረት የቅድመ ቴክኒክና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ (prelimenarey and technical evaluation) ተደርጎ መረጋጋጡ መረጃ ተጠይቆ የተሟላ መረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡ በኦዲቱ ወቅት ለ2004 በጀት ዓመት ግዥ በጨረታ ሰነዱ መሰረት የቅድመ ቴክኒክ፣ የፋይናንሻል ግምገማ እና ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት የፍተሻ ውጤት ለተጫራቾች በተሰጠው ኮድ መሰረት ዝርዝር ቴክኒክ ግምገማ ስለመደረጉ እንዲሁም የተጫራቹን ስምና ኮድ ወይም በመ/ቤቱ ባለሙያዎች ተተርጉሞ ውጤቱ የተቀመጠበትን የሚገልፅም ሆነ ሌሎች የግዥ ሰነድ ማስረጃዎች በተደጋጋሚ ተጠይቀው ተሟልተው ያልቀረቡ መሆኑ፤ በተጨማሪም የ2005 በጀት ዓመት ግዥ ከሎት 13-15 ላለው ዕቃ በባለሙያ የተተረጎመው ውጤት አለመገኘቱ፤ በኮምፒውተርና ተጓዳኝ ዕቃዎች በቴክኒክ ግምገማ ውጤት ላይ ዕቃው በናሙና ታይቶ ስለመረጋገጡ ወይም ለወደፊት አቅራቢዎች ዕቃውን ሲያቀርቡ ናሙናው እንደሚታይ አለመካተቱና እንደዚህ ዓይነት ተሞክሮም በአገልግሎቱ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

69. ከአገልግሎቱ በተገኘው ማስረጃ መሰረት ለ2005 በጀት ዓመት በግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 19 ተራ ቁጥር 2.1 "ሀ" ና "ለ" እና በአንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 19 ተራ ቁጥር 2.1 ከተቀመጠው ውጪ በጨረታ ሰነዱ የሁሉም ተጫራቶች የገቢና ወጪ ሂሳብ የሚያሳይ የባንክ ማስረጃ፣ አግባብነት ያለው የውል አፈጻጸም እንደነበራቸው፣ የሦስተኛ ወገን ምስክርነት የሚገልፅና የርክክብ ወቅት የሚያሳይ ማስረጃ ሳይታይ፤ በፋይናንሻል ክፍል ውጭ ከተቀመጠው ተጨማሪ መስፈርት /Additional criteria/ ላይ ለተጫራቾች የተቀመጠውን የፋይናንስ አቅምና የጥሬ ገንዘብ ፍሰት እንዲሁም መልካም የስራ አፈፃፀም እና ተጫራቾቹ ላለፉት ሁለት ዓመታት ያላቸው የባለሙያ ብቃትና ችሎታ የሚያሳይ ማስረጃ መስፈርቶች ላይ የቅድመ ቴክኒክ ገምጋሚ ባለሙያዎች ሲገመግሙ ብዙም አስገዳጅ ናቸው ተብሎ አይታሰብም በማለት በቃለ-ጉባኤ በመያዝ ብቻ ስምምነት ላይ በመድረስ ከመስፈርቱ እንዲወጡ ያደረጉ መሆኑን ለመረዳት የተቻለ ሲሆን በሌላ በኩል ለ2005 በጀት ዓመት በየእጩ ተጫራቾች የአጠቃላይ የዕቃ አቅርቦት የአራት አመት እና የሁለት አመት ከውሉ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ዕቃዎች በማቅረብ ያገኙትን መልካም የሥራ አፈጻጸም በውጤቱ ላይ የተካተተ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

70. እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ተወዳድረው ያለፉ የ9 ተጫራቾች ፋይል ሲታይ የአገልግሎቱ የጨረታ ሰነድ ላይ ከተቀመጠው የመገምገሚያ መስፈርት ጋር ወጥ ባልሆነ ሁኔታ 5ቱ የዕቃ አቅርቦት መልካም ሥራ አፈጻጸም በተሟላ መልኩ ያላቀረቡ ሲሆን፣ 2 አቅራቢዎች ደግሞ ሳያቀርቡ ያሸነፉ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

71. በተጨማሪም በ2005 በጀት ዓመት ሌዜር ኮምፒውተር ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር እና ኤም.ኤፍ.አይ ትሬዲንግና ኦፊስ ሶሉሽን ኃ.የተ.የግ.ድ የዕቃ አቅርቦትን የስራ አፈፃፀም የምስክር ወረቀት "general Experiences" በተመለከተ የ4ዓመት ማቅረብ ሲገባቸው፣ በሁሉም ዕቃዎች ላይ የ2 ዓመት ብቻ አቅርበው ለ2005 በጀት ዓመት ጨረታ ተወዳድረው እንዲያሸንፉ ተደርጓል፡፡ ሁለቱም እነዚህ ድርጅቶች በአፈፃፀም ብቃት ማነስ ምክንያት ፐርፎርማንስ ቦንዳቸውን መቀማታቸውና በመንግስት መ/ቤቶች በዕቃ አቅርቦት ላይ ችግር ያስከተሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

72. በሌላም በኩል ለ2005 በጀት ዓመት ግዥ የቴክኒክ ግምገማን በተመለከተ ከሎት1-12 ለተመደቡ ዕቃዎች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፀው መሰረት በመ/ቤቱ የተቋቋሙ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ገምግመው ሪፖርት ቢያደርጉም የቴክኒክ ገምጋሚ ኮሚቴው ካስቀመጠው ውጤት ውጪ በሎት1ና ከ6-12 ላይ (ስናፕ፣ ናኖዳስና ጁፒተር የተባሉ አቅራቢ ድርጅቶች) ውጤታቸው ከ90% በታች መሆኑ እና ቴክኒካሊ እንደወደቁ እየታወቀ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊና የግዥ ባለሙያዎች ተጫራቾቹ በፋይናንስ ግምገማ እንዲካተቱ በማድረግ በአጠቃላይ የቴክኒክና የፋይናንስ ግምገማ ላይ አሸናፊ ሆነው ዕቃ እንዲያቀርቡ በቃለ ጉባኤ መወሰኑ እንዲሁም ከሎት1-16 ግምገማ ሲደረግ የተጫራቾች ውጤት ከ40% ምን ያህል እንዳገኙ ሪፖርት ቢደረግም ውጤቱን በማሻሻል ተጫራቾቹ በአጠቃላይ ውጤት ማለፍ የሌለባቸው

ተጫራቾች እንዲያልፉ ተደርጓል። በዚህ ዙሪያ አላለፋችሁም የተባሉ አቅራቢ ድርጅቶች እንዴትና በምን ምክንያት ብቁ እንዳልሆኑ እንዲገለፅላቸው አገልግሎቱን የጠየቁ ቢሆንም አገልግሎቱ አጥጋቢ መልስ እንዳልሰጣቸው ከተፃፉ የቅሬታ ደብዳቤዎች ላይ ለማየት ተችሏል።

73. በአጠቃላይ በ2004ና በ2005 ዓ.ም ግዥዎች የፀደቁት በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ሳይሆን፣ ከግዥ አፈፃፀም መመሪያ ውጪ በስራ አመራር ቦርድ መሆኑና እንዲሁም በ2005 ዓ.ም. የስራ አመራር ቦርዱ የቴክኒክ ግምገማ ውጤትን በተመለከተ ተጫራቾች ስለማለፋቸውና ስለመውደቃቸው በጥልቀት ሳያይ በፋይናንሻልና ከፋይናንሻል ውጭ ከተቀመጠው ተጨማሪ መስፈርት/Additional criteria/ ውጤት ብቻ ግዥው እንዲፈፀም ማድረጉ ታውቋል።

74. ከዚህም በተጨማሪ አገልግሎቱ በ2004 ዓ.ም. አሸናፊ የነበሩትን ስናኝና ራደካል ኃ/የተ/የግ ማህበራትን በጊዜ የማቅረብ ችግር እንዳለባቸው በተደጋጋሚ ከተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች ቅሬታ ቢቀርብም፣ የበፊቱ የሥራ አፈጻጸማቸውን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ በ2005 ዓ.ም እነዚሁ ድርጅቶች በድጋሚ አሸናፊ ሆነው እንዲያቀርቡ አድርጓል።

75. በ2004 ዓ.ም. ጨረታ ተወዳድረው አሸናፊ የሆኑት ስናኝና ራደካል ኃ/የተ/የግ ማህበራት የቀድሞ መልካም ስራ አፈፃፀማቸው ሳይታይ በድጋሚ በ2005 በጀት ዓመት አሸናፊ በመሆናቸው በግዥ ላይ ችግር የፈጠሩ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ ከአገልግሎቱ በናሙና በታየው የመ/ቤቶች የግል ማህደር 7 መ/ቤቶች ቦክስ ፋይል፣ መካከለኛ ማስተወሻ ደብተርና የፎቶ ኮፒና የፕሪንተር ወረቀቶችን ለመግዛት የግዥ ትዕዛዝ አስተላልፈው ግዥ እንዲፈጽሙ ከአገልግሎቱ ቢገለጽላቸውም፣ አቅራቢዎቹ ዕቃውን በወቅቱ ሊያስረክቡ ያልቻሉ ሲሆን መ/ቤቶቹ ዕቃውን ለመረከብ በሄዱበት ወቅት እቃው እንደሌለ የተገለፀላቸው መሆኑ እና በተያዘው የጊዜ ገደብ ዕቃዎችን እንዳላገኙ እንዲሁም ጅማ ዩኒቨርስቲ ደግሞ እስከ በጀት ዓመቱ ማብቂያ ወረቀት እንዳላገኘና በአቅራቢዎች ምክንያት መ/ቤቶቹ የሥራ አፈፃፀም ላይ ችግር እንዳስከተለ ገልጸዋል።

76. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ለአገሪቱ አዲስ እንደመሆኑ መጠን በቂ ልምድ ካለመኖር እንዲህ ዓይነት ጥቃቅን ስህተቶች መከሰታቸው የማይቀር ቢሆንም መልካም ሥራ አፈፃፀም ማቅረብ ብቻ በራሱ ለውጤታማነት ቀጣይነት ምስክር ሊሆን እንደማይችል እንዲሁም በቴክኒክ ወድቆ በፋይናንስ ግምገማ የቀረቡ ተጫራቾች የሌሉ መሆናቸውና የተወሰኑ የኮምፒውተር አቅራቢዎች ባሉበት ሀገር እነሱን በተለያየ መስፈርት መጣሉና በየዓመቱ ተመሳሳይ ድርጅቶች በጨረታ እንዳይሳተፉ ማድረጉ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝንበት ሁኔታ ሊከሰት ስለሚችል በዚህ ላይ ተጨባጭ መፍትሄ ሊሆን የሚችል አስተያየት ቢሰጥ አገልግሎቱ ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን፤ በተጨማሪም ማንኛውም ተጫራች በተደጋጋሚ አሸናፊ ስለሆነ ብቻ ለቀጣይ ጨረታ መታገድ እንደሌለበት ገልፀዋል።

77. የበላይ ኃላፊው በቴክኒክ ግምገማ ወድቆ የቀረበ የለም ይበሉ እንጂ ናኖዳስ በቴክኒክ ገምጋሚዎች ወድቆ እንዲሁም ቅድመ ቴክኒክ ግምገማ ውጤት ላይ በሎት 3፣ በሎት 4፣ በሎት 5ና በሎት 6 ውጤታቸው ተሻሽሎ የቀረበ ሲሆን ለምሳሌ በሎት 3 ላይ በመጀመሪያ ግምገማ 40፣ 36፣ 28 እና 34 ውጤት የተሰጣቸው ቢሆንም በድጋሚ ኮሚቴዎቹ ባልተሟሉበት ሁኔታ ምክንያቱ በግልጽ ባልታወቀበት ውጤቱ ተሻሽሎ 34፣ 34፣ 22 እና 28 የተሰጣቸው መሆኑ ከአገልግሎቱ በተገኘው ማስረጃ ቢታወቅም የተለወጠው ውጤት ህጋዊ ስለመሆኑ ምንም አይነት ማስረጃ አልቀረበም ከዚህም በተጨማሪ የጨረታ ተወዳደሪዎች መመዘኛ መስፈርት ጨረታ ሰነዱ ላይ ባለው መሠረት ለሁሉም ተወዳዳሪዎች ወጥ የሆነ አሠራር አለመኖሩና አገልግሎቱ ትኩረት ሰጥቶ የአቅራቢ ድርጅቶች በአግባቡ እየገመገመ እንዳልሆነ የሚያሳይና በየዓመቱ ተመሳሳይ ድርጅቶች በጨረታ እንዳይሳተፉ መደረጉ ሳይሆን በፊት አሸናፊ ሆነው ይቀርብባቸው በነበረው ቅሬታዎችን ግንዛቤ በማስገባት ቢያንስ አቅራቢዎች ባለፈው አፈጻጸማቸው እንዲስተካከሉ ጥረት ሳይደረግ በድጋሚ እንዲወዳደሩ ማድረጉ በኛ እምነት ህጋዊ የሆነ ማስረጃ ባለመቅረቡ እንዲሁም በ2004 የነበረው ችግራቸውን ሳያሻሽል በ2005 ዓ.ም. እንዲደግሙት /ስናኝና ራዲካል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር/ ስላደረገቸው ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ጨረታ ጊዜ የክፍያ ሁኔታ ስለማመቻቸቱ እና አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን ተቀብሎ የእርምት እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ፤

78. የግዥና ውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያ መሰረት የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በአገር ውስጥ ጨረታ ጊዜ ዕቃውን ከተረከበ በኂላ ከ5 እስከ 10 ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን የክፍያ ሁኔታ ሊያመቻች ወይም እንዲመቻች ሊያደርግ እና የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታዎችን ተቀብሎ እንደየደረጃው ከሁለት እስከ አሥር ቀናት ውስጥ ምላሽ ሊሰጥ እንዲሁም ከተገልጋዮች የቀረበው ቅሬታ ወይም አቤቱታ ተጣርቶ ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ በአገልግሎቱ የተቀመጡትን የእርምት እርምጃዎችን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

79. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተጫራቾች አወዳድሮ ግዥ በመፈፀም ዕቃ መረከብ ያልጀመረ ከመሆኑም በላይ የመንግስት መ/ቤቶች ዕቃ እንዲረከቡ ባዘዘው መሰረት ዕቃ ለሚረከቡ የመንግስት መ/ቤቶች ዕቃ ከተረከቡ በኂላ ከ5 እስከ 10 ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን የክፍያ ሁኔታ ያላመቻቸ መሆኑ ታውቋል፡፡

80. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በዕቃ ርክክብና ክፍያ ዙሪያ የግዥ ውሉን ይዘት ሳያሳውቅ ለመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ትዕዛዝ እየሞላችሁ ክፍያውን በመፈፀም እቃ እንድትረከቡ በማለት በ30/06/04 ዓ.ም. በአሸናፊ ተጫራቾች ማሳወቂያ ደብዳቤ በማሳወቁ ምክንያት በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡ 11 የመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ 9ኙ ከአገልግሎቱ ጋር ውል ለተዋዋሉ አሸናፊ ድርጅቶች ክፍያ የፈጸሙት በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9

ላይ ከተገለፀው ውጭ ዕቃውን ተረክበው ሞዴል 19 ከመቁረጣቸው በፊት ቅድመ ክፍያ ፈፅመዋል፡፡ ከነዚህ ንብረቱን ሳይረከቡ ክፍያ ከፈጸሙት መ/ቤቶች ውስጥ፣ 5 መ/ቤቶች ለዕቃዎቹ ቅድመ ክፍያ ከፈጸሙ በኋላ በመጋዘን ባለመኖሩ በወቅቱ ማግኘት ያልቻሉ መሆኑንና 3 መ/ቤቶች ደግሞ አቅራቢ ድርጅቶች አስቀድመው በአካውንታቸው ውስጥ ብሩ እንዲገባ ቢጠይቋቸውም፣ ለአፈፃፀም ስለተቸገሩ የፋይናንስ፣ የግዥ፣ የቴክኒክና የንብረት ክፍል ባለሙያዎቻቸውን በአዲስ አበባ በሚገኙት የአቅራቢ ድርጅቶቹ መጋዘኖች ድረስ ይዘው በመሄድ ዕቃው መኖሩን ካረጋገጡ፣ ካስመረመሩና ሞዴል 19 ከቆረጡ በኋላ የተረከቡ ቢሆንም፣ አሰራሩ ለአላስፈላጊ የአበል፣ የትራንስፖርት፣ የነዳጅ ወጪ እና ዕቃው ንብረት ክፍል ሳይገባ ሞዴል 19 መቆረጡ ደግሞ በመንገድ ላይ ጉዳት ሊደርስበት ይችላል የሚል ከፍተኛ ሥጋት እንዳስከተለባቸው ገልጸዋል፡፡

81. እንዲሁም የክፍያ አፈጻጸም ሥርዓቱን በተመለከተ በዚሁ በአገልግሎቱ በተላለፈው ደብዳቤ መሰረት በክልል የሚገኙና በአዲስ አበባ ያሉ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች፣ ቅድሚያ ክፍያው ከፍተኛ በመሆኑ በገንዘብ ማስተላለፊያ ደብዳቤ (ሌተር ኦፍ ትራንስፈር) ክፍያውን መፈጸም ቢገባቸውም፣ ባልተረከቡት ዕቃዎች ቫትና ውዝሆልዲንግ ታክስ ቀድሞ እንዳይቆረጥ እና ዕቃዎቹ በአቅራቢ መጋዘኖች ላይገኙ ይችላሉ በሚል ስጋት ከ50ሺ ብር በላይ በቼክ በመክፈል አላስፈላጊ የክፍያ ስርዓት ውስጥ እንዲገቡ መደረጋቸውን የስራ ኃላፊዎቻቸው ገልፀዋል፡፡ በኦዲቱም እነዚህ የሚኒስቴር፣ ዩኒቨርስቲዎችና ባለስልጣን መ/ቤቶች የፋይናንስ ግዥና አሰራርን በመተላለፍ ለገንዘቡ ጥንቃቄ ባልተሞላበት ሁኔታ ከብር 50,000 በላይ በቼክ ከብር 74,476.24 እስከ ብር 3,030,859.26 ክፍያ በመፈፀም ግዥ ያከናወኑ መሆኑ ታውቋል፡፡

82. ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች መ/ቤቶችም የዕቃ ርክክብ ሳይፈፅሙ ሞዴል 19 ቆርጠውና ካለዱቤ ሽያጭ/credit invoice/ በባንክ አካውንት ዝውውር ለብርጅቴክ ኃ/የተ/የግ/ድርጅት በቅድመ ክፍያ ከፈፀሙ የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ አሶሳ ዩኒቨርስቲ ብር 295,420.80፣ ወለጋ ዩኒቨርስቲ ብር 1,523,201.20፣ የምግብ ክምችት አስተዳደር ብር 139,309.23 እና የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ብር 152,320.11 ይገኙባቸዋል፡፡ እንዲሁም ለራዲካል ኃ/የተ/የግ.ማህበር የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ብር 97,697.64፣ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ብር 271,641.84፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ብር 127,034.58፣ በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የወንዶ ገነት የደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ ብር 277,276.60፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 362,750ና 14,895,250 ከሁለት አቅራቢዎች በአንድ ጊዜ ግዥ ብቻ 8 የመንግስት መ/ቤቶች በድምሩ በብር18,141,902 የፈፀሙ ሲሆን፣ የፋይናንስ ሕግን በመጣስ ዕቃው ሳይገዛ ቀድሞ ተጨማሪ እሴት ታክስና ሌሎች ቀረጦች የተቆረጡ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

83. በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት ቋሚ ዕቃዎች፣ በተዘጋጀው ስፔስፍኬሽን መሠረት የቀረቡ ስለመሆናቸው በመ/ቤቱ የቴክኒክ ኮሚቴ ተረጋግጠው የገቢ ደረሰኝ ከተቆረጠላቸው በኋላ ዕቃ ግምጃ ቤት ከገቡ በኋላ ክፍያው የሚፈፀም ሲሆን፣ አገልግሎቱ በዚህ ዙሪያ ሁኔታዎችን ባለማመቻቸቱ

እንዲሁም  የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ግዥ ፈፃሚ ለሆኑ የመንግስት መ/ቤቶች በቅድሚያ በሂሳብ ቁጥራቸው  ውስጥ ገንዘቡን  ገቢ አድርገው ስሊፕ ማቅረብ እንዳለባቸው (ብሪጅቴክ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ ጁፒተር ትሬዲንግ፣ ከአልታ ኮምፕውቴክ ኃ/የተ/የግ/ማህበር) የተጠየቁ በመሆናቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶቹ ለአገልግሎቱ ቅድመ ክፍያ መክፈል እንደሌለባቸው ቢያሳውቁም፣ አገልግሎቱ ለአቅራቢ ድርጅቶች ደብዳቤ ከመፃፍ ውጭ ምንም ዓይነት እርምጃ ባለመውሰዱ ምክንያት አዲስ አበባ፣ ባህር ዳርና ደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲዎችና የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር  ከፋይናንስ ሕግ ውጭ ቅድመ ክፍያ በመፈፀም እና  ከፈጸሙም በኋላ ዕቃውን ባለመረከባቸው ሥራው ላይ ጫና እንደተፈጠረባቸው ገልፀዋል፡፡

84. እንዲሁም 3 መ/ቤቶች(የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ፣ ግብርና ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር) ኮምፒተሮችን፣ ፎቶ ኮፒ ማሽንና ፕሪንተር ለመግዛት እንደቅደም ተከተላቸው በትራንስፈርና በቼክ ቅድመ ክፍያ ብር101,546.73፣ ብር 204,058.30ና ብር115,263.99 ለአቅራቢ ድርጅቶች (ለብርጅቴክ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ለአልታ ኮምፒውቴክ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና MFI trading & office solution) የፈጸሙ መሆኑን፣ የኢትዮጵያ ሆልቲካልቸር ኤጀንሲ ቫት ከተቀነሰ በኋላ ከ8 ኮምፒውተሮች አምስቱን ከተረከበ በኋላ 3ቱን ኮምፒውተሮች እስከ 2006 በጀት ዓመት እንዳልተረከበ እና ዕቃው ሳይገባ ብር 44,685.75 በኤጀንሲው እንደተሰብሳቢ መመዝገቡ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ዕቃው በስቶክ መኖሩን በመግለፅ አቅራቢው ቅድመ ክፍያ ያስከፈለው ቢሆንም፣  የበጀት ዓመቱ የተቃጠለ መሆኑ፣ ብሩም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመለሰ እና ድርጅቱ ዕቃውን ማቅረብ ባለመቻሉ እስከ ነሐሴ 26/2005 ዕቃውን ያልተረከበ መሆኑን ለመረዳት የተቻለ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዮትና መቱ ዩኒቨርስቲ ለአቅራቢ ድርጅቶች/ለስናፕ ኃ/የተ/የግ/ማህበርና ለብሪጅቴክ/  የግዥ ትዕዛዝ አስተላልፈው ዕቃዎቹን ለመረከብ በሄዱበት ወቅት ክፍያው በባንክ አካውንታችን ካላስተላለፋችሁ በማለት ለማስተናገድ ፈቃደኛ አለመሆናቸው ታውቋል፡፡

85. አገልግሎቱ የመንግስት መ/ቤቶች ለሚያቀርቡት ቅሬታ  በመመሪያው ላይ በተቀመጠው መሰረት ምላሽ ስለመስጠቱ ሲታይ፤ በናሙና የታዩና ከአገልግሎቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች የተለያዩ ዕቃዎችን በጥራትና በወቅቱ አለማቅረብ ችግር በተመለከተ ለአገልግሎቱ ቅሬታ አቅርበው ለ8 መ/ቤቶች  ከግዥ መመሪያ ውጪ ከ12 እስከ 25 ቀናት ዘግይቶ  ምላሽ የተሰጣቸው መሆኑንና ለ6 መ/ቤቶች ደግሞ ምንም ምላሽ ያልሰጣቸው የተገኙ መሆኑ፣ እንዲሁም  በናሙና ከታዩት አምስት የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ውስጥ ከ4ቱ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች መ/ቤቶች ዕቃ ባለመረከባቸው እና የዋጋ ማስተካከያን በተመለከተ ለአገልግሎት መ/ቤቱ ቅሬታ አቅርበው፤ ላቀረቡት ቅሬታ ምላሽ ያልተሰጣቸው መሆኑ፣ እንዲሁም አንድ ድርጅት (ኤም.ኤፍ.አይ ትሬዲንግ እና ኦፊስ ሶሉሽን) ደግሞ ለባንክ በውጭ

ምንዛሪ ምክንያት ለLC ፈቃድ ደብዳቤ እንዲፃፍለት በተለያየ ጊዜ አቤቱታ ቢያቀርብም ከ2ወር በኋላ ምላሽ እንደተሰጠው ለመረዳት ተችሏል፡፡

86. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ፤

- አገልግሎቱ መ/ቤቶች ለሚያቀርቡት ቅሬታ በተቻለ መጠን በህጉ መሠረት ምላሽ እንደሚሰጥና ሆኖም ግን የአቅራቢ ድርጅቶች ቅሬታን በተመለከተ የዋጋ ማስተካከያ በአገልግሎቱ መረጃ ብቻ የሚፈፀም ሳይሆን የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲንም ስለሚመለከት ምላሽ ለመስጠት እንደሚያስቸግር እና በተቻለ ፍጥነት ግን የውጭ ምንዛሪ ቶሎ እንዲደርሣቸው የተደረገ መሆኑን፤
- ክፍያ ማመቻቸትን በተመለከተ በማዕቀፍ ስምምነት ክፍያ የሚፈጸመው የዕቃ ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ መሆኑን በውሉ ላይ በግልጽ መቀመጡን፣
- አገልግሎቱ የክፍያ ሥርዓት የሚዘረጋ ባለመሆኑ አገልግሎቱ የክፍያ ሥርዓት እንዲጣስ አለማድረጉንና የክፍያ ሥርዓቱን ጠብቀው ክፍያ መፈጸም የተጠቃሚ መ/ቤቶች ኃላፊነት መሆኑ፣
- እንዲሁም ዕቃ ተረክበው ሞዴል 19 ከመቁረጣቸው በፊት ቅድመ ክፍያን የፈጸሙ መ/ቤቶችን በተመለከተ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የአዲስ አበባ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ጽ/ቤት አቅራቢዎች የራሳቸውን ዕቃ ዱቤ መስጠት እንደሚችሉ ነገር ግን የተጨማሪ እሴት ታክስን ዱቤ መስጠት እንደማይችሉና ዕቃው ከመጋዘን ሳይወጣ የተጨማሪ እሴት ታክስ መቀበል እንደሚገባ አቅራቢዎችን እያስገደደ እንደሚገኝ፣
- የዕቃ ርክክብ የተፈጸመው በአቅራቢ መጋዘን መሆኑ ይህም የሆነበት አቅራቢው ያለትራንስፖርት ውሉ ከአዲስ አበባ ውጪ በሚገኙት ዩኒቨርስቲዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ አስቸጋሪ በመሆኑ እና ዩኒቨርስቲዎች ፍላጎታቸውን በወቅቱ ስለማይልኩ የርክክብ ቦታ ዩኒቨርስቲዎች ግቢ መሆኑን መግለጽ ባለመቻሉ መሆኑን ርክክብ በባለበጀት መ/ቤቶች ቢባል አቅራቢዎች ራቅ ባሉት ዩኒቨርስቲዎች የትራንስፖርት ዋጋ አዲስ አበባ ውስጥም ለሚገኙትም ሊያስከፍሉ ይችላሉ በማለት የተደረገ ቢሆንም ለ2007 ዩኒቨርስቲዎች ፍላጎታቸውን በወቅቱ ካሳወቁ እዚያው ዩኒቨርስቲ ጊቢ ውስጥ እንዲሆን እየተሰራ መሆኑን፣
- ዕቃ ሳይረከቡ የበጀት ዓመት ያለፈባቸውን መ/ቤቶች በተመለከተ ለአገልግሎቱ ጉዳዩ በወቅቱ ስላልገለጹ አገልግሎቱ ችግራቸውን ስላላወቀ በተገቢው ሁኔታ እየፈጸሙ ያለ መሆኑን እንደሚገመት ገልፀዋል፡፡

87. ይሁን እንጂ የመንግሥት መ/ቤቶች ለሚያቀርቡት ቅሬታ በህጉ መሠረት ምላሽ ለመስጠቱ የቀረበ ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ፍላጎታቸውን በወቅቱ ለላኩት ዩኒቨርስቲዎችም የዕቃ ርክክቡ ቦታ ዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ እንዲሆንላቸው ያልተደረገ በመሆኑና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መ/ቤቶችና አቅራቢዎች በርካታ ችግር እንዳለባቸው እየታወቀ ችግሩ እንዲፈታ ጥረት አለመደረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

**አገልግሎቱ የሚፈራረማቸው የግዥ ውሎች የተሟላ መረጃ/መመሪያ መያዛቸውና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ ስለመከታተሉ እና ለመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዙሪያ ድጋፍ ስለማድረጉ፤**

88. አገልግሎቱ የሚፈራረመው የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውል ላይ የአቅራቢው ኃላፊነትና ግዴታ፣ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር፣ የግዢ ትዕዛዝ የሚተላለፍበትን፣ ርክክብና ክፍያ የሚፈፀምበትን እና ክትትልና ግምገማ የሚደረግበትን ሥርዓት ሊያካትትና ተግባራዊ ሊያደርግ፣ የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ድርጅት በውሉና በውሉ ላይ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀመ መሆኑን አገልግሎቱ ሊከታተል እና ለመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዙሪያ ድጋፍ ሊያደርግ እንዲሁም ለማዕቀፍ ስምምነት ተፈፃሚነት የተያዘውን የውል ማስከበሪያ ገንዘብ ሊይዝ፣ ሊያስተዳድር እና በውሉ መሰረት አለመፈፀሙን ሲያረጋግጥ ገንዘቡን ሊወርስ ይገባል፡፡

89. አገልግሎቱ በ2004ና 2005 ዓ.ም ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር በተደረገው የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውል ላይ ዕቃውን የሚገዙ ወይም የሚረከቡ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር እንዲሁም ክትትልና ግምገማ የሚደረግበትን ሥርዓት አላካተተም፡፡ በዚህ ዙሪያ በናሙና ከታዩ 5 ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ውስጥ ለ2005 በጀት ዓመት ግዥ ለስናፕ ትሬድንግ እና ለኤም ኤፍ አይ ኦፍስ ሶሉሽን አገልግሎቱ የመ/ቤቶችን ዝርዝር ውሉን ከተፈራረመ ከ2 ወር በኋላ ቢያሳውቃቸውም ከ2003-2005 ዓ.ም. በተፈፀመው የግዥ ውል ላይ የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝር በወቅቱ ባለመካተታቸው 5ቱም የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ለስንትና ለየትኞቹ መ/ቤቶች ዕቃ ማቅረብ እንዳለባቸው ቀድመው እንዳያቅዱ ያደረጋቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

90. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ውል ላይ ዕቃውን የሚገዙ መ/ቤቶች ዝርዝር ስለማካተቱ፤ ከየትኛው አቅራቢ ዕቃ መውሰድ እንዳለባቸው ለባለበጀት መ/ቤቶችና ለአቅራቢው በግልባጭ ስለሚያሳውቁ ለአቅራቢዎች ዝርዝሩን ማሳወቁ አስፈላጊ አለመሆኑ የገለጹ ሲሆን ክትትልና ግምገማ በግዥ ውሉ ላይ ስለማካተቱ ምላሽ አልተሰጠም፡፡

91. አገልግሎቱ አቅራቢው ድርጅቶች በማዕቀፍ ስምምነቱ ውልና በውሉ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀሙ መሆናቸውን በመከታተል ለመንግስት መ/ቤቶች በተሟላ ሁኔታ ድጋፍ ያላደረገ ሲሆን፤ የማዕቀፍ ግዥን በተመለከተ አገልግሎቱ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችንና መ/ቤቶችን የሚከታተልበት ወጥ

የሆነ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ባለመፍጠሩና በውሉም ላይ ባለማካተቱ እንዲሁም የራሱ የሆነ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት በውለታው መሠረት ባልፈጸሙ አቅራቢዎች ላይ ተከታትሎ በወቅቱ ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ የማይወስድ መሆኑ ታውቋል፡፡

92. በኦዲቱ ወቅት በዚህ ዙሪያ ከታዩ 12 መ/ቤቶች ውስጥ 4 መ/ቤቶች የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢ ድርጅቾች በውሉና በውሉ ላይ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀሙ መሆኑን በመከታተል ድጋፍ የማያደርግ መሆኑን እንዲሁም 8 መ/ቤቶች ደግሞ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ወቅት እንጂ በራሱ ተነሳሽነት ተከታትሎ ድጋፍ እንደማያደርግ ገልጸዋል፡፡

93. ከአገልግሎቱ በተገኘ ማስረጃ መሰረት ለ8 የመንግስት መ/ቤቶች አገልግሎቱ በግዥ ውሉ ላይ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት ግዥው ስለመከናወኑ ባለመከታተሉና ለመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዙሪያ ድጋፍ ባለማድረጉ ከዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ዕቃ ለመግዛት በተመደቡበት አቅራቢ ድርጅት የግዥ ትዕዛዝ በማስተላለፍ 6 መ/ቤቶች ክፍያ ከፈፀሙ በኋላ በተደጋጋሚ በመሄድና በደብዳቤ ለአቅራቢው ቢያሳውቁም እንዲሁም ለአገልግሎቱ ቅሬታ ቢያቀርቡም መ/ቤቶቹ አቅራቢ ድርጅቶች ጋ ዕቃ ለመረከብ ሲሄዱ የዕቃ ክምችት በመጋዘን የሌለ መሆኑን፣ ዕቃው ወደብ ላይ ነው አልገባም ጠብቁ እንደሚባሉና LC ከፍተው ከውጭ እስከሚያስገቡ ጠብቁ የሚል የተለያዩ ምክንያቶችን በማቅረብ ከመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጋር በገቡት ውል መሰረት ሊያቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን አገልግሎት መ/ቤቱም ለእነኝህ መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ ሊያልቅ አንድ ወር እየቀረው እቃው ከውጭ እስኪገባ በመጠበቅ ተከታትለው ግዥ እንዲፈጽሙ በደብዳቤ ከማሳወቅ ውጭ ተከታትሎ ድጋፍ ያልሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

94. የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ድርጅቶች በውሉና በውሉ ላይ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀመ መሆኑን አገልግሎቱ በ2004ዓ.ም ያልተከታተለ ሲሆን በ2005 ዓ.ም መደበኛ በሆነ መልኩ እየተከታተለ አለመሆኑን፤ ሆኖም ግን ከየአቅራቢ ድርጅቶች ግዥ የፈፀሙትን መ/ቤቶች ዝርዝርና ምንያህል እንደገዙ ሁለት ሁለት ጊዜ አቅራቢዎቹ ለአገልግሎቱ የክትትል ሪፖርት ከመላክ ውጭ አገልግሎት መ/ቤቱ የትኞቹ መ/ቤቶች ግዥ እንዳልፈፀሙ፣ የትኞቹ ከተመደበላቸው በላይ እንደገዙ እና ከታዘዘው ምን ያህል እንደሚቀራቸው እንዲሁም በምን ምክንያት እንዳልቀረበላቸው ሪፖርት አለመጠየቁን እና በተጨማሪም ተወዳድረው ካሸነፉ ከሌሎች አቅራቢ ድርጅቶች አንድ ጊዜ ከጥቅምት/2005ዓ.ም ጀምሮ ቢጠይቅም ወጥ በሆነ መልኩ ሪፖርት አለመጠየቁ በአገልግሎት መ/ቤቱ ካለው የአቅራቢ ድርጅቶች የክትትል ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

95. በሰርቬይ መጠይቅ ከተላከላቸው 24 መ/ቤቶች ውስጥ 13 መ/ቤቶች(54%) የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በ2004 እና በ2005 ዓ.ም. ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ውል ከተፈራረመ በኋላ አቅራቢዎች በውሉ መሠረት ያልፈጸሙላቸውና

አገልግሎቱ ተከታትሎ ድጋፍ እንዳላደረገላቸው የገለጹ ሲሆን አቅራቢ ድርጅቶቹ ንብረቱን እንዳላቀረቡላቸው በደብዳቤ አገልግሎቱን ቢጠይቁም ጠብቁ ከማለት ውጭ ምላሽ እንዳልተሰጣቸው ገልፀዋል፡፡

96. ስለሁኔታው የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ም/ዳይሬክተር ተጠይቀው የመንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶችን የተከታተሉበት ሁኔታ እንዳልነበረ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አገልግሎቱ በራሱ ህጋዊ እርምጃ የሚወስድበት አግባብ የሌለው እና በውሉም ላይ የታየ የጐላ የህግ ጥሰት እንዳልነበረ እንዲሁም ክትትሉ በሪፖርት ላይ የተመሠረተ እንደነበረ ገልጸዋል፡፡

97. የመንግሥት ግዥና ንብረተ ማስወገድ አገልግሎት የውል ማስከበሪያው ገንዘብን በ2004 በወቅቱ ያላደሰ፣ በአግባቡም ያልያዘና ያላስተዳደረ መሆኑ እንዲሁም በውሉ መሰረት አለመፈፀሙን በማረጋገጥ ለሁሉም አቅራቢ ድርጅቶች ወጥ በሆነ መልኩ የግዥ ውል ማስከበሪያው ገንዘብ የመውረሻ ሥርዓት እንደሌለው ለማወቅ ተችሏል፡፡

98. በኦዲቱ ወቅት ራዲካል ኃላ/የተ/የግ ድርጅት የውል ማስከበሪያ ገንዘብ በ2004 ዓ.ም. በCPO እንዳስያዙ ነገር ግን CPO ለ6 ወር ብቻ እንደሚያገለግልና ከ6ወር በኋላ መታደስ እንደሚገባው ቢታወቅም አገልግሎቱ ተከታትሎ የውል ማስከበሪያውን እንዲታደስ አለመደረጉና ተመላሽ መሆኑ በአቅራቢው ቢገለፅም የተያዘው የውል ማስከበሪያ ገንዘብ መጠን ትክክል ስለመሆኑ ከአገልግሎቱም ሆነ ከድርጅቱ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ማስረጃው አልቀረበም፡፡

99. አገልግሎቱ ለማዕቀፍ ስምምነት ተፈፃሚነት የውል ማስከበሪያ ገንዘብ ቢይዝም በውሉ መሰረት ስለመፈፀሙ የማይከታተል እና እየወሰደ ያለው እርምጃ በሁሉም ላይ ወጥ በሆነ መልኩ ባለመሆኑ በ2004 ዓ.ም. ማስታወሻ ደብተር፣ የፎቶ ኮፒና የፕሪንተር ወረቀት አቅራቢ ከነበሩት ስናኘና ራዲካል የተባሉ ድርጅቶች የአቅርቦት ችግር እንዳለባቸው በተደጋጋሚ ከተለያዩ መ/ቤቶች አቤቱታና እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለአገልገሎቱ ጥያቄ ቢቀርብለትም የውል ማስከበሪያው ገንዘብ እንዳልተወረሰ ወይም ሌላ እርምጃ ወይም ምክር ያልተሰጣቸው ከመሆኑም በላይ በድጋሚ በ2005 ዓ.ም. ተወዳድረው እያቀረቡ የነበሩ መሆናቸው ታውቋል፡፡

100. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የውል ማስከበሪያ ገንዘብን ስለማስተዳደሩ በተመለከተ ገና ሥራ እንደጀመረ ከልምድ ማነስ ከታዩ ጥቂት ግድፈቶች ውጭ በዚህ ረገድ የተከሰተ ችግር አለመኖሩንና ለተፈጠሩትም ችግሮች ፈጣን ማስተካከያ በወቅቱ እንደተደረገ ገልጸዋል፡፡

101. ይሁን እንጂ የአገልግሎቱ ኃላፊዎች በውሎቹ አስተዳደር ላይ ጥቂት ችግሮች የነበሩና ወዲያውኑ የተስተካከሉ መሆናቸው ይግለጹ እንጂ በኛ አስተያየት የውሎች አስተዳደር፣ ክትትል፣ ቁጥጥር፣ እርምጃ አወሳሰድ ላይ በርካታ ችግሮች የታዩ ስለሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ለ. በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ እና ብቃት ባለው መልኩ በተመጣጣኝ ዋጋ፣ የተፈለገው ጥራት ያለው ዕቃ፣ በሚፈለገው መጠንና በተገቢው ጊዜ መከናወኑን በተመለከተ፤

### አገልግሎቱ የሚፈራረማቸው የግዥ ውሎች የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ /Specification/ የያዙ መሆናቸውን እና በዛ መሰረት ግዥ መፈፀሙን በተመለከተ፤

102. አገልግሎቱ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ/Specification/ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ባለስልጣን ወይም እንደግዢው ዓይነት አግባብ ያላቸው ሌሎች አካላት የሚያወጧቸውን ደረጃዎች በጨረታ ሰነዱ ዝርዝር ውስጥ ለማካተት ጠንካራ የቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ፣ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የተገለፀው የዕቃው ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ ተገቢ ጥንቃቄ፣ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ ዲዛይን፣ አስተሻሸጉን፣ ምልክቱንና ደረጃውን ወይም አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሆኑን የውሉ አንድ ክፍል በማድረግና የአቅርቦቱን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ ሊያውል እና በአቅራቢዎች የሚቀርቡ ዕቃዎች በታወቀ መ/ቤት የናሙና ፍተሻ እንዲደረግላቸውና እንዲረጋገጥ ሊያደርግ እንዲሁም ለመ/ቤቶች የተገዙትን ዕቃዎች በሚፈለገው ስፔስፊኬሽን መሰረት መቅረቡን ሊመረምር ወይም በባለሙያ አስፈላጊው ምርመራ እንዲደረግ ሁኔታዎችን ሊያመቻችና ከምርመራ በኂላም አስፈላጊው የዕቃ ርክክብ እንዲፈፀም ሊያደርግ ይገባል፡፡

103. በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ በ2004ና በ2005 በጀት ዓመት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ /Specification/ በአዘጋጀበት ጊዜ በተሟላ መልኩ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ባለስልጣንን ወይም እንደግዥው ዓይነት አግባብ ያላቸው ሌሎች አካላት የሚያወጧቸውን በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎች ደረጃ በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለዕቃው ደረጃ ዝርዝር አለመገለፁ እንዲሁም በዚህ ዙሪያ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲና አግባብ ካላቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቴክነክ ፍላጎት መግለጫን(specification) በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት እንዳልዘረጋና ተግባራዊ እንዳላደረገ ለመረዳት የተቻለ ሲሆን፤ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለ351 የቢሮ ዕቃዎች ደረጃ እንዲዘጋጅለት በደብዳቤ የደረጃዎች ኤጀንሲን ከጠየቀው ውስጥ በ2005 ዓ.ም መጨረሻ ለ219 ዕቃዎች ደረጃ ተዘጋጅቶ በኮሚቴ ታይቶ መፅደቁ ቢታወቅም ለተቀሩት 132 ዕቃዎች(ለምሳሌ ኮምፒውተርና አክሰሰሪ፣ የፅዳት ዕቃዎች እና የመሳሰሉት) ደረጃዎች ተዘጋጅቶ ያልፀደቀ መሆኑ ታውቋል፡፡ በሌላ በኩል ሲታይ አገልግሎቱ በ2004ና በ2005 ዓ.ም ለዕቃዎቹ (እስክብርቶና እርሳስ፣ የፋይል ማቀፊያና ቶነሮች) ደረጃ ሳይዘጋጅላቸው በጨረታ ሰነዱ ውስጥ አካቷል፡፡ ይህ በመሆኑ በ2004 ዓ.ም. ሆነ በ2005 ዓ.ም.

የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ ብዙ ከተሄደበት በኋላ የዕቃዎቹ ደረጃ ባለመኖሩ የጨረታ ሂደቱ እንዲቋረጥ ከማድረጉም በተጨማሪ በግዥ ሂደቱ ወቅት ደረጃቸውን የልጠበቁ ዕቃዎች (የፋይል ማቀፊያና ከሁለት ዓይነት ቶነሮች በስተቀር ለሌሎቹ) ለመ/ቤቶች እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

104. በዚህ ዙሪያ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በኩል የዕቃዎች ደረጃ በመዘጋጀት ላይ መሆኑን የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡ ይሁንእንጂ በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ የኮምፒውተር እና ተጓዳኝ ዕቃዎች የደረጃ ፍተሻ(test method) ለማድረግ ላብራቶሪ ባለመኖሩ ምክንያት አስቸጋሪ መሆኑን የገለጹና የቶነር ደረጃ ዝግጅትን በተመለከተ በኢትዮጵያ በአብዛኛው የሚሞላ ስለሆነ ይህ ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ስለሌለው ለመነሻ ያህል ሁለት ደረጃዎችን ወስደው እንዳጸደቁና ለወደፊት ወደ ተግባር እንዴት እንደሚገባ ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ጋር መነጋገር እንደሚቀራቸው የደረጃዎች ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

105. በተጨማሪም አገልግሎቱ ከ2004-2005 ዓ.ም ከ9 አቅራቢ ድርጅቶች ጋር በተዋዋለው ውል የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ክፍል ውስጥ ስለዕቃው ጠቀሜታ፣ ተገቢ ጥንቃቄና አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሆኑን እንዳላካተተ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ ከቀረበላቸው 5 የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ውስጥ 3ቱ(60%) አገልግሎቱ በግዥው ውል ላይ የተወሰኑትን የሚጠቅስ ቢሆንም ስለጠቀሜታው፣ ስለ ተገቢው ጥንቃቄና ስለአስተሻሸጉ አለመጠቀሱን ገልጸዋል፡፡ ይህ በመሆኑ ጠቀሜታው ላይ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ፣ ጂኦሎጂካል ሰርቬይና ሜትሮሎጂ የሚባሉ መ/ቤቶች ኮምፒውተር በአገልግሎቱ በኩል ከገዙ በኋላ እኛ የምንፈልገው ይህን አይደለም በማለት በተደጋጋሚ ሰራተኞቻቸው ጥያቄ እንዳነሱባቸው ከአቅራቢ ድርጅቶች መረጃ የተገኘ ሲሆን፤ እንዲሁም ተገቢ ጥንቃቄን በተመለከተ መ/ቤቶች ኮምፒውተሮችን ወስደው በባለሙያ ሲያስፈትሹ በማጓጓዝ ሂደቱ ላይ ብልሽት ቢገጥመው ኃላፊነቱን ማን እንደሚወስድ እና ዕቃዎችን ከማጓጓዝ ውጭ በአቅራቢዎች ወይም በመ/ቤቶች እንደሚሸፈን በስምምነቱ ውስጥ በግልፅ ያልተቀመጠ መሆኑን የመንግስት መ/ቤቶች ገልፀዋል፡፡

106. በሌላም በኩል የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በአቅራቢዎች የሚቀርቡ ዕቃዎች በታወቀ መ/ቤት የቅድመ ናሙና ፍተሻ እንዲደረግላቸውና እንዲረጋገጥ በማድረግ በኢትዮጵያ ተስማሚነትና ምዘና ድርጅት የናሙና ፍተሻ እየተደረገ የሚገኝ ቢሆንም በመንግስት መ/ቤቶች የሚፈለጉ ዕቃዎች በተሟላ ሁኔታ ቅድመ ናሙና ፍተሻ እየተደረገላቸው አለመሆኑ ታውቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት እንደተመለከትነው አገልግሎቱ በ2004ና በ2005 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የዕቃዎች (የእርሳስና የእስክብርቶ፣ ቶነርና የፋይል ማቀፊያ) ናሙና ፍተሻ እንዲያደረግለት ቢጠይቅም በ2004 ዓ.ም የተጠየቀው የእስክብርቶ የናሙና ፍተሻን በተመለከተ በወቅቱ ደረጃው ባለመዘጋጀቱ ምክንያት ፍተሻ አለመደረጉን፤ እንዲሁም የፋይል ማቀፊያን

በተመለከተ የተጠየቀውን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የፍተሻ ዘዴ/ደረጃ/ እንደሌላቸውና ለጊዜው አገልግሎት መስጠት እንደማይችሉ ማሳወቃቸው ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ከ2004-2005 ዓ.ም. በኮምፒውተርና ተጓዳኝ ዕቃዎች በተፈፀመው ግዥ የናሙና ፍተሻ ስለመደረጉ አገልግሎቱ ማስረጃ ተጠይቆ እነዚህ ዕቃዎች ላይ የናሙና ፍተሻ የተደረገበት ማስረጃ እንደሌለ ለመረዳት ተችሏል፡፡

107. በዚህ ዙሪያ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የኮምፒውተር እና ተጓዳኝ ዕቃዎችን ደረጃ /ስፔስፊኬሽን/ ዝግጅትን በተመለከተ ከአገልግሎቱ ጥያቄ ሲያቀርብለት ለሚጠይቁት ጥያቄ መልስ እንደሚሰጧቸውና በዌብ ሳይቱም ላይ የሚለቅ መሆኑን ሆኖም ግን አንዳንድ መ/ቤቶች ከፍተኛ ፍጥነት ያለው /High Processing Speed/ ኮምፒውተር ሊፈልጉ ስለሚችሉ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ስፔስፍኬሽን እንዲዘጋጅለት ሲጠይቅ ለምን ጥቅም እንደሚፈለግ በጥያቄው /need assesement/ ላይ አለመጠቀሱን እንዲሁም በ2005 ዓ.ም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፍተሻ እንዲያደርግለት ተጠይቆ የባለሙያ እጥረት እንዳለው ለአገልግሎቱ ማሳወቁን ገልጿል፡፡

108. የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅትም አቅራቢ ድርጅቶች ለሚያቀርቡት ዕቃዎች የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በጠየቁት መሠረት ዕቃዎችን ከመፈተሽ ውጭ ቅንጅታዊ የሆነ አሰራር ከአገልግሎቱ ጋር እንደለሌው የገለጸ ሲሆን፤ ደረጃ ለወጣላቸው 2 አይነት ቶነሮች የናሙና ፍተሻን በተመለከተ ይህንን ለመፈተሽ 9 ዓይነት ፕሪንተር ስለሚያስፈልግ ድርጅቱ ደግሞ በቂ ፕሪንተር የሌለው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ግን በድርጅቱ የሌሉ የመፈተሻ መሣሪያዎች አገልግሎቱ ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በጋራ በመሆን መፈተሽ የሚቻልበትን ሁኔታ እንዲመቻች አለመደረጉን እንዲሁም አገልግሎቱ የሚያቀርበው የዕቃዎች ቅድመ ናሙና ፍተሻ ላይ ለዕቃዎቹ ኮድ ቢሰጣቸውም የሁሉንም የአቅራቢ ድርጅቶች ስም በዕቃው ላይ በማህተም እንዲገለፅ ማድረጉ የጥቅም ግጭት የሚያስከትል መሆኑንና ዕቃ አቅርቦቱ ከተጀመረ በኋላ በየመሐሉ የማረጋገጥ ስራ ስለማይሰራ ወካይ ስለመሆኑ የሚያጠራጥር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

109. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ከኢትየጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የጠበቀ የሥራ ግንኙነት እንዳላቸው፣ ነገር ግን የኢትዮጵያ ደረጃዎች አጀንሲ የቴክኒክ ፍላጐት ዝርዝር መግለጫ እንዲያዘጋጅላቸው ጠይቀው እንዳማያውቁ፣ ደረጃ ያልተዘጋጀላቸው ተብለው ከተገለጹት እስክሪኝቶ፣ እርሳስ የፋይል ማቀፊያ ቶነሮች ውስጥ የእርሳስ ግዥ የኢትዮጵያን ደረጃ ባለማሟላቱ ግዥው እንዳልተፈጸመ፣ እንዲሁም ደረጃቸውን ያልጠበቁ ዕቃዎች ተገዝተዋል ከተባሉት ዕቃዎች ደረጃውን ያልጠበቃ ዕቃ ግዥ እንዳልተፈፀመ እና እስክሪኝቶ በ2005 ዓ.ም. ለተስማሚነት ምዘና በመላክ ተፈትሾ ውጤቱን በማሳወቁ ግዥው እንደተፈጸመ የገለጹ ሲሆን ለሌሎቹ ዕቃዎች መልስ ያልሰጡና ድርጅቱም ለቶነር ፍተሻ በቂ ፕሪንተር ሊያዘጋጅ እንደሚገባው፣ የኮምፒውተር ግዥ ሲፈጸም የፍላጐት ዝርዝር መግለጫው በመገናኛና ኢንፎርማሽን ኮሙኒኬሽን

ተክኖሎጂ ሚኒስተር ተዘጋጅቶ እንደተሰጠ፣ የኮምፒውተር ጥራት የሚረጋገጠው በናሙና ፍተሻ ሳይሆን በቀረበው የፍላጎት ዝርዝር መግለጫ መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ እንደሆነ፣ የቴክኒክ ግምገማው የሚከናወነው አቅራቢዎች በቀረበው ዝርዝር የፍላጐት መግለጫ መሠረት ማቅረብ መቻላቸው ላይ እንደሆነ በናሙና ፍተሻ ሳይሆን ሁሉንም የሚረከቡትን ኮምፒውተሮ በፍላጐት ዝርዝር መግለጫው መሠረት መሆኑን እያረጋገጡ የሚረከቡት ተጠቃሚ መ/ቤቶች መሆኑን ገልጸዋል፡፡

110. ይሁን እንጂ የተወሰኑ መ/ቤቶች የአይቲ ባለሙያዎች እና በዕቃ ግምገማው ላይ በቂ እውቀት የሌላቸው በመሆኑ እንዲሁም ለኮምፒውተርና ተጓዳኝ ዕቃዎች የናሙና ፈተሻ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ከሚመለከተው አካል የተረጋገጠ ቢሆንም እንኳን በአገልግሎቱ በርክክብ ወቅት ዕቃውን በዝርዝር ፍላጐት መግለጫ ላይ መታየት ስላለበት የናሙና ፍተሻ አያስፈልግም መባሉን በእኛ አስተያየት ተገቢ መልስ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

111. ለመ/ቤቶች የተገዙት ዕቃዎች በሚፈለገው ስፔስፊኬሽን መሰረት መቅረቡን ስለመመርመሩ ወይም ምርመራ እንዲደረግ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ከምርመራ በኂላ አስፈላጊውን የዕቃ ርክክብ ስለመደረጉ ሲታይ፤ አገልግሎቱ ለመ/ቤቶች የተገዙትን ዕቃዎች በሚፈለገው ስፔስፊኬሽን መሰረት መቅረቡን አልመረመረም፡፡ እንዲሁም በባለሙያ አስፈላጊው ምርመራ እንዲደረግ ሁኔታዎችን አላመቻቸም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከምርመራ በኂላ በተሟላ መልኩ አስፈላጊውን የዕቃ ርክክብ እንዲፈፀም አላደረገም፡፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 15 የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ የተገዙትን ዕቃዎች ከመረከባቸው በፊት በሚፈለገው ስፔስፊኬሽን መሰረት መቅረቡን ምርመራ ወይም ከምርመራ በኂላ አስፈላጊው የዕቃ ርክክብ እንዲፈፀም ባለማድረጉ ምክንያት 13ቱ(87%) በራሳቸው ባለሙያ ያስገመገሙ ቢሆንም ሁለት መ/ቤቶች ደግሞ ባለሙያ ስለሌላቸው ማስገምገም ያልቻሉ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ባለሙያ ያላቸውም ሆኑ የሌላቸው 15ቱም የመንግስት መ/ቤቶች በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በጋራ የሚፈለጉ መጠቀሚያ ዕቃዎች ሲገዙ በስፔስፊኬሽኑ መሠረት መሆኑን አስቀድመው በባለሙያ አስፈላጊውን ምርመራ ሳያደርጉ ክፍያ ፈጽመው የሚረከቡ ሲሆን መ/ቤቶቹ ከተረከቡ በኂላ የተበላሹና የማይሠሩ ዕቃዎች የገጠማቸው እና 2 መ/ቤቶች ደግሞ የሰው ኃይል ስለሌላቸው የባለሙያ እጥረት ስላለባቸው የማያስመረምሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

112. በሌላም በኩል በ2005 ዓ.ም. ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ብሪጅቴክ ኃ/የተ/የግ/ማ ከተባለ አቅራቢ ድርጅት 200 ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮችን በብር 2,979,050 (Cache Memory 3MBL2 እና ስፔስፊኬሽን No of free Memory Slot 3) እና ለሁሉም ኮምፒውተሮች Original factory resource 3 DVD እና አንቲቫይረስ የተጫነባቸው ቢልም ከተጠቀሰው ስፔስፊኬሽን ውጪ 3MBL3 እና Slot 1ና የገቡት ኮምፒውተሮች አንቲ ቫይረስ ያልተጫነባቸውና ዲቪዲውም ተካቶ ያልተገዛ

መሆኑን እንዲሁም የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ለራሱ መ/ቤት ከሌዘር ኮምፒውተር ትሬዲንግ ፕሪንተሮች Monthly Duty Cycle Recommended በስፔስፊኬሽኑ መሰረት 100,000ና ከፍተኛ ሚሞሪ 512 ሜጋ ባይት መሆን ሲገባው 20,000 እና 256 ሜጋ ባይት የሆነውን ክፍያ ፈጽመው የተረከቡና ከስፔስፊኬሽን ውጪ የተገዛ መሆኑን አገልግሎቱ ለሌዘር ኮምፒውተር ትሬዲንግ በ19/7/05 ዓ.ም. በቁጥር ግንማ 1/4/136/60/7 በተጻፈ ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

113. በአገልግሎቱ ቀርበው ከታዩ የመንግስት መ/ቤቶች የግል ማህደር ውስጥ 10 መ/ቤቶች በአገልግሎቱ በኩል ግዥ የተፈፀመባቸው ዕቃዎች በስፔስፊኬሽኑ መሠረት መሆኑን በራሳቸው የቴክኒክ ባለሙያ አረጋግጠው ዕቃዎቹን መረከብ እንደሚችሉ ለአቅራቢዎች ቢገልፁም፣ መ/ቤቶች ክፍያ ከመፈፀማቸው በፊት ዕቃዎችን ማስመርመር እንደማይችሉ የተገለፀላቸው በመሆኑና ከአገልግሎት መ/ቤቱ ጋርም በዚህ ዙሪያ ውል እንደሌላቸው አቅራቢ ድርጅቶች የገለፁ ሲሆን እንዲሁም ሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ ባለሙያ እንደሌላቸው የአገልግሎቱን ባለሙያዎች ቢጠይቁም አገልግሎቱ እየተዘዋወሩ የሚያረጋግጡ በቂ ባለሙያዎች እንደሌሉት የገለፀላቸው በመሆኑና ለምርመራ ሁኔታዎችን ባለማመቻቸቱ ምክንያት በጋራ የሚፈለጉ መጠቀሚያ ዕቃዎች በስፔስፊኬሽን መሰረት መሆኑን አስቀድመው አስፈላጊ ምርመራ ሳያደርጉ ክፍያ ፈፅመው ዕቃውን የሚረከቡ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም በመሆኑ በአብዛኛው የመንግስት መ/ቤቶች አቅራቢ ድርጅቶች ጋ በመመላለስ ለተጨማሪ አበል፣ ትራንስፖርትና ፓርኪንግ ወጪ እንደተዳረጉ እንዲሁም በርክክብ ወቅት ዕቃውን አዲስአበባ ድረስ ሄደው ስለሚረከቡ ሊጠፋና ጉዳት ሊደርስበት ይችላል የሚል ስጋት የፈጠረባቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

114. በተጨማሪም 4 መ/ቤቶች ደግሞ ክፍያ ከፈፀሙ በኂላ ዕቃዎቹ ስፔስፍኬሽን የሚያሟላ ሆኖ ባለመገኘታቸው ግዥውን መፈፀም የተቸገሩ መሆኑን፣ ለመረከብም ሆነ የተረከቡትም ለመጠቀም ያልቻሉ መሆኑን እና ሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ደግሞ ውሉ ላይ ከተዋዋለው ስፔስፍኬሽን ውጭ አገልግሎቱ ከሚመለከተው አካል ዕቃው ተቀባይነት እንዳለው ሳያጣራና የናሙና ፍተሻ ሳያስደርግ አቅራቢው ድርጅት መጀመሪያ ከተወዳደረበት እና ለመ/ቤቶች ከተሰጣቸው ስፔስፍኬሽንና ሞዴል ውጭ አምራቹ ኩባንያ ተቀይሯል በማለት በአገልግሎቱ ድጋሚ ስፔስፍኬሽን ለመ/ቤቶች የሚላክ መሆኑ ታውቋል፡፡ይሁን እንጂ ኮምፒውተር ከተረከቡ በኃላ ብልሽት የገጠማቸው መ/ቤቶች መበላሸታቸውን ጠቅሰው መፍትሔ እንዲሰጣቸው ለአገልግሎቱ ቢያሳውቁም አቅራቢ ድርጅቶች ስቶክ ውስጥ የለንም በማለታቸውና ተመላሽ ተደርጎ የተቀየረው ኮምፒውተር ለመውሰድም ሲሄዱ ማውዝ፣ ኪቦርድ እና ሲዲ የሌለው በመሆኑ ተሟልቶ እንዲቀርብላቸው ቢጠይቁም እንኳ የጠየቁትን ዕቃ እንዳልተረከቡና አቅራቢዎች ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እስከ ነሐሴ23/05 ችግሩ እንዳልተፈታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

115. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አገልግሎቱ ስራ የጀመረው ከ3 ዓመታት ወዲህ እንደመሆኑና የመንግስት መ/ቤቶች በኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት በመኖራቸው የዕቃ ርክክብ የሚፈፅሙበት የራሳቸው መንገድ ያላቸው ሲሆን በዚች ሶስት ዓመት ውስጥ ተቀይሮ የዕቃ ርክክብ የሚያስቀር አለመኖሩንና እንዲሁም መ/ቤቶች ግዥ ሲፈፅሙ በቀረበው የዝርዝር ፍላጎት መግለጫ መሰረት መሆኑን እያረጋገጡ እንዲረከቡና ችግር ሲኖር ለአገልግሎቱ እንዲያሳውቁ ሴሪኩላር የተላለፈ መሆኑንና ያለምንም ማረጋገጫ የተረከቡ መ/ቤቶች ካሉም ሊጠየቁ እንደሚገባ እንዲሁም የIT ባለሙያ የሌላቸው መ/ቤቶች ድጋፍ ጠይቀው ድጋፍ እንደተደረገላቸው ሆኖም ግን በ4 መ/ቤቶች የተገዙ ዕቃዎች ስፔስፍኬሽን የማያሟላ መሆኑን በተመለከተ የዕቃውን ርክክብ ሲፈፅሙ በስፔስፊኬሽኑ መሠረት መሆኑን አጣርቶ መረከብ የነሱ ኃላፊነት እንደሆነና ችግር ሲኖር ለአገልግሎቱ ማሳወቅ እንደነበረባቸው ይህን ያደረገ መ/ቤት እንዳልገጠማቸውና የተገዛው ዕቃ እኛ በምንፈልገው ስፔስፊኬሽን አይደለም የሚሉም እንዳሉ አገልግሎቱ መጀመሪያ ከተወዳደረበት እና ለመ/ቤቶች ከተሰጠው ስፔፊከሽንና ሞዴል ውጭ አምራቹ ኩባንያ ተቀይሯል በማለት አገልግሎቱ ድጋሚ ስፔስፊኬሽን ልኳል የተባለው የመረጃ ክፍተት እንደሆነና አገልግሎቱ ጨረታ ካወጣ በኂላ ያደረገው የስፔፊኬሽን ለውጥ እንደሌለና የሞዴል ለውጥ ግን እንደተደረገ እና የዕቃ ርክክብን በተመለከተ ገንዘብ አስቀድሞ የሚከፈልበት ሁኔታ እንደሌለና በውሉ ላይ በግልጽ የተቀመጠው ክፍያ የሚፈጸመው ከርክክብ በኂላ ሲሆን በ2006 ዓ.ም. ግን በውሉ ላይ የዕቃ ርክክብ ከተፈጸመ ከ5 ቀናት በኂላ ክፍያ እንዲፈጸም በውሉ ላይ የተቀመጠ ሲሆን ለሁሉም መ/ቤቶች እንዲያውቁት መደረጉን ገልጸዋል፡፡

116. ይሁን እንጂ መ/ቤቶች ዕቃ እንዲረከቡና አረጋግጠው እንዲወስዱ በተለያየ ቀን ደብዳቤ መተላለፉ ቢታወቅም በግዥና ውል አስተዳደር መመሪያ ላይ አገልግሎቱ ለመ/ቤቶች የተገዙትን ዕቃዎች በሚፈለገው ስፔስፊኬሽን መሰረት መቅረቡን ሊመረምር፣ ወይም በባለሙያ አስፈላጊው ምርመራ እንዲደረግ ሁኔታዎችን ሊያመቻችና ከምርመራ በኂላ አስፈላጊውን የዕቃ ርክክብ እንዲፈፀም ቢገለጽም አገልግሎቱ ይህን ተግባር አለመፈጸሙ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ሞዴሉ ተቀይሯል ለተባለው ኮምፒውተር የስፔስፊኬሽን ልዩነት ብቻ ሳይሆን ዕቃው በፊት በጨረታ ካሸነፈው ጋር የሚተካው /equivalent/ ስለመሆኑ የሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ያልሰጠበት ሲሆን በተጨማሪም የአይቲ ባለሙያ እጥረት ላለባቸውና ድጋፍ ለጠየቁ መ/ቤቶች ድጋፍ እንደሚሰጥ ቢገልጽም የኢትዮጵያ ደረጃዎች አጀንሲ ለአገልግሎቱ ድጋፍ ጠይቆ ባለሙያ እንደሌለው የገለጸና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የገዛውን ኮምፒውተር በተመለከተ ስፔስፊከሽን እንደማያሟላ ለአገልግሎቱ ከተጻፈው ደብዳቤ የተገኘ እና በ2004ም ሆነ በ2005 ዓ.ም. አልግሎቱ የተፈራረመው የግዥ ውል ላይ ከርክክብ በኂላ ክፍያ እንደሚፈጸም ሳይገለጽ ወይም ተከፍሎ እንደሆነ ሳይጣራ ገንዘብ አስቀድሞ የሚከፈልበት ሁኔታ የለም በማለት የተሰጠው መልስ አልተቀበልነውም፡፡

**አገልግሎቱ የሚፈራረመው የግዥ ውል የገበያ ጥናትና**

**መረጃን የተመረኮዘ መሆኑን በተመለከተ፤**

117. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ  አገልግሎት ለመንግስት መ/ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶችና ለክልል መንግስታት በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የግዥ አገልግሎት ሊሰጥ፣ ለማዕቀፍ ስምምነት ግዢ የሚፈራረመውን የውል ዓይነትና ዋጋ በገበያ ጥናት ላይ ተመርኩዞ ሊወስን እና አገልግሎቱ ከግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ወይም ከሌሎች ምንጮች በተገኘ የገበያ መረጃ የዕቃዎች ዋጋ ጥናት መሰረት ለግዥው የተመደበው በጀትና የግዥው መጠን መመጣጠኑን ሊያረጋግጥና ማስተካከያዎችንም ሊያደርግ ይገባል፡፡

118. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አልግሎት ለአብዛኛዎቹ የመንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች የማዕቀፍ ግዥ ውል ስምምነት ከመፈጸም ውጭ በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የግዥ አገልግሎት አለመስጠቱና ከ2004-2005 ዓ.ም ለማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የተፈራረመውን የዕቃዎች ውል ዋጋ በገበያ ጥናት ላይ ተመርኩዞ አለመወሰኑ ታውቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ የማዕቀፍ ግዥ ሲፈፀም የቀረበው ዋጋ መጋነኑንና አለመጋነኑን የሚገልፅ የዋጋ ጥናት ሣይደረግበት ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፣ በአገልግሎቱም የተደራጀ የገበያ ጥናት ቡድን የሌለ መሆኑ እና የመንግስት መ/ቤቶች (ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ጅማና አዲስ አበባ  ዩኒቨርስቲዎች) ዕቃዎችን  በዝቅተኛ ወይም በተሻለ ዋጋ ቢያገኙም እንኳ የገበያ ጥናት ባለመጠናቱ ምክንያት አገልግሎቱ ግዥ እንዳይፈፅሙ  የኤጀንሲውን ፍቃድ መጠየቅ እንዳለባቸው እንደሚያዝና ኤጀንሲውም  የከለከላቸው መሆኑ ከአገልግሎቱ በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

119. ከዚህም በተጨማሪ የዋጋ ጥናት ተሰርቶ ባለመቅረቡ ለአቅራቢዎች የዋጋ ማስተካከያ በወቅቱ እንዳይሰራና ዕቃ አቅርቦት ላይ ችግር የፈጠረ መሆኑ ከአገልግሎቱ በተገኘው ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

120. ይህም በመሆኑ አገልግሎቱ የዕቃዎች  የገበያ መረጃ ስለሌለውና ወጥ በሆነ መንገድ በየበጀት ዓመቱ የመ/ቤቶችን በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ገንዘብ  በጀት የሚመለከተውን አካል ስለማይጠይቅ እስከ 2005 ዓ.ም ለግዥው የተመደበው በጀትና የግዥ መጠን መመጣጠኑን በማረጋገጥ ማስተካከያዎችን አላደረገም፡፡

121. ከዚህ ጋር በተያያዘ አገልግሎቱ  ለኤጀንሲው የኘሪንተር ወረቀትና የፎቶኮፒ ወረቀት ኤ4 እና ኤ3 የወቅቱ የገበያ ዋጋ እንዲልኩላቸው ለኤጀንሲው በደብዳቤ ልከው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ የሚወጣው በማዕከላዊ ስታትስቲክስ በኩል እንደሆነና የማዕከላዊ ስታስትቲክስና የራሱን የኤጀንሲውን ዌብ ሳይት በመጠቀም የዋጋ ዝርዝር የሚለው ላይ ማየት እንዳለባቸው ኤጀንሲው ገልጿል፡፡ በዚሁ መሰረት አገልግሎቱ ለማዕከላዊ ስታትስቲክስ የ5 ዓይነት ኘሪንተርና የ2 ዓይነት ፎቶ ኮፒ ቶነሮች እንዲሁም

የዴል ኦፕቲክስ 790 እና 7010 ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮች ዋጋ እንዲልኩላቸው ቢጠይቁም የኮምፒውተሩም ሆነ የቶናሩን ዋጋ እንደሌላቸው የገለጹ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

122. በዚህ ዙሪያ የመግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ቁጥር በርካታ እንደሆነና በሀገሪቱ የተለያዩ ከተሞች ያላቸውም ዋጋም እንደሚለያይ ስለዚህ በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ በኤጀንሲያቸው በኩል በየጊዜው ለማጥናት የሚያስቸግር በመሆኑም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በኩል በየ3 ወሩ እየተጠና እንዲቀርብ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ መመሪያ የተላለፈ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት በተለይ ለመንግሥት ግዥ በሚል የማዕከላዊ ስታትስቲክስ በየ3 ወሩ የሚያጠናው ጠቋሚ የገበያ ዋጋ በኤጀንሲያቸው ድረ-ገጽ ላይ እንዲጫን ስለተደረገ አገልግሎቱ ከዛ ማየት እንደሚችል ነገር ግን ኤጀንሲው ይህን ቢያደርግም አገልግሎት መ/ቤቱ ሥራው ስለሆነ የጨረታ ውድድር በሚያካሂድበት ጊዜ በአሸናፊነት የሚመረጠው አቅራቢ የሰጠው ዋጋ ተቀራራቢ መጠን ያለው ስለመሆኑ የበኩሉን የገበያ ሁኔታ በዳሰሳ ጥናት ማየት እንዳለበት የገለጹ ቢሆንም የአገልግሎቱ የግዥ ሠራተኞችም ሆኑ የኦዲት ቡድኑ የሁለቱም መ/ቤት ድረ-ገጽ ላይ አለመኖሩን ያረጋገጠ ሲሆን፤ የማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ ኃላፊ በበኩላቸው የገበያ ጥናት ክፍሉ በየወቅቱ የተጠናውን መረጃ ለመ/ቤቱ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት እንደሚያስተላልፍ ነገር ግን ዳይሬክቶሬቱ ለምን እንዳላወጣ መጠየቅ እንዳለበት ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠንቷል የተባለው የገበያ ጥናት ያልተሟላና የአንድ ወር ጥናት/የሰኔ ወር 2004 ዓ.ም. ብቻ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

123. የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በገበያ መረጃ የዕቃዎች ዋጋ ጥናት መሰረት ለግዥው የተመደበው በጀትና የግዥው መጠን መመጣጠኑን አረጋግጦ ማስተካከያዎችን ማድረጉንም በተመለከተ እንደማይሰራና አገልግሎቱም የመንግስት መ/ቤቶችን በጀት የማይጠይቅ መሆኑን፤ የግዥ ሂደቱንም የሚያካሄደው በመንግስት መ/ቤቶች በጀት ሲሆን የመ/ቤቶች በጀት ስንት እንደሆነ እንደማያውቅና ከመ/ቤቶች የዕቃ ፍላጎት ጥያቄ በመነሳት ጨረታ የሚወጣ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

124. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሠረተ የግዥ አገልግሎትን በተመለከተ ወቅታዊ የገበያ መረጃ የመያዝ ኃላፊነት ያለው ማዕከላዊ ስታስትክስ ኤጀንሲ ሲሆን በየጊዜው የሚያወጣውን የገበያ መረጃ እየተጠቀሙ እንደሚገኙና በአገልግሎቱ ወቅታዊ የገበያ መረጃ የሚይዝ ክፍል ተደራጅቶ ሥራ እንደጀመረ ወደፊት የሁለቱንም የገበያ መረጃ እንደሚጠቀሙ እና መ/ቤቶች ለግዥ የተመደበውን በጀትና የግዥ መጠን መመጣጠኑን በተመለከተ በጀት የሚመደበው በየዓመቱ ይገኛል ተብለው በሚጠበቀው የአገር ውስጥ ገቢና የውጭ አገር ብድርና ዕርዳታ ግምት ተወስዶ በጀት እንደሚበጀትና ከዕቃ ዋጋ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ገልጸዋል፡፡

125. ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለጸው በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ ግዥ የፈጸመባቸው የዴል ኦፕቲክስ 790 እና 7010 ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮች እና የፕሪንተርና ፎቶ ኮፒ ቶነሮች ዋጋ ለማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ ጠይቆ ኤጀንሲው የሁለቱም ዋጋ እንደሌለው ሁለቱ መ/ቤቶች በተጻጻፉት ደብዳቤ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የኦዲት ቡድኑ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲን ዌብ ሳይት ላይ በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችን ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናቱን ያላገኘ መሆኑና የማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ ኃላፊው የገበያ ጥናቱን ለኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ቢያስተላልፉም ዳይሬክቶሬቱ እንዳላወጣው ያረጋገጡለት ስለሆነ አገልግሎቱ በወቅታዊ የገበያ ዋጋ ላይ ተመስርቶ ግዥ አለመፈጸሙ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## አገልግሎቱ በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለማስረከቢያ ቦታ፣ ጊዜ እንዲሁም የዋጋ ማስተካከያ ስለሚደረግበት ሁኔታ ያካተተ መሆኑን በተመለከተ፤

126. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ውል ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከ3ወር በኋላ ለሚኖር ግዢ የዋጋ ለውጥ ወይም ማስተካከያ ማድረግ እንደሚቻል በጨረታ ሰነዱ ላይ በማመላከት ማስተካከያ ሊያደረግ እንዲሁም ሰነዱ ላይ በማዕቀፍ ስምምነት የሚገዛውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚጠቀሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዝርዝር፣ የማስረከቢያ ቦታ፣ ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜና መጠን፣ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ሁኔታ፣ አፈፃፀሙንና የግዥው ውል ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲካተት ሊያደርግ ይገባል፡፡

127. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ውል ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከ3ወር በኋላ ለሚኖር ግዢ የዋጋ ለውጥ ወይም ማስተካከያ ማድረግ እንደሚቻል በጨረታ ሰነዱ ላይ ቢያመላክትም የዕቃዎች የዋጋ ጥናት ባለመዘጋጀቱ ዋጋ ሲጨምር እና ሲቀንስ ለዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችም ሆነ ለመንግስት መ/ቤቶች የዋጋ ለውጥ አለማድረጉ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ መ/ቤቶች ለ2005 በጀት ዓመት ግዥ ፍላጎታቸውን ባሳወቁት የፎቶ ኮፒ ወረቀት ላይ ጁፒተር የተባለ አቅራቢ ድርጅት የወረቀት ዋጋ ጨምሯል ዋጋ ከልሰን እስከምናዘጋጅ በቀድሞው ዋጋ አናስተናግዳችሁም በማለት ማቅረብ እንደማይችል በመግለፁ ምክንያት እስከ ነሐሴ 28/12/05 መፍትሄ አለማግኘታቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

128. በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ በ2004 እና በ2005 ባወጣው የጨረታ ሰነድ ላይ የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝርና ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ ያላካተተ መሆኑን ለመረዳት የተቻለ ሲሆን፤ ከ2004-2005 ዓ.ም የተፈራረመው የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውል ላይ በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችን የሚገዙ የመንግስት መ/ቤቶችን ስም ዝርዝር ባለማካተቱ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ 5 አቅራቢዎች ውስጥ 3ቱ ድርጅታቸው የጠበቀውን ወይም ያቀደውን ተረካቢ መ/ቤት ሳይሆን አንድ መ/ቤት ብቻ መጥቶ ዕቃውን ሊረከብ ስለሚችል ዕቅዳቸው ላይ ችግር እንደፈጠረባቸውና ፍላጎት ያላሳወቁ መ/ቤቶች ዕቃ

የሚረከቡ መሆኑ ይህ ደግሞ አቅርቦት ላይ ችግር እንዳስከተለባቸውና በቀጥታ መ/ቤቶች ጋር ሄደው ተረከቡ ለማለትም ሆነ ለማስገደድ እንዳላስቻላቸው፣ ከዚህም በተጨማሪ የድርጅታቸውን የአቅርቦት ዕቅድ እንዳያስተካክሉ ማድረጉን ገልፀዋል፡፡

129. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲም ሆነ ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ የገበያ መረጃ ባለማግኘቱ ምክንያት ከነዚህ መ/ቤቶች የተፈለገ የገበያ ዋጋ   መረጃ ስላልተገኘ የዋጋ ማስተካከያ እንዳልተደረገ የገለጹ ሲሆን፤ ጁፒተር የተባለውም አቅራቢ ድርጅት የዋጋ ማስተካከያ ቢጠይቅም እንኳ በገበያ ዋጋ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑ እንዲሁም ጁፒተር ኃ/የተ/የግ/ድርጅት ለጅማ ዩኒቨርስቲ የዕቃ አቅርቦት ስለማቋረጡ የደረሳቸው መረጃ እንደሌለ የገለጹ ቢሆንም የጨረታ ሰነድ ላይ የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝርና ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ ያላካተተ ስለመሆኑ ግን ምላሽ አልተሰጠም፡፡

130. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ስናፕ ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ ማህበር፣ ሌዘር ኮምፒውተር ትሬዲንግ፣ ከብሪጅቴክና ራዲካል ኃላ/የተ/የግ ማስተካከያ እንዲደረግላቸው  በአካልና በደብዳቤ ለአገልግሎቱ ጠይቀው፣ አገልግሎቱ ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ጋር የዋጋ ጥናት ሰርተው እንደሚያስተካክሉላቸው ነግሯቸው የነበረ ቢሆንም ተፈፃሚ እንዳልሆነና ዕቃዎች ላይ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ዕቃዎችን በተፈለገው መጠን እና ጊዜ ማቅረብ እንዳልቻሉ የገለጹ ሲሆን በዋጋ መጨመሩ የተነሳ በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ ሊያጋጥም የሚችለው ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት አገልግሎቱ ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ጋር በመነጋገር በ2004 ዓ.ም. እና በ2005 ዓ.ም. የዋጋ ማስተካከያውን አለማድረጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## አገልግሎቱ ጥራታቸውን የጠበቁ ዕቃዎች በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛቱን እና ጥቅል ግዥ በመፈፀም ኢኮኖሚያዊ  ጥቅም ማስገኘቱን በተመለከተ፤

131. አገልግሎቱ ለመንግሥት መ/ቤቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ሊገዛ እንዲሁም ለመንግስት መ/ቤቶች  በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች ተመሳሳይ ጥቅል ግዥ በመፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያስገኝ እና  ያስገኘው የኢኮኖሚ ጥቅም ሊታወቅ ይገባል፡፡

132. በኦዲቱ ወቅት ከ2004-2005 ዓ.ም አገልግሎቱ በፈፀመው የግዥ ውል  መሰረት በመንግስት መ/ቤቶች  የተገዙ ዕቃዎች ጥራትን በተመለከተ በናሙና ከታዩት 15 መ/ቤቶች ውስጥ 10ሩና በሰርቬይ መጠይቅ ተልኮላቸው ከመለሱት መ/ቤቶች ውስጥ 4 መ/ቤቶች  የጥራት  ችግር የገጠማቸው ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ 6 መ/ቤቶች የፎቶ ኮፒና የፕሪንተር ወረቀቶች፣ ቶነሮች፣ ፕሪንተሮችና የፋይል አቃፊ ከአቅራቢዎች የገዙት ዕቃዎች ጥራቱ ዝቅ ያለ በመሆኑ መ/ቤቶቹ ለሚጠቀሙበት  የፎቶ ኮፒ ማሽን ተስማሚ ያልሆነና ጥራቱን ያልጠበቀ  ወረቀት እንዲያገኙ ያደረገ መሆኑና የሳሳ ስለሆነ ፎቶ ኮፒ ሲያደርጉ እና ጽሑፎች በሚታተሙበት ጊዜ ስለሚጨማደድ በጣም

እየተቸገሩ ከመሆኑም በላይ በርካታ ወረቀቶች ተበላሽቶባቸው ለብክነት የተጋለጡ መሆኑን እንዲሁም በአገልግሎቱ የተገዙ ቶነሮች ኦሪጅናል ሳይሆኑ ሪፍል /በድጋሚ የተሞሉ/ ስለሆነ ማሽኖች በየጊዜው እየተበላሹ ለጥገና ከፍተኛ ወጪ እንዲወጣ ማድረጉን በተጨማሪም የፋይል አቃፊን በተመለከተ ሰነዶችን በመያዝ ለማቆየት የማይችል፣ በቀላሉ የሚቀደድና ለመገንጠልም የተጋለጠ ሲሆን ፕሪንተሮቹንም ያለአገልግሎት እንደቆሙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

133. እንዲሁም ተመጣጣኝ ዋጋን በተመለከተ ከሌሎች ስድስት መ/ቤቶች አገልግሎቱ ለመንግሥት መ/ቤቶች ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዳላቀረበ ከሰጡት መረጃ እና ከተገኘው ማስረጃ ታውቋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 3 የመንግስት መ/ቤቶች አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 200፣ ፍትህ ሚኒስቴር 60 እና ጅማ ዩኒቨርስቲ 100 በጠቅላላ 360 አገልግሎቱ ከገዛው ጋር ተመሣሣይ ዴስክ ቶፒ ኮምፒውተር በመግዛት ከአገልግሎቱ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በብልጫ ብር 1,989,034 የከፈሉ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ የመንግስት መ/ቤቶች ማግኘት የሚችሉትን ጥቅም እያስገኘላቸው እንዳልሆነ ታውቋል፡፡

134. በተጨማሪም የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጥቅል ግዥ በመፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማስገኘቱ ሲታይ፤ የመንግስት መ/ቤቶች ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ በአገልግሎቱ በኩል ግዥ እንዲፈፅሙ ቢደረግም አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች ተመሳሳይ በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች ጥቅል ግዢ በመፈፀም ያስገኘው የኢኮኖሚያዊ ጥቅም በአገልግሎቱ ተሰርቶ የማይታወቅ መሆኑን ከአገልግሎቱ በተገኘ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

135. በዚሁ መሰረት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በ2004 በጀት ዓመት በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉትን ዕቃዎች ለይቶ ለሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች በወቅቱ የግዥ ፍላጎት ባለመጠየቁና ባለማሰባሰቡ፣ የጨረታ ሂደት ጨርሶ ባለማሳወቁ እና የግዥ ሂደት ማካሄድ የማይችለውን ቀድሞ ባለማሳወቁ እንዲሁም በ2005 በጀት ዓመት ፍላጎት የጠየቀበትን ሁሉንም ግዥ አንድ ላይ ባለማከናወኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት 11 መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎች ጥቅል ግዢ በመፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አለማስገኘቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚሁ ምክንያት መ/ቤቶቹ በተለያየ ጊዜ በ2004ና በ2005 በጀት ዓመት የተለያየ ዋጋን በመጠቀም በውስን ጨረታ፣ በግልፅ ጨረታና በፕሮፎርማ ወይም በቀጥቀጥ ዜደዎች ግዥዎችን ፈፅመዋል፡፡ ይህም በመሆኑ በአጠቃላይ 9 የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ አላቂ የፅህፈት፣ የፅዳትና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎችን 121,642,598.47 ብር አውጥተው ግዥ የፈፀሙ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ በናሙና ከታዩ መ/ቤቶች በግላቸው ግዢ በመፈፀማቸው ለማስታወቂያ የተከፈለ ብር 225,225.79 እንዲሁም አገልግሎት መ/ቤቱ ጨረታ ካወጣባቸው አላቂ የፅህፈትና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች ዋጋ የመንግስት መ/ቤቶች ከተገዙት ዕቃዎች ዋጋ ጋር ሲነጻጸር በልዩነት በብልጫ ብር158,704.68 ያለው መሆኑ ታውቋል፡፡

136. በእኛ አስተያየት ከ9 መ/ቤቶች ብር 121,642,598.47 ለቋሚ ዕቃዎች ግዥ በወቅቱ አለመግዛቱ እንዲሁም አላቂና የፅዳት ዕቃዎች ግዥ ባለመፈጸሙ ለመፈፀም የወጣ ከሆነ ከ173 የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎት ግዥዎች  የታጣውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለመገመት አያዳግትም፡፡

137. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ መ/ቤቶች አገልግሎቱ ከገዛው ዕቃዎች ዋጋ ባነሰ ዋጋ ስለማግኘታቸው እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ስለማስጠበቁ በተመለከተ አገልግሎቱ የሚገዛው ግዥ ጥቅል ግዥ በመሆኑ በውድድሩ የሚሳተፉት ዕቃውን በቀጥታ ከውጭ የሚያስመጡ አስመጪዎች  እንደሆኑና ዕቃውን በብዛት ስለሚያስገቡ ዋጋቸው ቅናሽ እንደሆነና የዕቃዎች ዋጋ ገበያ ላይ ካለው ዋጋ በላይ ለመ/ቤቶች እያቀረበ ነው የተባለውም ትክክለኛ መረጃ እንዳልሆነና የሚለያየው በዕቃው ጥራት እንደሆነና የዕቃው ጥራት የሚለካው በዕቃው ስፔስፊኬሽን እንደሆነ፣ አገልግሎቱ የሚገዛቸው ኮምፒውተሮች ሶፍትዌር ጀንዊን እንደሆነ የአንድ ሶፍትዌር ዋጋ 3900 ብር እንደሆነና የዕቃዎች ዋጋ የሚለካው በስፔስፊኬሽን እንደመሆኑ የተለያየ ስፔስፊኬሽን ያላቸውን ዕቃዎች ማወዳደር ተገቢ እንዳልሆነ እንዲሁም ወረቀትና እና እስክሪብቶ ገበያ ላይ ከብር90-100፣ እንዲሁም እስክሪፕቶ ከብር 3.18-3.65 ሲሸጥ አገልግሎቱ በተከታታይ ብር 69 እና 2.45 መግዛቱን፣ ጥራት የሌላቸው ዕቃዎች በአቅራቢዎች ስለመቅረባቸው በተመለከተ ወረቀትንና አቃፊ ፋይልን በተመለከተ አገልግሎቱ የደረሰው ሪፖርት እንደሌለ በርክክብ ወቅት ችግር ካጋጠመ እንዲያሳውቁ የአሽናፊዎች ማሳወቂያ ደብዳቤ ላይ እንደተገለጸ ግዥው ሲፈጸምም የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ማላታቸው በተስማሚነት ምዘና እንደተረጋገጠና ቀጥታ ከውጭ ከሚያመጡ አቅራቢዎች ግዥው እንደተፈጸመ ቶነርም ቢሆን ናኖዳስ የተባለው አቅራቲ ሪፊል የሚያደርግ ሳይሆን አገር በቀል የቶነር መገጣጠሚያ ያለው ድርጅት እንደሆነ  ገልጸዋል፡፡

138. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአገልግሎቱ ከተገዙ ዕቃዎች የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ኤጀንሲና የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ወረቀቶች፣ የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዮት የፋይል አቃፊ ጥራታቸውን ያልጠበቁ በአቅራቢዎች እንደቀረቡላቸው በደብዳቤ ለአገልግሎቱ እንዳሳወቁ ከአገለግሎቱ በተገኘ መረጃ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ በቃለ መጠይቅ በስልክ ለአገልግሎቱ እንዳሳወቁ እንዲሁም ዋጋን በተመለከተ በ2005 ዓ.ም.  አገልግሎቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አሸንፎ ከነበረው ተመሳሳይ ስፔስፊኬሽን ያላቸው  የፎቶ ኮፒ ቶነር 2016 ከቫት በፊት ብር 370፣ ማስታወሻ ደብተር መካከለኛ 13.86፣ ቦክስ ፋይል ባለብረት 27.14፣ ዩፒኤስ 2,587.5፣ የፎቶ ኮፒ ማሽን 39,100.00 ገበያ  ላይ ካለው ዋጋ በላይ ፎቶ ኮፒ ቶነር 2016  በብር 796.94፣ ማስታወሻ ደብተር መካከለኛ በብር14.51፣ ቦክስ ፋይል ባለብረት በብር 29.00፣ ዴስክ ቶኘ ኮምፒውተር በብር 14,895.25 ዩፒኤስ 5002.5፣ የፎቶ ኮፒ ማሽን በብር 51,626.96 ከአቅራቢዎች ጋር ውል መዋዋሉን በተመሳሳይ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ማዕድን ሚኒስቴር፣ ፍትህ ሚኒስቴር ዴስክ ቶኘ

ኮምፒውተር ከአገልግሎቱ ባነሰ ዋጋ  አግኝተው የነበረና ይህንንም ለአገልግልሎቱ ማሳወቃቸው ከአገልግሎቱ በተገኘ መረጃ  በኦዲቱ ወቅት የታየና አገልግሎቱም ከመ/ቤቶች ጋር የተፃፃፈባቸው ደብዳቤዎች እያሉ የደረሰን ሪፖርት  የለም መባሉ አግባብ አይደለም፡፡

**ሐ. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥን በተመለከተ በደንቡ መሰረት የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የመረጃ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤**

**አገልግሎቱ ከሌሎች አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓት**

**ስለመዘርጋቱ እና ግንዛቤ መፍጠሩን በተመለከተ፤**

139. አገልግሎቱ የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም በወቅቱ የመንግስት ባለ በጀት መ/ቤቶች የግዥ ውሉን ኮፒ በመላክ እንዲያውቁት ሊያደርግ፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ ከመንግስት መ/ቤቶችና ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖረው እና  በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች  የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ሊፈጥር ይገባል፡፡

140. በደንብ ቁጥር 184/2002 እና  በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ  መሰረት አገልግሎቱ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ መረጃ መረብ ላይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በማጠናቀር ለህዝብ ይፋ ያላደረገ መሆኑና ለማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ ባለበጀት መ/ቤቶች የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም በወቅቱ እንዲያውቁት ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በአካል ከተሄደባቸው 16 የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ  ለ11ዱ(69%) አገልግሎቱ ለ2004ና 2005 በጀት ዓመት ግዥ ውሉ ከተፈራረመ በኂላ ከ1 ሳምንት እስከ 6ወር በመዘግየት  የአሸናፊ ተጫራቶች ስም፤ አድራሻ፣ የዕቃው ዓይነትና ዋጋ በደብዳቤ ከማሳወቅ ውጪ የግዥ ውል ኮፒ  ለመ/ቤቶቹ በመላክ እንዲያውቁት አላደረገም፡፡ ይህም በመሆኑ ከግዥው አንፃር የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችንና የመ/ቤታቸውን መብትና ግዴታ ለማወቅ እንዳላስቻላቸው፣ የግዥ ሂደቱ ላይ መጓተት ያስከተለ መሆኑና የውሉን ይዘት ባለማወቅ ለአቅራቢ ድርጅቶች ቅድመ ክፍያ መፈፀማቸውን የመ/ቤቶቹ የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

141. ከአገልግሎት መ/ቤቱ ከተገኘው 46 የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ የግል ማህደር እንደታየው ለ44ቱ(96%) በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ውስጥ የግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም የጨረታ አሸናፊ ድርጅቶችን ስም፣ አድራሻና የዕቃዎቹን ዋጋ

በደብዳቤ የ2004ን ውሉ ከተፈፀመ ከ10 ቀን እስከ 2 ወር እና የ2005ን እስከ 5 ወር ድረስ አዘግይቶ ያሳወቀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

142. ከዚህ በተጨማሪም አገልግሎቱ የግዥ ዕቅዶች፣ ሪፖርቶች፣ መመሪያዎችንና የግዥ መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚረዳ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ሲስተም ስርዓት ለመዘርጋት ቢያቅድም እስከ 2005 ዓ.ም ተግባራዊ በማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ ለመንግስት መ/ቤቶችና ለአቅራቢ ድርጅቶች በወቅቱ መረጃዎች እንዲደርሱ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

143. በዚህ ዙሪያ ከተጠየቁት 12 መ/ቤቶች 12ቱም እና የሰርቨይ መጠይቅ ተልኮላቸው ከመለሱት 24 መ/ቤቶች ውስጥ 13ቱ የሚፈልጉትን የግዥ መረጃዎች በሚፈለገው ጊዜና በተቀላጠፈ ሁኔታ በወቅቱ ያላገኙ መሆኑን የገለጹ ሲሆን፤ ይህም በመሆኑ በትክክል አገልግሎቱ የሚሰጠውን አገልግሎት ለማወቅ እንዳልቻሉ፣ ከአገልግሎቱ ጋር ቀልጣፋ አሰራርና ግንኙነት እንዳይኖር ከማድረጉም በተጨማሪ ስራዎችን ተናበው እንዳይሰሩ፣ የግዥ መረጃዎችን በወቅቱ ለማግኘት እንዳይችሉ፣ የግዥ ጨረታ ሂደቱንና የዕቃዎችን ዋጋ እንዳያውቁ እና ግልጸኝነት እንዳይኖር አድርጓል፡፡ ከዚህም የተነሳ ከመ/ቤቶች የሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ረዥም ጊዜ የሚወስዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

144. እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ከ 5 ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች በተገኘው መረጃ መሰረት አገልግሎቱ ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የግዥ መረጃዎች ለድርጅቶቻቸው እንዲደርሱ እንደማያደርግ ነገር ግን በደብዳቤና በስልክ አልፎ አልፎ የተለያዩ መረጃዎችን እንደሚለዋወጡ ገልፀዋል፡፡ ይህም አቅራቢ ድርጅቶች የግዥ መረጃዎችን በወቅቱና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማግኘት እንዳላስቻላቸውና አስቀድሞ የአገልግሎቱን የግዥ እቅድ እንዳያውቁ ማድረጉ ይህ ደግሞ የራሳቸውን ዕቅድ ለማሻሻልና የፋይናንስ ዝግጅት ለማድረግ እንዳልረዳቸው እንዲሁም መ/ቤቶችም ሆኑ አቅራቢ ድርጅቶች መብታቸውንና ግዴታቸው እንዲያውቁ ከማድረጉም በተጨማሪ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት እንዳላስቻላቸውና ብዙ ተወዳዳሪዎች እንዳይኖሩ ማድረጉን ገልፀዋል፡፡

145. በሌላም በኩል አገልግሎቱ የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት በመገናኛ ብዙሃን፣ በስብሰባ፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፕ፣ በደብዳቤና በመወያያ መድረኮች ወዘተ ግንዛቤ እንዳልፈጠረላቸው ታውቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ከታዩ 16 የመንግስት መ/ቤቶችና ሁለት የልማት ድርጅቶች ውስጥ 9 መ/ቤቶች **(56%)** አገልግሎቱ የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ዙሪያ በመገናኛ ብዙሃን፣ በስብሰባ፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፕ፣ በደብዳቤና በመወያያ

መድረኮች ወዘተ ግንዛቤ እንዳልፈጠረላቸው ሲገልጹ 4 መ/ቤቶች(19%) ደግሞ የግንዛቤ መፍጠሩ ስራ በቂ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሲቋቋም ለውይይት ተጠርተው እንደነበረ ሆኖም ግን ግንዛቤ ማስጨበጫ ስጡን ብለው ቢጠይቁም ፕሮግራሙ ለፌደራል መ/ቤቶች ስለሆነ አቅማችንን አጎልብተን ለወደፊት እንሰጣችኋለን በማለት እንዳልሰጡአቸው የኮርፖሬሽኑ የስራ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ ወቅት ገልፀዋል፡፡

146. በተጨማሪም ከተከለሱ ማስረጃዎች 3 መ/ቤቶች /የፌዴራል ፖሊስ፣ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዮት፣ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽህፈት ቤት/በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች ግዥን በተመለከተ ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ ለአገልግሎቱ ደብዳቤ መላክ ሲገባቸው ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የላኩ መሆኑና አብዛኞቹ መ/ቤቶች በ2004 ዓ.ም. በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ ከሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎች ውጭ የሆኑ በማያያዝ ፍላጎታቸውን የላኩ መሆኑን ከተገኘው ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

147. ከዚህም የተነሳ የመንግስት መ/ቤቶች ስለአገልግሎቱ ደንብ ምንነት በግልፅ እንዳያውቁ ያደረጋቸው መሆኑን፣ ከዚህም በተጨማሪ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት እና የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ኃላፊነትና ልዩነት ግልፅ እንዳልሆነላቸው፣ የአገልግሎት መ/ቤቱን፣ የአቅራቢ ድርጅቶችና የመንግስት መ/ቤቶች ኃላፊነት በግዥ ላይ እስከምን ድረስ እንደሆነ እንዳያውቁ፣ የግዥ በጀትን በአግባቡ እንዳይጠቀሙበት ማድረጉንና ከዚህም የተነሳ በግዥው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ መፍጠሩንና በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች ዝርዝርና አገልግሎቶች ለመለየትና ግዥ አፈጻጸማቸውን እንዳያውቁ ያደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

148. ስለጉዳዩ የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በ2004ና 2005 በጀት ዓመት የግዥ ውል ለተጠቃሚ መ/ቤቶች እንዳልተላኩ ነገር ግን የማዕቀፍ ስምምነት እንደተፈረመ ወዲያውኑ መ/ቤቶች እንዲያውቁት መደረጉና የዕቃዎቹ ስፔስፍኬሽን መላኩን ይሁን እንጂ ከ5ወር በኃላ ተልኳል የተባለውን መረጃው እንደሌለ በ2006 ዓ.ም ግን ለመንግስት መ/ቤቶች የሰጡ መሆኑን፤ እንዲሁም አገልግሎቱ በቅርብ ስራ እንደመጀመሩ የግዥ መረጃዎችን ለመለዋወጥ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም ዘርግቶ ተደራሽ አለማድረግ እንደችግር ሊታይ እና አገልግሎቱን መውቀስ ተገቢ እንዳልሆነ የገለፁ ሲሆን፤በተጨማሪም የግንዛቤ ማስጨበጫ ለተጠቃሚ መ/ቤቶችና ለአቅራቢዎች እንደተሰጠ እና በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን፣በፋና ኤፍ ኤም መግለጫ እንደተሰጠበተመሳሳይ ሁኔታ በአገልግሎቱ በሚዘጋጀው መፅሔም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መሰራታቸውን ገልፀዋል፡፡

149. ይሁን እንጂ አገልግሎቱ ሃምሌ 2002 በደንብ ቁጥር 184/2002 የተቋቋመ ቢሆንም ከመ/ቤቱ ዓላማ፣ ኃላፊነትና ተግባር አንፃር በአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች የግዥ መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚያስችል

የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም ዘርግቶ ተደራሽ አለማድረግ እንደችግር አለመታየቱና የኦዲቱም አላማ መልካም ተሞክሮ ለማሳወቅ እንጂ አገልግሎቱን ለመውቀስ መባሉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## አገልግሎቱ የምክርና ስልጠና አገልግሎት ስለመስጠቱና እና የመወያያ መድረኮችን ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤

150. አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ለክልል መንግስታትና ለግሉ ዘርፍ የግዥ አፈፃፀምን የሚመለከት የምክርና ሥልጠና አገልግሎት ሊሰጥ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በማዕቀፍ ስምምነት የግዢ ሂደት ላይ በአቅራቢ ድርጅቶችና በዕቃ ተረካቢ መ/ቤቶች መካከል የሚፈጠሩትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል መደበኛ የሆነ የመወያያ  መድረኮችን (ወርክሾፖችና ሴሚናሮች ወዘተ) በማዘጋጀት ተቀናጅቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

151. በኦዲቱ ወቅት በአካል የተሄደባቸው 15 መ/ቤቶች እና የሰርቨይ መጠይቅ ከተላከላቸው 24 መ/ቤቶች ውስጥ ለ13ቱ /54%/ ከ2003-2005 ዓ.ም አገልግሎት መ/ቤቱ  የግዥ አፈፃፀምን የሚመለከት የምክርና  ስልጠና አለመስጠቱ ተገልጿል፡፡ በዚሁ ምክንያት የመንግስት መ/ቤቶች የአቅም ውስንነት እንዲኖርባቸው ከማድረጉም በተጨማሪ የግንዛቤና የስራ አፈፃፀም ክፍተት እንዳስከተለባቸው፣ የሚፈለገው ስራ በሚፈለገው ፍጥነት እንዲሄድ አለማድረጉ እንዲሁም በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችንና አገልግሎቶች ግዥ ዝርዝርን ለይተው ለማወቅና ስለአፈፃፀሙም በቂ ግንዛቤ ማግኘት እንዳላስቻላቸው፣ ከማዕቀፍ ግዥ የሚገኙ ጥቅሞችን እና የማዕቀፍ ግዥ ጠቀሜታን በወቅቱ እንዳይገነዘቡ እና በወቅቱ ፍላጐታቸውን እንዳያሣውቁ ያደረገ መሆኑን፤ ከዚህም የተነሳ ፍላጐት ሳያሳውቁ ግዥ የሚፈፅሙ መ/ቤቶች እንዳሉ እና ፍላጐታቸውን ያሣወቁ መ/ቤቶች ላይም የአቅርቦት እጥረት እንደሚያስከትልባቸው  የመ/ቤቶቹ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

152. በተጨማሪም አገልግሎቱ በግዥ ሂደቱ የሚገጥሙትን ችግሮች ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረኮችን  በማዘጋጀት በተሟላ ሁኔታ ተቀናጅቶ ያልሰራ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

153. በኦዲቱ ወቅት በዚህ ዙሪያ ከታዩት 13 መ/ቤቶች 10ሩ(77%) በአገልግሎቱ በኩል የመወያያ መድረክ ተዘጋጅቶ ጥሪ ተደርጐላቸው እንደማያውቅ የገለጹ ሲሆን፣ 3 መ/ቤቶች እና 5 የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች  ከ2003-2005 ዓ.ም አንድ ጊዜ በሰኔ 27 ቀን 2005 ዓ.ም. ጥሪ የተደረገላቸው እንደሆነና ከዛ ውጭ ግን መደበኛ በሆነ መልኩ ስለዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች የዕቃ አቅርቦት ሁኔታ አለማወያየቱን ጥሪ ተደርጐላቸው እንደማያውቅ የገለፁ መሆኑ እንዲሁም መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረክ ባለመኖሩም በመ/ቤቶች  እና በዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች መካከል የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት እንዳላስቻለ  ገልፀዋል፡፡

154. እንዲሁም በሰርቨይ መጠይቅ ከተላከላቸው 24 መ/ቤቶች ውስጥ ለ13ቱ(54%) የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በዕቃ ተረካቢ መ/ቤቱና በዕቃ አስረካቢ ድርጅቶች መካከል የሚፈጠሩትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል መደበኛ የሆነ የመወያያ  መድረኮችን (ወርክሾፖችና ሴሚናሮች ወዘተ) በማዘጋጀት ጥሪ ተደርጎላቸው እንደማያውቅ ለማወቅ ተችሏል።

155. በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲና በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መካከል በተፈፀመው የትብብር ስምምነት ላይ ጥር 15/2005 ዓ.ም. በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ላይ የሚታዩትን ችግሮች በመለየት፣ ችግሮቹ የሚፈቱበትን አግባብ ውይይት ማቅረብ እና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ መስራት እንዳለባቸው ቢቀመጥም ከስምምነቱ በፊትም ሆነ በኋላ ,,በመደበኛነት የመወያያ መድረክ በማዘጋጀት በቅንጅት ያልሰራ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

156. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግለቱ የስራ ኃላፊ ተጠይቀው አገልግሎቱ የምክር አገልግሎት በግሉ ዘርፍ ጥያቄ እንዳልቀረበለት እና የስልጠና አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑን እንዲሁም የመመወያያ መድረክን በተመለከተ ከ2003-2005 አንድ ጊዜ በ2005 ዓ.ም. ሰኔ ወር ላይ የመወያያ መድረክ እንዳዘጋጁ እና ሪፖርቱም ለኦዲት ቡድኑ እንደሚቀርብ የተገለፀ ሲሆን፤በተጨማሪም  የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ አገልግሎቱ የግዥ አፈፃፀም በሚመለከት የምክርና ስልጠና በመ/ቤቶች ጥያቄ ላይ የተመሰረተ የነበረ ሲሆን ስልጠናና  ምክር ለጠየቁ መ/ቤቶች የምክር ድጋፍ ብቻ እንደተሰጣቸው በመግለፅ ወደፊት አገልግሎቱ በዕቅድ ይዞ የስልጠናና የምክር አገልግሎት ለተጠቃሚ መ/ቤቶች እንደሚሰጥ እንዲሁም አገልግሎቱ አቅራቢዎችንና መ/ቤቶችን ብዙ ጊዜ አንድ ላይ ጠርቶ አወያይቶ የማያውቅ መሆኑን ነገር ግን ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ጋር በመሆን በየስድስት ወሩ ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ እንዳለው እና ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚጠራው መድረክ ላይም መልዕክት ሲያስተላልፍ መቆቱን ሆኖም ግን ወደፊት ቋሚ የባለድርሻ አካላት የውይይት ፕሮግራም እንደሚቀርፁ ምላሽ ሰጥተዋል።

157. ይሁን እንጂ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የመወያያ መድረክ የተዘጋጀበትና ለስንት መ/ቤቶችና አቅራቢ ድርጅቶች ጥሪ እንደተላለፈ የሚገልፅ ማስረጃ አልቀረበም።

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

158. በመንግስት መ/ቤች በጋራ የሚፈለጉ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀም ዙሪያ ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማስገኘት በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትና በባለድርሻ አካላት የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፤ከክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በመንግስት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ ተፈፃሚና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ከዚህ ዓላማ አንፃር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀም እና ውጤታማነት በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

- የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አልግሎት በደንቡ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና ሥራውን በተቀላጠፈና በጥራት ለማከናወን የሚያስችል የተሟላ የሰው ኃይል አደረጃጀት የሌለው እና በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን በተሟላ መልኩ አለማረጋገጡ እንዲሁም አገልግሎቱ እንደ ግዥው አፈፃፀም ሂደት ቅደም ተከተል የግዥ ሠነዶችንና መረጃዎችን ከጨረታ ሰነድ ጀምሮ ዕቃው ገቢ እስከሆነበት ድረስ ለይቶና አደራጅቶ ለብቻው እንዳላስቀመጠ ታውቋል፡፡
- አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን /Common user items/ በተመለከተ የመ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት በወቅቱ /ከመጋቢት1 እስከ ሚያዚያ 30 ቀን ድረስ ባለው ጊዜ/ እንደማይሰበስብ እና ፍላጎቶችን ለማደራጀት በአገልግሎቱ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ አለመኖሩ እንዲሁም ከባለበጀት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን ፍላጎት የሚያደራጀው ከገበያ ጥናት የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ አለመሆኑ ታውቋል፡፡
- አገልግሎቱ ከ2003-2007 ዓ.ም. የውጤት ተኮር ስርዓት የ5 ዓመት እስትራቴጅክ ዕቅድ ቢኖረውም የትኛው ተግባር በየትኛው ዓመት እንደሚሰራ ተለይቶ ያልተገለፀና በስትራቴጂው የታቀደው ተግባር ከዓመታዊ ዕቅድ ጋር በየዓመቱ በተጣጣመ መልኩ ያልተቀመጠ እና ከ2003-2005 ዓ.ም. በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ ለሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የመ/ቤቶችን ፍላጎት የያዘ የግዥ ዕቅድ እንደሌለው እንዲሁም ከ2003-2005 ዓ.ም. ድረስ ባሰባሰበው የግዢ ፍላጎት መሰረት በ2004ና በ2005 ዓ.ም. በመርሐ-ግብር የተደገፈ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ግዢ ዕቅድ በማዘጋጀት ለባለበጀት መ/ቤቶችና ለኤጀንሲው አለማሳወቁ ታውቋል፡፡
- አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች የማዕቀፍ ግዥ ውል ስምምነት ከመፈጸም ውጭ ዕቃ በመረከብ ግዥ አያከናውንም፤ በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መ/ቤቶቹ

በሚፈለጉበት ጊዜ ፣ መጠንና አይነት በተሟላ ሁኔታ እንዲያገኙ ካለማድረጉም በተጨማሪ የግዢ መፈፀሚያ ጊዜን ከመንግስት መ/ቤቶች የበጀት ዓመት/ፕሮግራም/ ጋር በማጣጣም አልወሰነም፡፡

- አገልግሎቱ እስከ ብር 100 ሚሊዮን በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚዘጋጅ ማንኛውንም የጨረታ ሠነድን በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ማጽደቅ ሲገባው በሥራ አመራር ቦርድ አጽድቋል፡፡ በተጨማሪም ከ10,000,000 ብር በላይ የሆኑ ዕቃዎችን በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ሳይሆን በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ግዥ ፈጽሟል፡፡
- አገልግሎቱ እጩ ተጫራቾች የግዥ ውልን ከመፈራረማቸው በፊት ውሉን መፈጸም የሚያስችል ብቃት እንዳላቸው ወጥ በሆነ መልኩ ባለማረጋገጡ በቅድመ ቴክኒክና በቴክኒክ ግምገማ ወድቀው በጨረታ እንዲያሸንፉ የተደረጉ ተጫራቾች እንዳሉ ታውቋል፡፡ እንዲሁም አገልግሎቱ በ2004 ዓ.ም. አሸናፊ የነበሩትን ስናፕና ራደካል ኃ/የተ/የግ ማህበራትን በጊዜ የማቅረብ ችግር እንዳለባቸው በተደጋጋሚ ከተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች ቅሬታ ቢቀርብም በ2005 እነዚህ ድርጅቶች በድጋሚ አሸናፊ ሆነው እንዲያቀርቡ የተደረገ መሆኑና ወጥ በሆነ መልኩ ለውል ማስከበሪያ ገንዘብ የማስተዳደሪያና በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ላልፈፀሙ አቅራቢ ድርጅቶች የመውረሻ ስርዓት የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡
- ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በአገር ውስጥ ጨረታ ጊዜ ዕቃውን ከተረከበ በኋላ ከ5 እስከ 10 ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን የክፍያ ሁኔታ ባለማመቻቸቱ ዩኒቨርስቲዎች፣ የሚኒስቴርና ባለስልጣን መ/ቤቶች የፋይናንስ ግዥና አሰራርን በመተላለፍ ለገንዘቡ ጥንቃቄ ባልተሞላበት ሁኔታ ከብር 50,000 በላይ በቼክ ከብር 74,476.24 እስከ ብር 3,030,859.26 ክፍያ በመፈፀም ግዥ ያከናወኑ መሆኑ፤እንዲሁም መ/ቤቶችም የዕቃ ርክክብ ሳይፈፅሙ ሞዴል 19 ቆርጠውና ካለዱቤ ሽያጭ/credit invoice/ በባንክ አካውንት ዝውውር በአንድ ጊዜ ግዥ ብቻ ለአንድ አቅራቢ ድርጅት 8 የመንግስት መ/ቤቶች በድምሩ በብር18,141,902 ቅድመ ክፍያ የፈፀሙ መሆኑ ታውቋል፡፡
- የመንግስት መ/ቤቶች ለሚያቀርቧቸው ቅሬታዎች በመመሪያው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የሚፈለገውን ምላሽ ከአገልግሎቱ እያገኙ አይደለም፡፡
- አገልግሎቱ ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር በሚያደርገው የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውል ላይ ዕቃውን የሚገዙ ወይም የሚረከቡ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝርና የመከታተያ ስርዓት አላካተተም እንዲሁም አገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች በማዕቀፍ ስምምነቱ ውልና በውሉ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀሙ መሆናቸውን በመከታተል ለመንግስት መ/ቤቶች ድጋፍ አላደረገም፡፡
- አገልግሎቱ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ /Specification/ ሲያዘጋጅ አግባብነት ያላቸው አካላት የሚያወጧቸውን በጋራ የሚፈለጉ የተመሳሳይ ዕቃ ደረጃዎችን በጨረታ ሰነድ ላይ በዝርዝር አልገለፀም፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓት በመዘረጋት ተግባራዊ አላደረገም እንዲሁም አገልግሎቱ በተዋዋለው ውል ላይ ስለዕቃው ጠቀሜታ፣ ተገቢ ጥንቃቄና ደረጃ ውን ወይም አለም አቀፍ ተቀባይነትን (ISO certificate) ያላካተተና ለመንግስት መ/ቤቶች የቀረቡ ዕቃዎች በተሟላ ሁኔታ በታወቁ መ/ቤቶች የናሙና ፍተሻ በማድረግ እንዲረጋገጥላቸው አልተደረገም፡፡ በተጨማሪም አገልግሎቱ

ለመ/ቤቶች የተገዙትን ዕቃዎች በሚፈለገው ስፔስፊኬሽን መሰረት መቅረቡን በባለሙያ አስፈላጊው ምርመራ እንዲደረግ አላደረገም፡፡

- አገልግሎቱ ከ2004-2005 ዓ.ም. ለማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የተፈራረመውን የውል ዓይነትና ዋጋ በገበያ ጥናት ላይ ተመርኩዞ አለመወሰኑ እና በመንግስት መ/ቤቶች ለግዥው የተመደበውን በጀትና የግዥው መጠን መመጣጠኑን በማረጋገጥ ማስተካከያዎችን አድርጎ እንደማያውቅ ታውቋል፡፡
- አገልግሎቱ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ውል ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከ3ወር በኋላ ለሚኖር ግዢ የዋጋ ልዩነት ሲኖር ማስተካከያ አላደረገም፡፡ እንዲሁም በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት ባወጣው የጨረታ ሰነድ ላይ የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝርና ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ አልተካተተም፡፡
- አገልግሎቱ በፈፀመው የግዥ ውል ወቅት ሰፊ የገበያ ጥናት የተደረገበት እቃዎች በሚፈለገው ጊዜና መጠን በተሟላ ሁኔታ ለመንግስት መ/ቤቶች እንዲቀርቡ ያላደረገ በመሆኑና ለመ/ቤቶች ከተገዙት ዕቃዎች ውስጥ የፎቶ ኮፒና የፕሪንተር ወረቀቶች፣ ቶነሮች፣ ፕሪንተሮችና የፋይል አቃፊ ላይ የጥራት ችግር የገጠማቸው መሆኑ፤ እንዲሁም 3 የመንግስት መ/ቤቶች 360 ዴስክ ቶፒ ኮምፒውተር በመግዛት ከአገልግሎቱ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በብልጫ ብር1,989,034 የከፈሉ መሆኑና ዋጋው ተመጣጣኝ አለመሆኑ ታውቋል፡፡
- አገልግሎቱ በወቅቱ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ ባለመፈፀሙና መ/ቤቶች የሚፈልጉትን ዕቃዎች ባለመግዛቱ 9 መ/ቤቶች በግላቸው በብር 121642598.47 ግዥ በመፈፀም፣ ለጨረታ ማስታወቂያ ብር 225225.79ና አገልግሎቱ ከገዛበት ዋጋ በላይ በብልጫ በብር 158704.68 በመገዛቱ በጋራ ከሚፈለጉ አገልግሎቶችና ዕቃዎች ጥቅል ግዢ ሊያስገኝ የሚገባውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያላስገኘ መሆኑ ታወቋል፡፡
- አገልግሎት የማዕቀፍ ግዥ ለሚፈፅሙ ለመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም በወቅቱ ለመንግስት ባለ በጀት መ/ቤቶች የግዥ ውሉን ኮፒ በመላክ እንዲያውቁት፣ የግዥ መረጃዎች በወቅቱ እንዲደርሳቸውና የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ ስለሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግገዢ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ አለመስራቱ ታውቋል፡፡
- አገልግሎቱ ከ2004-2005 ዓ.ም. በማዕቀፍ ስምምነት የግዥ አፈፃፀም ዙሪያ ለመንግስት መ/ቤቶች እና ለመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ለክልል መንግስታትና ለግሉ ዘርፍ የምክርና ሥልጠና አገልግሎት አለመስጠቱ፤ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአቅራቢ ድርጅቶችና በዕቃ ተረካቢ መ/ቤቶች መካከል የሚፈጠሩትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀት ተቀናጅቶ አለመስራቱ ታውቋል፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የዕቃ ግዥ ሥርዓት ሲታይ፤ ቀደም ብሎም በርካታ ችግሮች ያሉበትና አገልግሎቱ በቅርብ ጊዜያት ስራ የጀመረና ብዙ ችግሮችን እየፈታ እና ስርዓት በማስያዝ ላይ መሆኑ ቢታወቅም በኦዲቱ ግኝቶች ላይ አገልግሎት መ/ቤቱ የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅም የሌለውና በሚፈፅመው የግዥ ውል ሰፊ የገበያ ጥናት በማድረግ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ ጥራታቸውን የጠበቁ ዕቃዎች በሚፈለገው ጊዜና መጠን ለተጠቃሚ መ/ቤቶች እንዲደርሱ አለማድረጉን እንዲሁም በጋራ በሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎት ግዥ ሊገኝ የሚገባውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያላስገኘ ሲሆን፤ በኦዲቱ ለተገኙት የአሰራር ግድፈቶች ሊታረሙና የተሻለ አሰራር እንዲኖር ያስችላሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው ክፍል ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

159. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በደንቡ የተሰጠውን ኃላፊነት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግና ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስችል በመዋቅሩ መሰረት የተሟላ የሰው ኃይል አደረጃጀትና ግብዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

160. አገልግሎቱ በጋራ ለሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ተግባር ተጠያቂነትን ከማጠናከር አንፃር በአዋጁና አዋጅን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን ማረጋገጥ አለበት፡፡

161. በፌዴራል መንግስት ግዥና አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 23 የመንግስት መ/ቤቶችን የግዥ ሰነዶች የግዥ ክንውን እና የአቅራቢ ድርጅቶች የውል ስምምነት አፈፃፀም ገምግሞ ማስተካከያዎችን ለመውሰድ እንዲያስችል አገልግሎቱ እንደ ግዥው አፈፃፀም ሂደት ቅደም ተከተል የግዥ ሠነዶችንና ማስረጃዎችን ለይቶና አደራጅቶ ለብቻው ማስቀመጥ አለበት፡፡

162. አገልግሎቱ ለቀጣይ በጀት ዓመት የሚገዙ ግዥዎችን ከመ/ቤቶች የግዥ ዕቅድ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የመ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት በየዓመቱ ከመጋቢት1 እስከ ሚያዚያ 30 ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ሊለይና ሊያሰባስብ፣ እና ከባለበጀት መ/ቤቶች በቀረበው የግዥ ፍላጎት መሰረት በኤጀንሲው የተወሰኑትን ግዥዎች በአስር የስራ ቀናት ውስጥ በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት ደረጃ እና በሚገኝበት ቦታ በተለያየ ምድብ /በሎት/ መድቦና አደራጅቶ ሊይዝና ለግዥው አፈፃፀም አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር እንዲያስችል ተመሳሳይና ተቀራራቢ ፍላጎቶችን አንድ ላይ በማሰባሰብ ከገበያ ጥናት የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ ሊያደራጅ ይገባል፡፡

163. በእስትራቴጅክ ዕቅድ መሰረት በየዓመቱ ተመንዝረው የሚታቀዱ ተግባራት የመ/ቤቱን የስራ አፈፀፃም ለመለካትና የማሻሻያ ሃሳብ ለመውሰድ እንዲያስችል አገልግሎቱ በግልፅና በመቶኛ፣ የትኛው ተግባር በየትኛው ዓመት እንደሚሰራ ሊያስቀምጥ፣ ዕቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

164. በግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት የባለበጀት መ/ቤቶች የስራ ፕሮግራማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ግዢ በወቅቱ ለመፈፀም እንዲያስችላቸው የግዢ ፍላጎት መሰረት በመርሐ-ግብር የተደገፈ የሚገዛውን ዕቃና አገልግሎት ዓይነት፣ ግዥው የሚፈፀምበትን የገንዘብ ምንጭ፣ የግዥው ምድብ፣ ለግዥው የተያዘው የበጀት ግምት፣ የተመረጠው የግዥ ዘዴ የግዥው ዓይነትና ግዥን ለመፈጸም የሚወስደው ጊዜ /ጨረታ የሚወጣበት ወይም የሚካሄድበት እና ግዥው ተጠናቆ ርክክብ የሚፈፀምበትን ዕቅድ በማዘጋጀት የታወቁትን የግዥ ፍላጎቶች በሙሉ በግዥ ዕቅዱ ውስጥ እና

እንደ ግዥ ሁኔታ ለእያንዳንዱ ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዥ ዘዴ በመምረጥ ማመላከት እና ለባለበጀት መ/ቤቶችና ለኤጀንሲው ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

165. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሀገሪቷ ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማግኘት እንድትችል የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችም ሆነ አገልግሎቶች ግዥ በማቋቋሚያ ደንቡ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የመ/ቤቱን አቅም በማሳደግና የራሱ ዕቃዎችን ገዝቶ የሚያስቀምጥበት የዕቃ መጋዘን በመሥራት/ እንዲኖር በማድረግ መ/ቤቶችም ለጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የሚያውሉት በጀት በአንድ ማዕከላዊ በሆነ አካውንት እንዲከቱ በማድረግና ለመንግሥት መ/ቤቶች ዕቃዎችን እስከ ማስረከብ ያለውን የግዥ ሂደት ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

166. አገልግሎቱ የመንግሥት መ/ቤቶች ዕቃዎችን በሚፈልጉት መጠንና ጊዜ እየደረሳቸው መሆኑን ሊከታተልና በወቅቱ ካላገኙ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ለተጠቃሚው አካላት እንዲደርሱ ሊያደርግ፣ የመንግስት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን የግዥ ገንዘብ በበጀት ዓመቱ ለመጠቀም እንዲያስችላቸውና አላስፈላጊ የግዥ ዘዴ ውስጥ እንዳይገቡ የግዥ ፍላጎት ለመ/ቤቶች በጊዜ በመላክና አመታዊ የግዥ ዕቅድ በማውጣት የሚፈጽመውን ግዥ ከመ/ቤቶች የበጀት አመት /ፕሮግራም/ጋር በማጣጣም በገበያ ላይ ሰፊ አቅርቦትና ውድድር ሊኖር የሚችልበትን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ የግዥ መፈጸሚያ ጊዜን ሊወስን ይገባል፡፡

167. በአገልግሎቱ የግዥ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ በአዋጁ፣ በግዥ አፈፃፀም መመሪያ፣ ደንብና በኤጀንሲው በሚወጡ የአፈፃፀም ስርዓቶች መፈፀሙን ለማረጋገጥ እንዲያስችል በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ለሚፈፀም በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚዘጋጅ ማንኛውም የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ በማቋቋም በኮሚቴው ተቀባይነት ማግኘቱ ሊረጋገጥ በተጨማሪም ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ ዕቃዎችን በአለም አቀፍ ግዥ ጨረታ ግዥ ሊፈጽም ይገባል፡፡

168. የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ውል ተፈፃሚ እንዲሆን በተቀመጠው ጊዜ ከአቅራቢ ድርጅቶች ዕቃ እንዲያገኙ ለማድረግ እንዲረዳ አገልግሎቱ በግዥ መመሪያውና በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው የመመዘኛ መስፈርት መሰረት ብቃታቸውን ሊያረጋግጥ፣ ቀደም ባሉ ጊዜያት ለመ/ቤቶች ዕቃና አገልግሎት ያቀርቡ የነበሩ አቅራቢ ድርጅቶች በድጋሚ ለመወዳደር በግዥ ጨረታ ላይ እጩ ተወዳዳሪ ሆነው ሲቀርቡ በፊት የነበራቸው የሥራ አፈጻጸም እንደ አንድ መገምገሚያ መሥፈርት ሆኖ ሊታይ ይገባል፡፡

169. በዕቃና አገልግሎት አቅራቢዎችና በመ/ቤቶች መካከል መልካም የሥራ ግንኙነት ለመፍጠር እንዲያስችል በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ 16.26 ስለ ቅድመ ክፍያ አከፋፈል ሁኔታ እና በንዑስ አንቀፅ 1ና 2 እንዲሁም የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለትና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት በመጋቢት/2005 በተላለፈው ሴሪኩላር መሰረት

አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ጨረታ ጊዜ ዕቃውን ከተረከበ ወይም የመንግስት መ/ቤቶችም ዕቃውን ከተረከቡ በኃላ ከ5 እስከ 10 ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን የክፍያ ሁኔታ ሊያመቻች ወይም እንዲመቻች ሊያደርግ ይገባል፡፡

170. የመንግሥት ንብረት ግዥና ማስወገድ አገልግሎት የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱን ለማሻሻል እንዲረዳውና ግዥዎች ሳይዘገዩ በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመፈጸም እንዲያስችል አገልግሎቱ የተገልጋዮችን ቅሬታዎች ተቀብሎ ከሁለት እስከ አስር ቀናት ምላሽ ሊሰጥ እና የእርምት እርምጃዎችን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

171. ከግዥው ዓላማ አንፃር የመንግስት መ/ቤቶች የሚያጠፉትን ጊዜ ለመቆጠብ እንዲረዳ አገልግሎቱ የሚፈራረመው የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውል ላይ የአቅራቢው ኃላፊነትና ግዴታ፣ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር፣የግዢ ትዕዛዝ የሚተላለፍበትን፣ ርክክብና ክፍያ የሚፈፀምበትን እና ክትትልና ግምምገማ የሚደረግበትን ሥርዓት ሊያካትትና ተግባራዊ ሊያደርግ፣የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ድርጅት በውሉና በውሉ ላይ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀመ መሆኑን ሊከታተል እና ለመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዙሪያ ድጋፍ ሊያደርግ እንዲሁም አቅራቢዎች የውል ማስከበሪያ ብለው የሚያስይዙትን ገንዘብ በውሉ መሰረት መፈፀማቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሊኖረውና በውሉ መሰረት እንዳልፈፀሙ ሲያውቅ ገንዘቡን ሊወርስ ይገባል፡፡

172. በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 16.5 መሰረት የሚዘጋጀው የቴክኒክ መግለጫ በተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ እንደግዥው ዓይነት፣ ጠቀሜታና የቴክኒክ ባህርይን መሰረት በማድረግ አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎች በሙሉ ደረጃ /standard/ በማዘጋጀት በጨረታ ሰነዱ ላይ ለማካተት እንዲያስችል ጠንካራ የቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

173. ለመንግስት መ/ቤቶች የሚቀርቡ ዕቃዎች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ አገልግሎቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ደረጃ ላልወጣላቸው ደረጃ እንዲዘጋጅ በማድረግ እንዲሁም ለሁሉም ዕቃ የመመሪመሪያ መሳሪያዎች እንዲኖሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሁኔታዎች እንዲመቻች በማድረግ በአቅራቢዎች የሚቀርቡ ዕቃዎች ሙሉ በሙሉ በታወቀ መ/ቤት የናሙና ፍተሻ እንዲደረግላቸው በተጨማሪም የናሙና ፍተሻ በማስደረግ ብቻ ሳይሆን እቃ አቅራቢዎች ጋ አልፎ አልፎ በመሄድ የዕቃውን ጥራት በማረጋገጥ አገልግሎቱ ለመንግሥት መ/ቤቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ሊገዛና የመንግስት መ/ቤቶች በፌዴራል መንግስት በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀፅ 2 እና የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9 መሰረት ከክፍያ በፊት ሊደረጉ የሚገባቸውና በዕቃ ርክክብ መወሰድ የሚገባቸውን ጥንቃቄ ለመውሰድ እንዲያስችላቸው አገልግሎቱ ለመ/ቤቶች የተገዙትን ዕቃዎች በሚፈለገው ስፔስፊኬሽን መሰረት መቅረቡን ሊመረምር ወይም በባለሙያ አስፈላጊው ምርመራ እንዲደረግ እና

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የራሱን ባለሙያ በመላክ ሁኔታዎችን ሊያመቻች እንዲሁም ከምርመራ በኋላ የዕቃ ርክክብ እንዲፈፀም ሊያደርግ ይገባል፡፡

174. በደንብ ቁጥር 184/2002 ላይ የተቀመጠውን የአገልግሎቱን ዓላማ ለማሳካት እንዲረዳ እና የመንግስት መ/ቤቶች ለቁጥቁጥ ግዢና ለዋጋ ንረት እንዳይጋለጡ ለመንግስት መ/ቤቶች ተመሳሳይ በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ጥቅል ግዢ በመፈፀም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያስገኝ እና ያስገኘው የኢኮኖሚ ጥቅም ሊታወቅ ይገባል፡፡

175. በመንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ላይ በተሰጣቸው ኃላፊነት መሰረት ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲና የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈልጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር ላይ ወቅታዊ የሆነ የገበያ ጥናትና ለዋጋ ማስተካከያ የሚውል ጠቋሚ ዋጋ /price index/ አጥንተው እንዲሰጧቸው በመጠየቅ ወይም በድህረ ገፃቸው ላይ እንዲለቁ ለበላይ አካል በማሳወቅ አገልግሎቱ ለማዕቀፍ ግዥ የሚፈራረመውን የውል ዓይነትና ዋጋ፣ ለመንግስት መ/ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ለክልል መንግስታትና ለግሉ ዘርፍ የሚፈፅመውን ግዥ፣ለግዥው የተመደበው በጀትና የግዥው መጠን መመጣጠኑን በማረጋገጥ፣ በጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተውን የግዢ የዋጋ ለውጥ ማስተካከያዎችን ሲያደርግ በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፡፡

176. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተጫራች ድርጅቶች የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝርና ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜን በመረዳት አቅማቸውን አውቀው ለመጫረት እንዲያስችላቸውና በዕቃ አቅርቦት ጊዜ ለአገልግሎቱ የሚቀርብለትን አቤቱታና ቅሬታ ለመቀነስ እንዲረዳ አገልግሎቱ በሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ውስጥ የሚገዛቸውን ዕቃዎችና የማዕቀፍ ስምምነት የሚጠቀሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝርና ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ እንዲካተት ሊያደረግ ይገባል፡፡

177. የግዥ መረጃዎችን በወቅቱ ለመለዋወጥ እንዲረዳቸውና በየጊዜው የሚታዩ ችግሮችን ከመረጃ ላይ አይተው የመፍትሄ እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችላቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችንና የመ/ቤታቸውን መብትና ግዴታ በማወቅ የግዥ ሂደቱ እንዳይጓተት ለማድረግ በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ላይ በተገለፀው መሰረት እንደማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የጨረታ አሸናፊው ከተመረጠና የግዥ ውል ከተፈራረመ በኃላ ባሉት 5 ቀናት ውስጥ በኤጀንሲው መረጃ መረብ ላይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሙላት አገልግሎቱ ለህዝብ ይፋ እንዲደረግ ወይም የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም በወቅቱ የመንግስት ባለ በጀት መ/ቤቶች የግዥ ውሉን ኮፒ በመላክ እንዲያውቁት ሊያደርግ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖረው በማድረግ እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ሲስተም ስርዓት በመጠቀም የግዥ መረጃዎችን በወቅቱ ለባለድርሻ አካላት እንዲደርሱ ማድረግ አለበት፡፡

178. የባለድርሻ አካላት ስለአገልግሎቱና ስለኤጀንሲው ልዩነት በአግባቡ እንዲያውቁና አገልግሎቶች ለመለየትና በጋራ የሚገዙ ዕቃዎች ከሚያስገኘው ጥቅም አንፃር እንዲሁም በሥራው ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን አስቀድሞ ለመቀነስና ችግሮች ሲፈጠሩ በቀላሉ ለመፍታት እንዲያስችል አገልግሎቱ መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ጋርተቀናጅቶ ሊሰራ እንዲሁም የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት የምክርና ሥልጠና አገልግሎት በመስጠት እና በመገናኛ ብዙሃን፣ በስብሰባ፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፕ፣ በደብዳቤና በመወያያ መድረኮች ወዘተ ግንዛቤ ሊፈጥር ይገባል።

በመጨረሻም ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት፣ በናሙና ተመርጠው መረጃ የተሰበሰበባቸው መ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ስላደረጉልን የስራ ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን!!!

**አባሪ 1**

# <u>የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች</u>

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች<br>/Audit Issue/ | የኦዲት መስፈርቶች<br>/Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| 1. አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች፣ ለልማት ድርጅቶችና ለክልል መንግሥታት በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀም፤ የግዢ ደንብና መመሪያዎችን ተከትሎ መከናወኑን፣ ለተገልጋዮች አቤቱታ ተገቢውን ምላሽ መስጠቱን እና ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የግዢ ሂደት መኖሩን እንዲሁም የክትትል ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፡፡<br>1.1 አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች፣ ለልማት ድርጅቶችና ለክልል መንግሥታት በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ፤ የግዢ ደንብና መመሪያዎችን ተከትሎ ማከናወኑን እንዲሁም የግዢ ሂደት አደረጃጀት መፍጠሩን ማረጋገጥ፤ | 1.1.1 በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ግዢ የሚፈፀምላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝር በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊወሰን ይገባል |
| | 1.1.2 ዝርዝራቸው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መመሪያ የሚወሰን የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አጥንቶ ለመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በሚልከው መሠረት አገልግሎቱ ግዥ ሊያከናውን ይገባል፡፡ |
| | 1.1.3 አገልግሎቱ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥዎችን ለመፈፀም የሚያስችል የተሟላ የሰው ኃይል አደረጃጀት እና ግብዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 1.1.4 አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| 1.2 አገልግሎቱ የሚያከናውነው የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን እና የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታዎች ተቀብሎ ተገቢውን ምላሽ የሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ | 1.2.1 የመንግሥት ንብረት ግዥና ማስወገድ አገልግሎት የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታዎችን ተቀብሎ በሁለት ቀናት ውስጥ ምላሽ ሊሰጥ እና ከተገልጋዮች የቀረበው ቅሬታ ወይም አቤቱታ ተጣርቶ ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ በአገልግሎቱ የተቀመጡትን የእርምት እርምጃዎችን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.2.2 የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ዙሪያ ባዘጋጀው እስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት ዓመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| | 1.2.3 አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን /Common user items/ በተመለከተ የመ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት በየዓመቱ ከመጋቢት1 እስከ ሚያዚያ 30 ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ለቀጣይ በጀት ዓመት የሚገዙ ግዥዎችን ሊለይና ሊያሰባስብ ይገባል፡፡ |
| | 1.2.4 የመንግስት ንብረት ግዢና ማስወገድ አገልግሎት ባሰባሰበው የግዢ ፍላጎት መሰረት በመርሐ-ግብር የተደገፈ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ግዢ ዕቅድ ሊያዘጋጅ እና ለባለበጀት መ/ቤቶችና ለኤጀንሲው ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issue/ | የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | 1.2.5 አገልግሎቱ የግዥ ዕቅድ በሚያዘጋጅበት ወቅት የታወቁትን የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የግዥ ፍላጎቶች በሙሉ በግዥ ዕቅዱ ውስጥ እና ለእያንዳንዱ ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዥ ዘዴ በመምረጥ ሊያመላክት ይገባል፡፡ |
| | 1.2.6 አገልግሎቱ የሚፈራረመው የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውል ላይ የአቅራቢው ኃላፊነትና ግዴታ፣ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር፣ የግዢ ትዕዛዝ የሚተላለፍበትን፣ ርክክብና ክፍያ የሚፈፀምበትን እና ክትትልና ግምገማ የሚደረግበትን ሥርዓት ሊያካትትና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.2.7 የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ድርጅት በውሉና በውሉ ላይ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀመ መሆኑን አገልግሎቱ ሊከታተል እና ለመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዙሪያ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.2.8 አገልግሎቱ ኤጀንሲው አዘጋጅቶ በላከው የጨረታ ሰነድ መሰረት ሰነዱን ሊያሻሽል፣ የጨረታ ሰነዱን ሊገመግምና ሊያፀድቅ ይገባል፡፡ |
| | 1.2.9 በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ለሚፈፀም በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚዘጋጅ ማንኛውም የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በኮሚቴው ተቀባይነት ማግኘቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.2.10 አገልግሎቱ ከብር10 ሚሊዮን በላይ ዋጋ ያላቸው የማዕቀፍ ግዥዎችን በአለም አቀፍ ግዢ ጨረታ መግዛት ይኖርበታል፡፡ |
| | 1.2.11 አገልግሎቱ እጩ ተጫራቾች የግዥ ውልን ከመፈራረማቸው በፊት ውሉን መፈጸም የሚያስችል ብቃት እንዳላቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.2.12 አገልግሎቱ ለመንግሥት መ/ቤቶች በፊት ያቀርቡ የነበሩ የዕቃና አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች በድጋሚ ለመወዳደር የበፊቱ የሥራ አፈጻጸማቸውን ማየት ይኖርበታል፡፡ |
| | 1.2.13 አገልግሎቱ ለማዕቀፍ ስምምነት ተፈፃሚነት የተያዘውን የውል ማስከበሪያ ገንዘብ ሊይዝ፣ ሊያስተዳድር እና በውሉ መሰረት አለመፈፀሙን ሲያረጋግጥ ገንዘቡን ሊወርስ ይገባል፡፡ |
| 2. በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ እና ብቃት ባለው መልኩ በተመጣጣኝ ዋጋ፣ የተፈለገው ጥራት ያለው ዕቃ፣ በሚፈለገው መጠንና በተገቢው ጊዜ መከናወኑን መገምገም፤ | 2.1 አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች ተመሳሳይ ጥቅል ግዢ በመፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያስገኝ እና ያስገኘው የኢኮኖሚ ጥቅም ሊታወቅ ይገባል፡፡ |
| | 2.2 አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ለክልል መንግስታትና ለግሉ ዘርፍ በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የግዥ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 2.3 አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ሂደት በማጠናቀቅ ዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ለተጠቃሚው አካላት እንዲደርሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.4 አገልግሎቱ ከባለበጀት መ/ቤቶች በቀረበው የግዢ ፍላጎት መሰረት በኤጀንሲው የተወሰኑትን የመ/ቤቶችን ተመሳሳይ ፍላጎት አንድ ላይ በማሰባሰብ ግዢዎች በአስር የስራ ቀናት ውስጥ በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት ደረጃ እና በሚገኝበት ቦታ በተለያየ ምድብ/በሎት/ መድቦና አደራጅቶ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 2.5 አገልግሎቱ ከገበያ ጥናት የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ ከባለበጀት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን ፍላጎት ማደራጀት አለበት፡፡ |
| | 2.6 አገልግሎቱ ለማዕቀፍ ስምምነት ግዢ የሚፈራረመውን የውል ዓይነት እና ዋጋ በገበያ ጥናት ላይ ተመርኩዞ መወሰን አለበት፡፡ / |
| | 2.7 አገልግሎቱ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ /Specification/ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ባለስልጣን ወይም እንደግዢው ዓይነት አግባብ ያላቸው ሌሎች አካላት የሚያወጧቸውን ደረጃዎች በጨረታ ሰነዱ ዝርዝር ውስጥ ለማካተት ጠንካራ የቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ |
| | 2.8 በአገልግሎቱ የተዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የዕቃውን ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ ተገቢ ጥንቃቄ፣ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ ዲዛይን፣ አስተሻሸጉን፣ |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issue/ | የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | ምልክቱንና ደረጃውን ወይም አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሆኑን የውሉ አንድ ክፍል በማድረግና የአቅርቦቱን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ ሊያውል ይገባል፡፡ |
| | 2.9 አገልግሎቱ በአቅራቢዎች የሚቀርቡ ዕቃዎች በታወቀ መ/ቤት የናሙና ፍተሻ እንዲደረግላቸውና እንዲረጋገጥ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.10 አገልግሎቱ ለመ/ቤቶች የተገዙትን ዕቃዎች በሚፈለገው ስፔስፊኬሽን መሰረት መቅረቡን ሊመረምር ወይም በባለሙያ አስፈላጊው ምርመራ እንዲደረግ ሁኔታዎችን ሊያመቻችና ከምርመራ በኋላም አስፈላጊው የዕቃ ርክክብ እንዲፈፀም ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.11 አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ጨረታ ጊዜ ዕቃውን ከተረከበ በኃላ ከ5 እስከ 10 ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን የክፍያ ሁኔታ ሊያመቻች ወይም እንዲመቻች ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.12 አገልግሎቱ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ውል ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከ3ወር በኋላ ለሚኖር ግገር የዋጋ ለውጥ ወይም ማስተካከያ ማድረግ እንደሚቻል በጨረታ ሰነዱ ላይ በማመላከት ማስተካከያ ሊያደረግ ይገባል፡፡- |
| | 2.1.3.አገልግሎቱ በሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ የሚገዛውን ዕቃዎችና የማዕቀፍ ስምምነት የሚጠቀሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዝርዝር፣ የማስረከቢያ ቦታ፣ ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜና መጠን፣ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ሁኔታ፣ አፈፃፀሙንና የግዥው ውል ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲካተት ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.14 አገልግሎቱ ለመንግሥት መ/ቤቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ሊገዛ ይገባል፡፡ |
| | 2.15 አገልግሎቱ በየጊዜው በኤጀንሲው የሚመዘገቡና የሚታገዱ የዕቃና አገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 2.16 አገልግሎቱ የግዥ ሂደቱ ከመ/ቤቶች የበጀት አመት /ፕሮግራም/ የተጣጣመ በገበያው ላይ ሰፊ አቅርቦት የሚገኝበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረገና ሰፊ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል በማድረግ የግዥ መፈጸሚያ ጊዜን ሊወስን ይገባል፡፡ |
| 3. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥን በተመለከተ በደንቡ መሰረት የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የመረጃ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፤ | 3.1 አገልግሎቱ እንደ ግዥው አፈፃፀም ሂደት ቅደም ተከተል የግዥ ሠነዶችንና መረጃዎችን ለይቶና አደራጅቶ ለብቻው ማስቀመጥ አለበት፡፡ |
| | 3.2 አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ለክልል መንግስታትና ለግሉ ዘርፍ የግዥ አፈፃፀምን የሚመለከት የምክርና ሥልጠና አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 3.3 አገልግሎቱ የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም በወቅቱ የመንግስት ባለ በጀት መ/ቤቶች የግዥ ውሉን ኮፒ በመላክ እንዲያውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3.4 አገልግሎቱ በቂ ቁጥር ያላቸው ተወዳዳሪዎች በግዢ ጨረታ እንዲሳተፉ ለማድረግ አገራዊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ቢያንስ አንድ ጊዜ አሣትሞ በማውጣት እና ሌሎች ተጨማሪ ስልቶችን በመጠቀም የጨረታ ጥሪ ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡ |
| | 3.5 አገልግሎቱ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከኤጀንሲው፣ ከመንግስት መ/ቤቶችና ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖረው እና የኢንፎርሜሽንቴክኖሎጅ ሲስተም ስርዓት በመጠቀም የግዥ መረጃዎችን(ዕቅዶች፣ሪፖርቶች፣ መመሪያዎችና የመሳሰሉት) በወቅቱ እንዲደርሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3.6 አገልግሎቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በማዕቀፍ ስምምነት የግዢ ሂደት ላይ በአቅራቢ ድርጅቶችና በዕቃ ተረካቢ መ/ቤቶች መካከል የሚፈጠሩትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረኮችን |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issue/ | የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
| --- | --- |
| | (ወርክሾፖችና ሴሚናሮች ወዘተ) በማዘጋጀት ተቀናጅቶ ሊሰራ ይገባል፡ |
| | 3.7 አገልግሎቱ የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዢ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት በመገናኛ ብዙሃን፣ በስብሰባ፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፕ፣ በደብዳቤና በመወያያ መድረኮች ወዘተ ግንዛቤ ሊፈጥር ይገባል፡፡ |
| | 3.8 አገልግሎቱ በጋራ ለሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዢ የተመደበውን ጠቅላላ በጀትና በሪፖርት አደራረግ ዙሪያ ከመንግስት መ/ቤቶች ጋር የመግባቢያ ሰነድ (Mou) ወይም አስገዳጅ የሆነ ኃላፊነት ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 3.9 አገልግሎቱ ከግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ወይም ከሌሎች ምንጮች በተገኘ የገበያ መረጃ የዕቃዎች ዋጋ ጥናት መሰረት ለግዥውየተመደበው በጀትና የግዥው መጠን መመጣጠኑን ሊያረጋግጥና ማስተካከያዎችንም ሊያደርግ ይገባል፣ |
| | 3.10 አገልግሎቱ ለአሸናፊና ተሸናፊ ተጫራቾች ውጤቱን በደብዳቤ ሊገልጽ፣ ለተሸናፊዎችም የተሸነፉበትን ምክንያትና የአሸናፊውን ተጫራች ማንነት ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ |